unesco

United Nations
Office on Drugs and Crime

# ተማሪዎችን ለፍትሃዊ ማህበረሰብ ግንባታ ማብቃት

## ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የተዘጋጀ የሐቀኝነት ማስተማሪያ



Education 2030

## ዩኔስኮ UNESCO ፤ በትምህርት አለም አቀፍ መሪ

ትምህርት የዩኔስኮ ተቀዳሚ ተልእኮ (አጀንዳ) ነው፡፡ ለዚህም ምክንያቱ መሰረታዊ የሰው ልጆች መብት ብቻ ሳይሆን የሰላም እና ዘላቂ ልማት መሰረት በመሆኑም ጭምር ነው፡፡ ዩኔስኮ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (ተመድ) የትምህርት ልዩ ኤጀንሲ (specialized agency) ሲሆን በአለም አቀፍ እና በአህጉራት ደረጃ የትምህርት ልማትን ለማጎልበት፣አገሮች ሁሉንም ተማሪዎች የማገልገል እና ተግዳሮቶችን የመቋቋም አቅማቸውን የሚያጠናክር አመራር ይሰጣል፡፡

በተጨማሪም ዩኔስኮ በልዩ ሁኔታ የጾታ እኩልነት እና አፍሪካ ላይ ትኩረት አድርጎ አሻጋሪ (ለዋጭ) በሆነ የትምህርት አሰጣጥ (transformative learning) አማካኝነት በየጊዜው የሚከሰቱ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ

## የ2030 አለም አቀፍ የትምህርት አጀንዳ

የ2030 አለም አቀፍ የትምህርት አጀንዳ ድህነትን በ2030 ለማጥፋት የተቀረጹት አስራ ሰባቱ ዘላቂ የልማት ግቦች አካል ሲሆን ዩኔስኮ እንደ ተመድ የትምህርት ኤጀንሲነቱ ይህን አለም አቀፍ አጀንዳ የማስተባበር እና የመምራት ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡ትምህርት እነዚህን ዘላቂ የልማት ግቦች ለማሳካት የግድ አስፈላጊ በመሆኑ ራሱን የቻለ (የራሱ የሆነ) ግብ ተቀምጦለታል፡፡ ትምህርትን የተመለከተው በተራ ቁጥር 4 የተገለጸው ግብ “ለሁሉም ሰው አካታች ፍትሃዊና ደረጃውን የጠበቀ ትምህርት ማረጋገጥ እና የእድሜ ልክ የመማር እድሎችን ማበረታታትና መደገፍ” እንደሆነ ይገለጻል፡፡ ይህን ሰፊ ግብና ግዴታዎችን ለመፈጸም የሚያስችል መመሪያ በ2030 የትምህርት የተግባር ማዕቀፍ ላይ ሰፍሮ ይገኛል፡፡

Published in 2024 by the United Nations Educational, Scientific and Cultural Organization, 7, place de Fontenoy, 75352 Paris 07 SP, France and the United Nations Office on Drugs and Crime, PO Box 500, 1400 Vienna, Austria

© UNESCO and the United Nations, 2024

ISBN 978-92-3-100683-8

This publication is available in Open Access under the Attribution-ShareAlike 3.0 IGO (CC-BY-SA 3.0 IGO) license (http://creativecommons.org/licenses/by-sa/3.0/igo/). By using the content of this publication, the users accept to be bound by the terms of use of the UNESCO Open Access Repository (https://www.unesco.org/en/open-access/cc-sa).

Images marked with an asterisk (*) do not fall under the CC-BY-SA license and may not be used or reproduced without the prior permission of the copyright holders.

The designations employed and the presentation of material throughout this publication do not imply the expression of any opinion whatsoever on the part of UNESCO or the United Nations concerning the legal status of any country, territory, city or area or its authorities or concerning the delimitation of its frontiers or boundaries.

The ideas and opinions expressed in this publication are those of the authors; they are not necessarily those of UNESCO or the United Nations and do not commit these Organizations.

Inside icons: UNESCO/Aurelia Mazoyer and Anna Mortreux
Cover image credit: Angelina Bambina/Shutterstock.com*
Designed by UNESCO/Anna Mortreux

This educational and training handbook was translated and published into Amharic with the financial support of the Government of Malta.

ይህ የትምህርትና የስልጠና መምሪያ የማልታ መንግስት ባደረገው የገንዘብ ድጋፍ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ታትሟል።

# አ ጭ ር ማ ጠ ቃ ለ ያ

## ተማሪዎች ፍትሃዊ ለሆነ ማህበረሰብ የበቁ ይሆኑ ዘንድ ሐቀኝነትን በትምህርት ቤቶች ማስተማር

የትምህርት ጠቀሜታ የሚመነጨው የመጭውን ትውልድ እሴቶች በመቅረጽ ካለው ሃይል እና በመረጃ የተመሰረተ ውሳኔ እንዲወስኑ የሚያስችላቸውን እውቀት ከማስጨበጡ ነው። በመሆኑም በየጊዜው የሚነሱ እንደ ሙስና ያሉ ተግዳሮቶችን በትምህርት፣ግልጸኝነት፣ተጠያቂነት እና የሕግ በላይነትን በመሰሉት መንገዶች ሊፈቱ ይገባል።

ይህ በተመድ የወንጀል እና አደንዛዥ ዕፅ ጽ/ቤት (UNODC) እና በተመድ የትምህርት ፣ ሳይንስና የባሕል ድርጅት (UNESCO) የተዘጋጀው የትምህርት (ስልጠና) መምሪያ ለዚህ ጉዳይ መፍትሔ (ምላሽ) እንዲሆን ታስቦ ነው። አላማ ያደረገውም መሰረታቸውን በሐቀኝነት ሥነ-ምግባር እና የሕግ የበላይነት ላይ በጣሉ ማህበረሰቦች ውስጥ የነቃ ተሳትፎ የሚያደርጉ ቀጣይ ትውልድ አባላትን የሚያነቃቁ እና የሚያዘጋጁ መምህራንን ነው። ይህ የመምህራን የትምህርት (ስልጠና) መምሪያ በ2019 በወጡ (በታተሙ) ሁለት ህትመቶች ላይ ተመስርቶ እና ጎልብቶ የቀረበ ነው።

ይህ የስልጠና መምሪያ ትምህርት አለም አቀፍ ተግዳሮቶችን በለተይም ከሐቀኝነት ጉድለት የሚመነጩ ችግሮችን ለመቅረፍ አስፈላጊ የሆኑትን እውቀትን ፣ ክህሎትን ፣ ባህርያትን እና እሴቶችን ለማጠናከር ያለውን የማሻገር (የመለወጥ) ሃይል በጉልህ ያሳያል። በተጨማሪም ትምህርት ምክንያታዊና የጠለቀ አስተሳሰብን (critical thinking)፣ ሌሎችን እንደራስ አድርጎ ለመረዳት መጣርን (empathy) ፣ ሥነ-ምግባር የተላበሰ ባህሪን እንዲሁም ፍትህን እና እኩልነትን ለማስፈን ያለውን ቁርጠኝነት ለማጎልበት የሚጫወተውን ሚና በአጽንኦት ያሳያል።

**190 የተመድ ፀረ-ሙስና ኮንቬንሽን (ስምምነት) ፈራሚዎች**

ሙስናን ለመዋጋት እና ለመከላከል ማህበረሰብ አቀፍ አካሄድ (whole society approach) ለመከተል ተስማምተዋል ።

ይህ የስልጠና መምሪያ ወጣቶች የሙስና ተግባራትን እንዲጠየፉ ፣ የለውጥ ሃይል (መሳሪያ) እንዲሆኑ ፣ ሐቀኝነትን እንዲያበረታቱ እና እንዲያስፋፉ እንዲሁም የዴሞክራሲ እሴቶችን እንዲጠብቁ የሚያስችላቸውን ብቃት ለማጎልበት የተቀረጸ የትምህርት መልመጃዎች (ተግባራት) ፣ የትምህርት እቅዶች እና የክፍል ውጭ (የመስክ) ግብአቶችን ይዟል።

UNESCO unesco

"ጦርነቶች በወንዶች እና በሴቶች አእምሮ ውስጥ የሚጀምሩ ስለሆነ በዚሁ በወንዶች እና በሴቶች አእምሮ ውስጥ ነው የሰላም ማስከበርያዎች መገንባት ያለባቸው"

United Nations
Office on Drugs and Crime

# ተማሪዎችን ለፍትሃዊ ማህበረሰብ ግንባታ ማብቃት

## ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የተዘጋጀ የሐቀኝነት ማስተማሪያ መምሪያ

# መቅድም

ትምህርት መሰረታዊ ለውጥ የማምጣት ሃይል አለው፡፡ የመጭውን ትውልድ እሴቶች በቅርጽና እንዲሁም ተማሪዎች የማህበረሰባቸውን ልማትና አስተዳደር የሚመለከቱ የወደፊት ውሳኔዎቻቸው እና መልካም ሥነ-ምግባር የተላበሱ እንዲሆኑ በማዘጋጀት እረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡እንደ ሙስናና የሐቀኝነት እጦት የመሰሉ የወቅቱ ተግዳሮቶች በመላው አለም ላሉ በርካታ ማህበረሰቦች አሳሳቢ ፈተና ናቸው፡፡ ሙስና ሰዎች መብቶቻቸውን በአግባቡ እንዳይጠቀሙ እና እራሳቸውን እንዳያሳድጉ (እንዳያጎለብቱ) እንቅፋት ይሆናል፡፡ ሙስና ለትምህርት ያላቸውን ተደራሽነት በማሰናከል ፤ሴቶችን ፣ ህጻናትና ድሆችን በተለየ ሁኔታ በከፍተኛ ደረጃ ይጎዳል፡፡ ለዚህም ምክንያቱ እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች በዋናነት የመንግስትን የትምህርት ተቋማት የሚጠቀሙ በመሆኑ፤የትምህርት አገልግሎት ለማግኘት ኢ-መደበኛ ክፍያ የመፈጸም አቅም ስለሌላቸው እና የህግ ከለላ ለማግኘት ያላቸው አቅም ዝቅተኛ በመሆኑ ነው፡፡ ሙስና በተቋማትና ስርአቶች ላይ የሚኖርን የህዝብ አመኔታ በመሸርሸር የሕግ የበላይነትን ያዳክማል፡፡

ልጆች እና ወጣቶች ሐቀኛና ሙስናን የሚጸየፉ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን እውቀት፣ክህሎትና እሴቶች እንዲያገኙ በማድረግ ትምህርት በማህበረሰብ ውስጥ መልካም ሥነ-ምግባር የተላበሰ ባህሪ እንዲጎለብት ያበረታታል፡፡ የአለም አቀፍ የዜግነት ትምህርት (global citizenship education) ተማሪዎች እነዚህን ተግዳሮቶች እንዲረዱ እና የሙስና ልምዶችን እንዲጸየፉ የሚያግዛቸው ከመሆኑ በተጨማሪም መብታቸውን የሚረዱ እና በማህበረሰባቸው ውስጥ የሐቀኝነት ባህል እንዲጎለብት ተግተው የሚሰሩ ዜጎች እንዲሆኑ ያዘጋጃቸዋል፡፡

የሐቀኝነት እሴቶችን ማስረጽ ከለጋ እድሜ ይጀምራል፡፡ መምህራን ወጣቶች አሳሳች መረጃን እና ፕሮፖጋንዳን መቋቋም የሚያስችል ምክንያታዊና የጠለቀ አስተሳሰብ ክህሎትን የማስረጽ፣ሐቀኛ እንዲሆኑና መንግስታትን ለሚፈጽሙት ተግባር ተጠያቂ የማድረግ ዝግጅት እንዲኖራቸው የማድረግ ሃላፊነት አለባቸው፡፡ በተጨማሪም ወጣቶች የማህበራዊ ኑሮ ልምምድ ሒደት (socialization process) የሚጀምሩበት ጊዜ ወላጆች ፣ ትምህርት ቤቶች እና ሕብረተሰቡ እነዚህን እሴቶች የማስተማር እና ተምሳሌት (አርአያ) የመሆን ቁልፍ ሚና ሊጫወቱ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ታዳጊ ወጣቶች ማህበራዊ ደንቦችን (socital norms) ፣ ኃላፊነት እና አብሮ መኖርን የሚማሩት በማህበራዊ ኑሮ ልምምድ ወቅት ስለሆነ ነው፡፡

ይህ የስልጠና (ትምህርት) መምሪያ በዩኔስኮ እና በተመድ ወንጀልና አደንዛዥ እፅ ጽህፈት ቤት ትብብር የተዘጋጀ ነው፡፡ አላማውም ሐቀኝነትን የሚያስተምሩ መምህራን እንደየ አዉዱ (ሁኔታው) በቀላሉ እያስማሙ ጥቅም ላይ ሊያውሏ የሚችሏቸውን የትምህርት ማቴሪያሎችን ማቅረብ ነው፡፡

አላማውም ሐቀኝነት ፣ ሥነ-ምግባር ፣ ከአድሎ የነጻ እና የሕግ የበላይነት ቁልፍ የማህበረሰብ አምዶች የሆኑበትን አለም አቀፍ ሕብረተሰብ እንዲፈጥር ማገዝ ሲሆን ይህም በበኩሉ በተመድ ቻርተር የሰፈሩ እሴቶችን ያጠናክራል፡፡ ወጣቶች ከሌሎች ጋር ያላቸው ግንኙነት በመልካም ሥነ-ምግባር የተመሰረተ እና የኃላፊነት ስሜት ያለበት እንዲሁም በማህበረሰባቸው ውስጥ ሐቀኝነት ፣ ፍትህ እና እኩልነት እንዲሰፍን በትጋት የሚሰሩ የለውጥ ሃይሎች እንዲሆኑ ማነቃቃት ነው፡፡ ይህ ማቴሪል የ2030 የዘላቂ ልማት አጀንዳን ለማሳካት ቁልፍ የሆኑትን፤ በግብ 4 የተጠቀሰው ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት ማረጋገጥ እና በግብ 16 የሰፈሩት ሰላም ፣ ፍትህ እና ጠንካራ ተቋማት ያሉት ግቦች ይፈጸሙ ዘንድ ቀጥተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡

**ስቴፋኒያ ጂያኒኒ**
የትምህርት ረዳት ዳይሬክተር ጀነራል
የተመድ የትምህርት የሳይንስና የባህል ድርጅት

**ጆን ብራንዶሊኖ**
የአለም አቀፍ ስምምነት ጉዳዮች ክፍል ዳይሬክተር
የተመድ ወንጀልና አደንዛዥ እፅ ጽ/ቤት

# ምስጋና

ይህ የትምህርትና የስልጠና መምሪያ ለመምህራን የተዘጋጁ ተከታታይ የማስተማሪያ ግብአቶች አካል ነው፡፡

UNESCO እና UNODC ይህን ህትመት በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ ጊዜያቸውን ፣ ጉልበታቸውን እና እውቀታቸውን ተጠቅመው ረቂቁን በማዘጋጀት ፣ በአርትኦት እንዲሁም ለመጨረሻ ውጤት በማብቃት ረገድ ከዋናው ደራሲ ሳይመን ጀንኪንስ (Simon Jenkins) ጀምሮ ለተሳተፉ ሰዎች እና አካላት ልባዊ ምስጋናቸውን ያቀርባሉ፡፡

ይህ መምሪያ የተዘጋጀው በቀድሞ የሰላምና ዘላቂ ልማት ክፍል ዳይሬክተር ቪቤክ ጀንኪንስ ፣ የዩኔስኮ (UNESCO) የትምህርት ሴክተር የአለም አቀፍ ዜግነትና የሰላም ክፍል አላፊ ሲሲሊያ ባርቤሪ ፣ የUNESCO የሙስናና የኢኮኖሚ ወንጀሎች ቅርንጫፍ አላፊ ብሪጅት ስትሮቤል ሻው እና የሙስናና ኢኮኖሚ ወንጀሎች “ቴማቲክ” ድጋፍ ክፍል ኃላፊ ጂአቫኒ ጋሎ ክትትልና ቁጥጥር ነው፡፡

ይህ ማቴሪያል በ UNESCO እና በ UNODC ዋና መስሪያ ቤቶች እንዲሁም የየሃገሮች ቅርንጫፍ ቢሮዎች ካሉ ሰራተኞች እውቀት ፣ልምድ እና አስተውሎት በእጅጉ ተጠቅሟል፡፡

ህትመቱን በማስተባበር ለመሩ ከ UNESCO ኢስሚኒ አኒሞጂያኒ ፣ ኢሎዲ ቤት ሲዮ ፣ ኩዋኒ ኪረ ኩዋኒ እና ታሪክ ታላል ሞሳድ ፣ ከ UNESCO ለሉሉዋ አሳድ ፣ ፐሪንሰስ ቺሬየሮ ፣ ሮበርታ ፍላሽ ፣ ቢያንካ ኮፐ እና ኑኃሚን ጥበቡ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

ለሙስናና የኢኮኖሚ ወንጀሎች ቅርንጫፍ (CEB) ባጠቃላይ እና ለፍራንቼስኮ ቼቺ ፣ ጂአቫኒ ጋሎ ፣ ሊዮርዶ ፓራዲሶ ፣ ጂሊያ ፒልግሪም ፣ ጄሰን ሪቼልስ እና ብሪጂት ስትሮቤል ሾው በተለይ ምስጋና እናቀርባለን፡፡ ከ UNESCO ጃሚል ኤደን ቤን አብደላ ፣ ማርታኬ ፣ ሮሚና ካስማን ፣ ሄዝር ማን ፣ ሊዲያ ማዚሊ ፣ ሊዲያ ሮናሬክት ፣ ማቲልድ ስቴሎሮፍ እና ዩኪዮ ው ላበረከቱት ግብአት ባለውለታ ነን፡፡ በተጨማሪም በUNESCO የፍልስጤም ቋሚ ተጠሪ (ወኪል) ሳራ አቡናዳ ላበረከቱት ግብረ መልስ (feedback) ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

በመጨረሻም UNESCO እና UNODC ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ባለሙያዎች ምክር በከፍተኛ ደረጃ የተጠቀመ መሆኑን መግለጽ ይወዳሉ፡፡ እነሱም፡ - ሳራ ዲክስ (UNDP) ፣ ጊቹንግ ሊ (UNDP) ዚኪ ማይ ፣ ስቴፈን ሜንክ አኒኒዮ (Step Up Nigeria) ጂናን ካራሜህ ሻያ ፣ ባደር ሸሃያብ ፣ ሉቺያና አስፐር ናልዴዝ (Public Ministry of the Federal District and Territories, the Federative Republic of Brazil) እና አኒስ ዩሳል ዮሶፍ ናቸው፡፡

# ማውጫ


ዩኔስኮ (UNESCO) ፤ በትምህርት አለም አቀፍ መሪ ........ ii
የ2030 አለም አቀፍ የትምህርት አጀንዳ ........ ii
አጭር ማጠቃለያ ........ iii
መቅድም ........ iv
ምስጋና ........ v
ማውጫ ........ vi

**ክፍል 1 መግቢያ ........ 11**

1.1 ሐቀኝነት (Integrity) ምንድን ነው? ........ 12
1.2 ሐቀኝነትን የማስተማር አስፈላጊነት ........ 12
1.3 የመምህሩ መምሪያ አላማ ........ 13
1.4 ይህ መምሪያ ለማን ተዘጋጀ? ........ 13

**ክፍል 2 መልመጃዎችን ጥቅም ላይ ለማዋል መዘጋጀት ........ 15**

ሰንጠረዥ 1 ተማሪዎች ምን ያህል ማድረግ ይችላሉ? ........ 17
ሰንጠረዥ 2 ሴቶች ለምን ከፍተኛ ጉዳት (በደል) ይደርስባቸዋል፡፡ ........ 18
ሰንጠረዥ 3 የባህል ሚና እና በሐቀኝነት ላይ ያለውን ተጽእኖ መገንዘብ ........ 18
ሰንጠረዥ 4 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ግብአቶች ከ “አለምአቀፋዊ ግብአት ለጸረ-ሙስና ትምህርት እና ወጣቶችን ማብቃት” የተገኘ (The Global Resource for Anti -Corruption Education and Youth Empowerment- GRACE) ........ 19

**ክፍል 3 የትምህርት መልመጃዎች(ተግባራት) ዝርዝር ........ 25**

3.1. የክፍል ውስጥ እና የክፍል ውጭ መልመጃዎች ጠቅለል ያለ እይታ ዳሰሳ ........ 27
3.2 የክፍል መልመጃዎች ........ 29
ሰንጠረዥ 5 ጾታ እና የመሰረታዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት እንቅፋቶች ........ 36
ሰንጠረዥ 6 ሙስና በመቃወም ያጋለጡ ሴቶች ታሪኮች ........ 60
3.3 የክፍል ውጭ ግብአቶች ወይም መልመጃዎች (ተግባራት) ........ 63

**ክፍል 4 የምዘና ዘዴዎች (መንገዶች) ........ 69**

ሰንጠረዥ 7 ተማሪዎች ስለ ሐቀኝነት እና ተዳዳኝ ጽንሰ ሃሳቦችን የቀሰሙትን ትምህርት መገምገም (መመዘን) ........ 71
አባሪ I- የቁልፍ ቃላት መፈለጊያ ........ 74
አባሪ II- የርዕሰ ጉዳይ መፈለጊያ ........ 75

ክፍል 1

# መግቢያ



## 1.1 ሐቀኝነት (INTEGRITY) ምንድን ነው?

"ቀኝነት ማለት ሰው በማይመለከትበት ሳይቀር ጊዜ ተገቢውን ነገር ማድረግ ነው"

ሲ ኤስ ሉዊስ

ሐቀኝነት የሚደርስብንን ጫና ወይም ፈተና በመቋቋም በውሳኔዎቻችንና ስራዎቻችን ወቅት የሥነምግባር መርሆዎችን በተለይም ታማኝነትን በወጥነት መከተል ማለት ነው፡፡ ግላዊ ሐቀኝነትን (Personal integrity) እና ማህበረሰባዊ ሐቀኝነትን (Public integrity) መለየት አስፈላጊ ነው፡[1] ማህበረሰባዊ ሐቀኝነት ማለት ከግለሰብ (ግላዊ) ጥቅም ይልቅ የማህበረሰብን ጥቅም በማስቀደም ለማስጠበቅ ሲባል የጋራ የሆኑ የሥነ-ምግባር እሴቶችን ፣ መርሆዎን እና ህግጋትን መከተል ማለት ነው፡፡

በተመድ ወንጀል እና አደንዛዥ እጽ ጽ/ቤት ዩኒቨርስቲ የሥነ-ምግባርና ሐቀኝነት ሞጁሎች ውስጥ ሐቀኝነት "የእምነቶች ውሳኔዎችና ተግባራት መጣጣም እና ለእሴቶችና መርሆዎች ወጥና ቀጣይ በሆነ መንገድ መገዛት" የሚል ትርጉም ተሰጥቶት ይገኛል[2]

ከባድ ወይም አስቸጋሪ የሆኑ ውሳኔዎችን ለመወሰን በምንገደድበት ጊዜ ግልጽና የማያሻማ መልስ እንደሌለው ይሰማናል፡፡ይሁንና ውሳኔው ትክክል (ተገቢ) በሆነና ባልሆነ መካከል ያለ ምርጫ እንደሆነ ደመነፍሳችን (intuition) ይነግረናል፡ ፡ በሐቀኝነትና ሥነ-ምግባር ላይ የሚያደርጉ ውይይቶች ተገቢ (ልክ) በሆነና ልክ ባልሆነ መካከል ያለውን መሰረታዊ ልዩነት የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ይህን መሰል ውሳኔዎች አንድን የምግብ ዓይነት ከሌላው ለመምረጥ ከመወሰን ወይም አንድን የሂሳብ ጥያቄ መልስ ትክክል መሆኑን ያለመሆኑን ከመወሰን የበለጠ ከባድ ነው፡፡[3]

ሐቀኝነት የፍትሃዊና ሰላማዊ ማህበረሰቦች መሰረታዊ አምድ ነው፡፡ ዜጎች በመንግስት፣ በግል ሴክተሩና በሚዲያዎች ላይ ለሚኖራቸው አመኔታ ሊሟላ (ሊኖር) የሚገባው ቅድመ ሁኔታ ነው፡፡ የሐቀኝነት ጉድለት የመሪዎች ፣ የሚመራቸው ተቋማትና የሚከተሏቸው የአሰራር ሂደቶች ስምና ክብር ያጎድፋል፡፡ ይህም በበኩሉ ዜጎች በመንግስታቸው ውጤታማነት ያላቸው እምነት እንዲሸረሸር ያደርጋል፡፡ ሐቀኝነትን የተከተለ የውሳኔ አሰጣጥ በማህበረሰቦች ውስጥ ለሚሰፍን የፍትህ እና እርትዕ ስሜት አስተዋጽኦ በማበርከት ሙስናን የሚጸየፍ ባህል እንዲገነባ ያደርጋል፡፡[4]

የተመድ 75 አመት በሚዘከርበት ወቅት ዋና ጸኃፊው እንዳስታወሱት "ሙስና ወንጀል ኢሞራላዊ (ከግብረገብ ተፃራሪ የሆነ) እና በህዝብ እምነት ላይ የሚፈጸም ከባድ ክህደት ነው፡፡ ያለምንም መዘግየት በጋራ በመሆን ጠንካራ የተጠያቂነት ፣ የግልጽነት እና የሐቀኝነት ስርአት መዘርጋት አለብን" ማለታቸው ይታወሳል።

በትምህር ሴክተሩ የውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ የሐቀኝነት ጉድለት የተለያዩ መልኮችን ይዞ ሊከሰት ይችላል፡፡ ከነዚህም መሃል ለትምህርት የሚሰጥን ገንዘብ ከታሰበለት አላማ ውጭ ማዋል ፣ ለእቃ ግዢ የተመደበ ገንዘብን ለሌላ ጉዳይ ማዋል ፣ ለምዝገባ ጉቦ መጠየቅ፤ግሬድን በግብረ ስጋ ግንኙነት መሸጥ ፣ ሰራተኛን በዝምድና መቅጠር ፣ በጥናትና ምርምር ህትመቶች ላይ የሌላውን የአዕምሮን ንብረት መኮረጅ እና በትምህርትና ምርምር ላይ የሚደረግ የፖለቲካ እና የኮርፖሬሽን ተጽእኖ ይጠቀሳሉ፡፡ ይህም በበኩሉ በልጆችና ወጣቶች የወደፊት የእድገት እድሎች ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ በተጨማሪም ልጆች ከለጋ እድሚያቸው ጀምሮ የሙስናን ተቀባይነት ያለው ማህራዊ ምግባር ነው የሚል እምነትን እንዲያድርባቸው ሊያደርግ ይችላል፡፡[5]

ማህበራዊ ደምቦች(ህግጋት) ታሪክ ፣ ባህል እና እንደየ አውዱ የሚወስኑ (context-specific) ጉዳዮች የሚወልዷቸው በማህበረሰቡ በጋራ የሚጠበቁ ተገቢ ባህርያት ወይም አኗኗር ዘየዎች ስብስብ ናቸው፡፡ ግለሰቦች ማህበራዊ እውቅናን፣ ክብርንና ተቀባይነትን ለማግኘት በማህበረሰቡ ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት ያላቸው አኗኗር ዘዬዎች ወይም ባህርያትን የመከተል እድላቸው ሰፊ ነው፡፡ ግለሰቦች ባሉበት ቡድን የሚገኙ ሌሎች በተደጋጋሚ ሥነ-ምግባር የጎደለውን ድርጊት ፈጽመው በተቀረው የቡድን አባላት አሉታዊ ምላሽ (ውጤት) ሳይከተል ሲቀር እነዚህ ግለሰቦች ያ ተግባር በቡድን ውስጥ ተቀባይነት ያለው ባህሪ (ተግባር) ነው የሚል እምነት ሊያድርባቸው ይችላል፡፡[6] ለዚህ ነው በየትኛውም ማህበረሰብ ውስጥ ሐቀኝነት የማህበረሰባዊ ሕግ አካል ይሆን ዘንድ ከለጋ እድሜ ጀምሮ የሚሰጠው ትምህርት አካል እንዲሆን ያስፈለገው፡፡

## 1.2 ሐቀኝነትን የማስተማር አስፈላጊነት

ተማሪዎች ከለጋ እድሜያቸው ጀምሮ ፍትሃዊነትን ፣ ታማኝነትን ፣ መከባበርን አብሮ መኖርን እና የመረዳት እና ዋጋ የመስጠት አቅማቸውን በማጎልበት እረገድ ትምህርት ወሳኝ ሚናን ይጫወታል፡፡ መምህራን በ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ሐቀኝነትን በሚያስተምሩ ጊዜ ተማሪዎችን ፡-

- እንደ ፍትህ ፣ ርትዕ ፣ ሐቀኝነት ፣ ዴሞክራሲ እና ሰብአዊ መብቶች ያሉ እሴቶችና ጽንሰ ሃሳቦችን እንዲረዱ እንዲሁም ሐቀኝነት የጎደለው ውሳኔ አሰጣጥ ምን እንደሚመስል እንዲለዩ ያስችሏቸዋል፡፡
- ሐቀኝነት ከሌሎች ጋር በሚኖር ግንኙነት ላይ ያለው አወንታዊ ተጽእኖ እንዲሁም ፍትሃዊ እና እኩልነት ለሰፈነባቸው ማህበረሰቦች ያለውን አስተዋጽኦ እንዲረዱ እና ሃላፊነት የሚሰማቸው እንዲሆኑ ያግዛል፡፡
- በውስብስብ ሁኔታዎች ውስጥ በሥነ-ምግባር ላይ የተመሰረተ ውሳኔን ለማሳለፍ የሚያስችን "የሞራል ኮምፓስ" እንዲያዳብሩ እንዲሁም ስለ ማህበረሰባቸው አስተዳደር በጥልቅ የማሰብ ብቃትን ይገነባል፡፡
- ምግባራቸው በሐቀኝነት እንዲመሰረት ያግዛቸዋል፡፡
- ከቤተሰብ ጓደኞችና ከህብረተሰቡ ጋር በመሆን ለማህበረሰባዊ ሐቀኝነት በትጋት እንዲታገሉ (እንዲሟገቱ) ያግዛቸዋል፡፡

1 Organisation for Economic Co-operation and Development, "Public Integrity: A Strategy Against Corruption" (2017).

2 David Malan, "Integrity", in *The A to Z of Corporate Social Responsibility*, Wayne Visser, Dirk Matten, Manfred Pohl and Nick Tolhurst, eds. (Chichester, West Sussex, Wiley, 2010), p.278.

3 United Nations Office on Drugs and Crime (UNODC) Global Resource for Anti-Corruption Education and Youth Empowerment (GRACE), "Knowledge tools for academics and professionals – Module Series on Integrity and Ethics: Module 1 Introduction and Conceptual Framework" (Vienna).

4 ምንም እንኳ በአለም አቀፍ ደረጃ በጋራ ተቀባይነት ያለው የሙስና ትርጓሜ ባይኖርም፣ አብዛኛዉ ሰው" ሙስና የሚለውን ቃል እና ስለ ምንንቱ ጠቅለል ያለ ግንዛቤ አላቸው፡፡ብዙውን ጊዜ ሰወች ቃሉን ከስስት፣ካለመታመን፣ ሚስጥራዊነት እና ወንጀል ጋር ያስተሳስሩታል፡፡ እነዚህ ሁሉ የስነምግባር ጉድለት ምሳሌወች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ሙስና ለአንድ ሰው የግል ጥቅም ሲባል የስልጣን (ወይም በስልጣን ያልአግባብ መጠቀም) ግንኙነትን ያመላክታል፡፡ ለተጨማሪ መረጃ የተመድ ፀረ ሙስና ኮንቬንሽንን እና የ "GRACE teritiary anti-corruption module series"ን ይመልከቱ፡፡

5 United Nations Educational, Scientific and Cultural Organization (UNESCO) and International Institute for Educational Planning, *Corrupt schools, corrupt universities: What can be done?* (Paris, 2007).

6 Henry J. Leir Institute, *Social Norms, Corruption & Fragility* (September 2019).

በመሆኑም ትምህርት ቤቶች እውቀትን ማስጨበጥ ብቻ ሳይሆን ወጣቶች በጎ ሥነ-ምግባር የተላበሰ ባህሪን እንዲያጎለብቱ መሰረት የሚሆኑ እሴቶች ፣ ክህሎት እና አመለካከቶችን እንዲያዳብሩ ለማድርግ አስተዋጽኦዋቸው የጎላ ነው፡፡ እንዲሁም በማህበረሰቡ ውስጥ ስላሉ ሕጋዊና አብረዋቸው ለሚመጡ መብቶች እና ግዴታዎች የጋራ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ ትምህርት ቤቶች የላቀ ሚና አላቸው፡፡

መምህራን በሚያስተምሩት ሥርዓተ ትምህርት (ካሪኩለም) ብቻ ሳይሆን በሚያስመሩበት መንገድ (ፔዳጎጂ) የተማሪዎቻቸውን አመለካከት ይቀርጻሉ፡፡ ምንም እንኳን ከላይ የተጠቀሰው ለሁሉም የትምህርት ዓይነት የሚሰራ ቢሆንም ፣ ይህ “ለሐቀኝነት” ትምህርት በልዩ ሁናቴ የበለጠ ልክ ይሆናል፡፡ መምህራን ተማሪዎቻቸው የራሳቸውን ሐቀኝነት የሚመረምሩበት እና ሌሎችን የሚፈትኑበት የትምህርት ተሞክሮ (experience) እና አካባቢን መፍጠር ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች በራሳቸው ህይዎት ውስጥ የሐቀኝነትን ትርጉም በጥልቀት በመመርመር እና ከማህበረሰባቸው ጋር በሚኖራቸው መስተጋብር ፣ ከእሴቶቻቸው ጋር በወጥነት በሚስማማ መንገድ እንዲንቀሳቀሱ የሚያስችሉ ክህሎትና ሌሎችን እንደራስ የማየት (ርህራሄ / empathy) አቅምን ማጎልበት እንዲሁም ሌሎች ሐቀኝነት በሚጎድላቸው ጊዜ ምላሽ መስጠት ይችላሉ፡፡

በተጨማሪም መምህራን በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ የሚወስኗቸው ውሳኔዎች የሚያስተምሯቸውን እሴቶች የሚያንጸባረቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያሻቸዋል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ተማሪዎች ሐቀኝነትን የመረዳት ፣ የመቀበል (የማክበር) እንዲሁም በራሳቸው አኗኗር ውስጥ የመተግበር እድላቸው ከፍተኛ ይሆናል፡፡ ይህ በተለይም ተማሪዎች ሐቀኝነትንና ፍትህ ሲተገበር የማየት እድሉ በሌለበት አከባቢ ውስጥ የሚኖሩ ሲሆን ወይም ለሐቀኝነትና ፍትህ አርአያ የሚሆን ሰው በማያገኙበት ጊዜ የበለጠ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ እዚህ ላይ መምህራን ተማሪዎች በኑሯቸው የገጠሟቸውን የሐቀኝነት መጓደሎችን የሚያጋሩበትንና ይህም በማህበረሰብ ላይ የሚኖረውን አሉታዊ ተጽእኖ ለመረዳት የሚያስችል ምቹ የሆነ አካባቢን በክፍል ውስጥ መፍጠር ይጠበቅባቸዋል፡፡

መምህራን ተማሪዎቻቸው በአካባቢዎቻቸው እና ማህበረሰባቸው የሚወሰኑ ሐቀኝነት የጎደላቸውን ውሳኔዎች እንዲቃወሙ እንዲሁም ውሳኔውን ለማስቀየር ውሳኔ ሰጭዎች ወይም ሌሎች ባለ ድርሻ አካላት ላይ ግፊት እንዲያደርጉ ሊያበረታቱዋቸው ይችላሉ፡፡ ይሁን እንጂ መምህራን ይህን ሊያደርጉ የሚገባው ሁኔታው የሚፈቅድ ሲሆንና ለተማሪዎች ደህንነት ስጋት የማይኖር ከሆነ ብቻ ነው፡፡

## 1.3 የመምህሩ መምሪያ አላማ

የዚህ መምሪያ አላማ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን ስለ ሐቀኝነት ለማስተማር የሚያስችሉ የክፍል ውስጥ እና ከክፍል ውጭ (የመስክ) መልመጃዎችን ዝርዝር ማቅረብ ነው፡፡

መምህራን ሐቀኝነትን የሁሉም ትምህርቶች አካል እንዲያደርጉትና የሐቀኝነት መልመጃዎችንም በሁሉም የትምህርት አይነቶች እንዲያካትቷቸው በሚያስችል ሁኔታ የቀረበ ነው፡፡ ምንም እንኳን አብዛኛዎቹ መልመጃዎች በስነ ዜጋ እና ማህበረሰብ ትምህርቶች ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቢሆኑም እንደ ስነጥበብ ፣ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ሂሳብ ባሉ ሌሎች የትምህርት አይነቶች ላይ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ መልመጃዎች ተካተዋል፡፡

በተጨማሪም ይህ የስልጠና መምሪያ መምህራን በትምህርት ቤትም ይሁን ከማህበረሰቡ ጋር በሚኖራቸው መስተጋብር ከመደበኛው ካሪኩለም ውጭ ሊጠቀሙባቸው የሚችሏቸውን መልመጃዎች አካቷል፡፡

አስቸጋሪ ወይም ከባድ የሆኑ ውሳኔዎችን ለመወሰን በምንገደድበት ብዙውን ጊዜ ግልጽ እና ቁርጥ ያለ መልስ እንደሌለ ይሰማናል፡፡ ይሁንና ውሳኔው ትክክል (ተገቢ) በሆነ እና ትክክል ባለሆነ ነገር መካከል ያለ ምርጫ መሆኑን ደመነፍሳችን (intuition) ይነግረናል፡፡

መምሪያው መታየት ያለበት ትክክለኛ ስለሆኑ እና ስላልሆኑ ባህሪዎች የምክሮች (የትእዛዛት) ዝርዝር ሳይሆን እንደ ስነምግባራዊ ማመዛዘንን (አስተሳሰብን) ፣ ምክንያታዊ እና ጥልቅ አስተሳሰብን ፣ ራስን በሌሎች ቦታ አድርጎ ማየትን (empathy) እና በጋራ መስራትን የመሳሰሉ ቁልፍ ብቃቶችን ለማዳበር የሚጠቅም መንገድ አመልካች ተደርጎ ነው፡፡

በተጨማሪም በሁሉም ማህበረሰብ ባህሎች የጋራ ተቀባይነት ያላቸውን እንደ ታማኝነት ፣ ፍትሃዊነት እና ተጠያቂነት ያሉ እሴቶችን ማሳደግ አላማው ያደረገ ነው፡፡

## 1.4 ይህ መምሪያ ለማን ተዘጋጀ

ይህ መምሪያ በሚከተሉት አካላት ጥቅም ላይ እንዲውል የታሰበ ነው፡፡

- የሁለተኛ ደረጃ መምህራን እና ሰልጣኝ መምህራን
- ከትምህርት ባለሙያዎች ጋር ሆነው ለተማሪዎች የትምህርት ስልጠና የሚያዘጋጁ የጸረ- ሙስና ኤጀንሲ ባለሞያዎች
- ከወጣቶች ጋር የሚሰሩ የትምህርትና ሌሎች ባለሙያዎች (ለምሳሌ በስፖርት ፣ ህብረተስብ ፣ የሃይማኖትና የወጣት ማህበራት እነዲሁም የማህበራዊና ባህላዊ ስራ ውስጥ ኢ-መደበኛ የትምህርት ስልጠና መደረኮች)

በአጠቃላይ የዚህ መምሪያ ግብ ከወጣቶች ጋር የሚሰሩ መምህራንና ሌሎች የትምህርት ባለሙያዎች በውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ ሊኖር ስለሚገባ ሐቀኝነት ወጣቶችን እንዲያስተምሩ ድጋፍ መስጠት ነው፡፡ ይህም ድጋፍ ተማሪዎች ስለ ሐቀኝነት ያላቸው ግንዛቤ እንዲጨምር ማድረግ ብቻ ሳይሆን ይህ ግንዛቤ በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ በሚያሳዩት ባህሪ እና ወደ ፊት በሚመሩት ህይዎት ማለትም እነደ ነጋዴ ፣ ተጓዥ ፣ ሰራተኛ ፣ ቀጣሪ ፣ በጎ ፈቃደኛ ፣ ወላጅ ፣ የማህበረሰብ አባል ፣ ብሄራዊ እና አለም አቀፋዊ ዜጋ እና መሪ ወ.ዘ.ተ. ላይ አወንታዊ ተጽዕኖ ማሳረፍ ነው፡፡

የዚህ መመሪያ ዋናው ተጠቃሚዎች የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ለሐቀኝነትና ፍትህ በትጋት የሚያበረክቱ ብቁ ወጣት አለም አቀፍ ዜጎችን ለማፍራት እንዲረዳ የተዘጋጀውን ይህን መመሪያ ወላጆች ቢያነቡት ይጠቀማሉ፡፡

ክፍል 2

# መልመጃዎችን ጥቅም ላይ ለማዋል መዘጋጀት



## 2.1 ማህበረሰብን የሚለውጡ ዕውቀቶች ፣ ክህሎቶችና አመለካከቶችን ማዳበር

ይህ መምሪያ ትምህርት ወጣቶች በማህበረሰብ ውስጥ ሐቀኝነትን ለማጎልበት ዝግጁ እንዲሆኑ የሚጫወተውን ሚና የሚያየው በአለም አቀፍ የዜግነት ትምህርት መነጸርነት ነው፡፡ አለም አቀፍ የዜግነት ትምህርት ተማሪዎች የበለጠ ፍትሃዊ ፣ ሰላማዊ ፣ መቻቻል የሰፈነበት ፣ አካታች ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ዘላቂ የሆነ አለም ለመፍጠር በአካባቢያቸውና በአለም አቀፍ ደረጃ እንዲሳተፉ ፣ የነቃ ሚና ኑሯቸው የራሳቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ብቃት መፍጠርን ግቡ ያደረገ ነው፡፡ ይህም ለሰብአዊ መብቶችና መሰረታዊ ነጻነት ያለ ቁርጠኝነትን ይጠይቃል፡፡ አለም አቀፍ የዜግነት ትምህርት መሰረታዊ የለውጥ (ሽግግር) ምንጭ በመሆን ተማሪዎችን መብትና ግዴታዎቻቸውን እውን የሚያደርጉበት እድልና ብቃት አግኝተው ለሙስና ቦታ የሌለው መጻኢ አለምን እንዲገነቡ ማስቻልን ያልማል፡፡

በዩኔስኮ የተዘጋጀው አለም አቀፍ የዜግነት ትምህርት የብቃት ማእቀፍ የተሟላ የትምህርት ተሞክሮን ለመፍጠር ሶስት የተለያዩ ክፍሎች (ጎራዎች) መሸፈንን አላማ ያደረገ ነው፡፡ እነዚህም የእውቀት (cognitive) ፣ የማህበራዊና ስሜት (social and emotional) እና የባህሪ (behavioural) ናቸው፡፡[7]

ምንም እንኳን እነዚህ ሶስት ክፍሎች በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ የተለያዩ ቢሆኑም የተነጣጠሉ የትምህርት ሂደቶችን የሚወክሉ ግን አይደሉም፡፡ እዲያውም ብዙ ጊዜ የሚነባበሩበት ፣ አንዱ ሌላኛውን የሚያጠናክርበትና አንዱ በአንዱ ላይ የሚጨመርበት (የሚገነባበት) ጊዜ አለ፡፡ ጎን ለጎን የሚከሰቱበት ጊዜም አለ፡፡ ለምሳሌ ማህበራዊና ስሜታዊ ትምህርት (የትምህርት አወሳሰድ) በመህበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ተግዳሮቶች በጥልቀት መረዳትና (ማወቅ / እውቀት) በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔን ማሳለፍ (ባህሪያዊ) ይጠይቃል፡፡

ሶስቱንም ክፍሎች (ጎራዎች) ተጠቅሞ ትምህርትን በማቀረብ መምህራን አለም አቀፍ የዜግነት ትምህርት የሚያበረታታውን (የሚጠይቀውን) እውቀት ፣ አመለካከቶች ፣ እሴቶችና ባህሪያት በሰፊው መሸፈን ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ይህ አካሄድ ተማሪዎች ንቁና ተሳታፊ ዜጎች ለመሆን የሚያስፈልጋቸውን ክህሎት የሚያስጨብጧቸውን አራቱን ትምህርት አምዶች ለመሸፈን ያስችላል፡፡ እነዚህም አምዶች፡- ማወቅን መማር ፣ መስራትን መማር ፣ መሆንን መማርና አብሮ መኖርን መማር ናቸው፡፡

## 2.2 ተጠባቂ የትምህርት ውጤቶችን ማስቀመጥ

መምህራን ሐቀኝነትን በማስተማር ሊያሳኳቸው የሚፈልጓቸውን ውጤቶች መለየት ይገባቸዋል፡፡ ይህን በሚያደርጉበት ጊዜ ማስታወስ የሚገባቸው በተማሪዎቻቸው የቀን ተቀን ባህሪ ውስጥ ሐቀኝነትን ለማስረጽ የተማሪዎቻቸው እውቀትና እሴቶች እንዲሁም ክህሎቶችን ማጎልበት እንዳለባቸው ነው፡፡

በመምሪያው ውስጥ የተቀመጡት መልመጃዎች በሚከተሉት የሐቀኝነት ተጠባቂ ውጤቶች ዙሪያ ተደራጅተዋል፡፡

| የእውቀት (COGNITIVE) |
|---|
| ተማሪዎች ሐቀኝነት እና ተያያዥ ጽንሰ ሃሳቦችን በጥልቀት ይረዳሉ፡፡ |
| ተማሪዎች ሐቀኝነት እና ተያያዥ ጽንሰ ሃሳቦችን በጥልቀት ይረዳሉ፡፡ |

| ማህበራዊ እና ስሜታዊ |
|---|
| ተማሪዎች የሐቀኝነትን ዋና (ቁልፍ) እሴትነት ይቀበላሉ፡፡ |
| ተማሪዎች የሰብአዊነት ስሜትን ይጋራሉ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች ሐቀኛ የመሆን የሃላፊነት ስሜትን ይጋራሉ፡፡ |

| ባህሪያዊ |
|---|
| ተማሪዎች የሰብአዊነት ስሜትን ይጋራሉ፡፡ እንዲሁም ተማሪዎች ሐቀኛ የመሆን የሃላፊነት ስሜትን ይጋራሉ፡፡ |
| ተማሪዎች ሥነ-ምግባርን የተላበሰ ባህሪ ባለቤት በመሆን ሕይዎታቸውን በሐቀኝነት ይመራሉ፡፡ |
| ተማሪዎች ሐቀኝነትን ለማጠናከር በጋራ ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡ |

7 Organisation for Economic Co-operation and Development, "Public Integrity: A Strategy Against Corruption" (2017).

## 2.3 ሐቀኝነትን ለማስተማር አመቺ አከባቢዎችን መፍጠር

ሐቀኝነትን ለማስተማር አመች ሁኔታ ተፈጠረ የምንለው የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተሮች እና ሌሎች በአስተዳደር ውስጥ ያሉ ሰራተኞች እንዲሁም መምህራን ሐቀኝነትን በንቃትና በትጋት ሲያበረታቱ እነዲሁም በራሳቸው ባህሪ ይህን ሲተገብሩ ነው፡፡ ይህን ዓይነት አከባቢ ለመፍጠር የሚከተሉትን ማድርግ ይቻላል፡

### የሐቀኝነት አርአያ (ተምሳሌት) መሆን

ከሁሉም በፊት የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተሮች ፣ መምህራን እና ሌሎች ሰራተኞች የሐቀኝነት ተምሳሌት መሆን አለባቸው፡፡ ይህ ማለትም ተግባሮቻቸውን ከሚያስተምሯቸው እና ከሚጠብቋቸው እሴቶች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡ ስለ እሴቶች በሚገለጽበት ጊዜ ት/ቤቶችም ሆኑ መምህራን እንደ ታማኝነት ፣ ፍትህና ርትዕ የመሰሉ አለም አቀፍ እና በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ስላላቸው እሴቶች መግለጽ አለባቸው። የት/ቤቶች ህግና ደንቦች በሰራተኞችና ተማሪዎች ላይ ያላቸው አፈጻጸም ፍትሃዊና ወጥነት (consistent) ያለው መሆን አለበት፡፡ ህግና ደንቦችን መጣስ የሚያስከትለው ግልጽ እና ተገቢ የሆነ ቅጣት መኖር አለበት፡፡ ይህም ቅጣት ተገቢ ፣ ተመጣጣኝ እና የቅጣቱም አላማ እና ውጤቱ አወንታዊ እንዲሆን ሊደረግ ይገባል፡፡

ዳይሬክተሮችና መምህራን እንደ በጀት እና ወጭዎች የመሰሉ የት/ቤቱን መረጃዎች (ዳታ) በግልጽ በመለጠፍ (በማሳየት) እንዲሁም በተማሪዎች ካውንስልና ሌሎች አካላት ውስጥ ያለ ተሳትፎ እንዲጠናከር በማድረግ በት/ቤቱ ውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ ግልጸኝነት እና ተጠያቂነት እንዲኖሩበት ማድረግ ይችላሉ፡፡ይህንንም በማድረግ ት/ቤቶች የሐቀኝነት ባህል የሰፈነባቸው እና ሐቀኝነት የእያንዳንዱ ውሳኔ አሰጣጥ መሰረት የሆነባቸውን ደሴቶችን መፍጠር ይችላሉ፡፡

መምህራን የየእለት ባህሪያቸው ለተማሪዎቻቸው ጠቃሚ ተምሳሌትነት ስላለው በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ የሚወስኗቸው ውሳኔዎች የሐቀኝነት ምሳሌ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያሻቸዋል፡፡ መምህራን ተማሪዎቻቸው ሃላፊነት የሚሰማቸው እንዲሆኑና ስህተቶች ሲከሰቱ በግልጽ እንዲያምኑ በማበረታታት በክፍል ውስጥ የመተማመንና ግልጽነት አከባቢ እንዲሰፍን ለያድርጉ ይገባል፡ ፡አጽንኦት ሊሰጠው የሚገባው አሉታዊ ባህሪን ከማስወገድ የበለጠ ሰላማዊ መስተጋብርን ለማጎልበት ጠቃሚ የሆኑንና ለማህበረሰብ ግንባታ እና አብሮነት አስተዋጽኦ ያላቸው አዎንታዊ ባህሪያትንና ተግባራትን ማበረታታትና ማስረጽ መሆን ይኖርበታል፡፡

### ሐቀኝነትን ጥንቃቄ በሚያሻ አውድ ስለማስተማር

ከክፍል ውጭ ባለው አከባቢ የሐቀኝነት ጉድለት ባለበት ሁኔታ ውስጥ መምህራን ይህ ጉድለት በእያንዳንዱ ቤተሰብ ፣ በማህበረሰብ ፣ እንዲሁም በከፍተኛ የመንግስት እርከን ውስጥ የሚገኙ ግለሰቦች ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት ሊያስረዱ ይገባል፡፡ ለምሳሌ ለመንገድ ፣ ክሊኒክ ወይንም ት/ቤት ስራ የተመደበን ገንዘብ መስረቅ የሚያስከትለው የአጭር እና የረጅም ጊዜ ውጤትን ማብራራት ይችላሉ፡፡ የማህበረሰቡን የወደፊት መሪዎች ጠንካራ የሥነ-ምግባር ኮምፓስ እንዲኖራቸው በማስቻል እና በማህበረሰባቸው ውስጥ የሐቀኝነት ታጋዮች (ደጋፊዎች) እንዲሆኑ በማብቃት ርገድ ትምህርት የማህበራዊ ደንቦችን በመቅረጽ (መገንባት) ረገድ ስላለው ጠቃሚ ሚናም ማስረዳት ይችላሉ፡፡ ይህን ሲያደርጉ ግን ተማሪዎቻቸውን ሙስና በተስፋፋበት አከባቢ ውስጥ የሚደረጉ ተግባራት ሊያስከትሉ ስለሚችሉት አደጋ ግንዛቤ እነዲኖራቸው ሊያግዟቸው ይገባል፡፡ (የሚከተለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ)

> *ሰንጠረዥ 1*
> *ተማሪዎች ምን ያህል ማድረግ ይችላሉ?*
>
> *ሐቀኝነት የጎደላቸው ተግባራት ለማስቆም የምንፈጽማቸው ተግባራት ሊያስከትሏቸው የሚችሉ ከፍ ያሉ አደጋዎች ሊኖሩም ለይኖሩም ይችላል፡፡ ይህ የሚወሰነው ስለጉዳዩ ያለን ግንዛቤ መጠን ፣ ባለን ቁርጠኝነት መጠን እና ሊከተል ስለሚችለው አደጋ መጠን ያለን ግንዛቤ ነው፡፡*
>
> *በተለይም ለወጣቶች የአደጋውን መጠን በትክክል መገመት ከባድ ነው፡፡ ከአደጋው መጠን ምንም ይሁን ተማሪዎች ማድረግ ያለባቸውን ነገር ያለማድረጋቸው እንደ ጉድለት (ውድቀት) ይቆጠራል፡፡ ይሁንና ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትልባቸው በሚችል ሁኔታ እርምጃ እንዲወስዱ ማበረታታትም ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡*

በዚህም የተነሳ መምህሩ ተማሪዎቹ ሊደርስባቸው ስለሚችለው የአደጋ መጠንና አይነትን በመለካት ረገድ የሚኖረው የማገዝ ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ መምህራን ማህበረሰባቸውንና በውስጡ ያለውን የስልጣንና ሃይል መዋቅር ያውቃሉ፡ ፡ ተማሪዎቻቸው ሊከተሉት የሚችለውን አደጋ እንዲለዩ እና ተገቢና በደንብ የታሰበባቸው ምላሾችን እንዲያዘጋጁ በማገዝ መምህራን ተማሪዎቻቸው ውጤታማ ዜጎች እንዲሆኑ የሚያስችሏቸውን ጠቃሚና አስፈላጊ የህይዎት ክህሎቶችን ያበረክታሉ፡፡ ይህንን በማድረግም ተማሪዎቻቸው ለማህበረሰባቸው መሻሻል አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ያግዟቸዋል፡፡

ስለ ሐቀኝነት በሚያስተምሩበት ወቅት መምህራን የማያስተውሏቸው (የማይታወቋቸው) የተሳሳቱ አመለካከቶች (biases) ሊኖራቸው ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋቸዋል፡፡ እነዚህ የተሳሳቱ አመለካከቶች ከጾታ ፣ ከዘር እና ሌሎች ጉዳዮች ጋር ሊገናኙ ይችላሉ፡፡ መምህራን ትህትናን በተግባር ማሳየት እና የራሳቸውን የውስጣዊ ሐቀኝነት ተግዳሮቶች ግልጽ ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ በተጨማሪም መምህራን በትምህርታቸው ውስጥ የሐቀኝነት ጉድለት እና ሙስና በማህበረሰብ ውስጥ ያሉ የእኩልነት እጦቶችን እንደሚያባብሱ በጉልህ ማሳየት አለባቸው፡፡ (ለምሳሌ የሴቶችን እና ሌሎች የተበደሉ (የተጎዱ) የማህበረሰብ ክፍሎች በተመለከተ ሰንጠረዥ 2ትን ይመልከቱ)

### ሰንጠረዥ 2 ሴቶች ለምን ከፍተኛ ጉዳት (በደል) ይደርስባቸዋል?

ርሙስና በሴቶች መሰረታዊ መብቶች በተለይም የትምህርት ፣ የጤና እና የፖለቲካ መብታቸው ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል፡፡ እንዲሁም በማህበረሰብ ውስጥ የጾታ እኩልነት ያለመኖርን እንዲከፋ ያደርጋል፡፡

በብዙ ማህበረሰቦች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች አንጻር ከፍ ያለ ድህነት ውስጥ በመገኘታቸው ምክንያት እንደ ጤና ፣ የንጽህና አጠባበቅ እና ትምህርት የመሰሉ የህዝብ መሰረታዊ አገልግሎቶችን የበለጠ ጥገኛ ናቸው፡፡ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሴቶች የህዝብ (መንግስት) መሰረታዊ አገልግሎቶች የበለጠ ጥገኛ መሆናቸው ለእነዚህ አገልግሎቶች ጉቦ የመክፈል እድላቸው ከፍ ያለ ያደርገዋል፡፡

ብዙውን ጊዜ ሴቶች ወንዶች ከሚከፍሉት ጉቦ የበለጠ ይከፍላሉ፡፡ ምክንያቱ ጉቦ ጠያቂው ሴቶችን በመጠየቁ የሚደርስበት ችግር (ቅጣት) ባለመኖሩ ብቻ ሳይሆን በጉቦ መልክ የሚወስዱት ገንዘብ ከገቢያቸው ትልቁን መጠን የሚሸፍን በመሆኑ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜም ጉቦ የሚጠየቀው ነጻ ለሆኑ አገልግሎቶች ሲሆን ይህም ለህወይት አደጋ ስጋት የሆኑ የወሊድ መወሳሰቦች ጊዜም ሊከሰት ይችላል፡፡ ሴቶች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለማግኘት እድል ካጡ ጉቦ የሚጠይቁ አገልግሎት ሰጭዎችን ለመቃዎም ወይም ሌሎችን በሃላፊነት ለመጠየቅ ያላቸውን አቅም በእጅጉ ይቀንሳል፡፡ በተለይ ይህ የሚሆነው ከመማር ይልቅ የቤት ውስጥ ስራ እንዲሰሩ በሚያደርጉ ወይም የማንበብ እና መጻፍ ክህሎቶችን ለማዳበር በቂ የትምህርት ጊዜ በማይፈቅድ ማህበረሰብ ውስጥ ነው፡፡

በተጨማሪም ሙስና የሴቶችን ሲቪል እና ፖለቲካዊ መብቶችን ይሸረሽራል፡፡ ለምሳሌ በብዙ አገሮች ሴቶች የንብረት ባለቤትነት እና ውርስን በተመለከተ ከወንዶች እኩል መብት የላቸውም፡ ፡ መብታቸውን ለማክበር ፍ/ቤት በሚቀርቡ ጊዜ ሚዛናዊ አገልግሎት አያገኙም፡፡ በተጨማሪም የምርጫ ስርአቶች ሚዛናዊነት ሲጎድላቸው በተለይም የእጩዎች ምርጫ ወደ ወንዶች ያደላ ሲሆን ሴቶች እጩ መሆንም ሆነ ለመመረጥ ከባድ ይሆንባቸዋል፡፡ የሙስና ተጽእኖ ከፉ የሚሆነው ለአገልግሎቱ የሚጠይቁት ክፍያ ወሲብ ሲሆን ነው፡፡ ይህ ተግባር ወሲባዊ ጉቦ (sexual extortion) ይባላል፡፡ ወሲባዊ ጉቦ ብዙ አይነት የወሲብ ጥቃቶችን ሊጠቀልል ሲችል ከወሲብ ትንኮሳ እስከ አስገዳጅ ወሲብ ያሉትን ሁሉ ይይዛል፡፡ ሴቶች ብዙውን ጊዜ ለወሲባዊ ጉቦ የተጋለጡ ናቸው፡፡ ይህ አይነት ሙስና አስከፊ የሴቶች የዜግነት መብት ጥሰት ሲሆን ሰብአዊ ክብራቸውን የሚቀማና ጤናቸውን አደጋ ላይ የሚጥል ነው፡፡

“ወሲባዊ ሙስና ወይም ጉቦ” በእንግሊዝኛው “sextorition”በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውል የተደረገው በአለም የሴት ዳኞች ማህበር (International Association of Women Judges) ሲሆን የታለመው ወሲብን በግዴታ ለማግኘት ሲባል የሚደረግ ስልጣንን ያለ አግባብ መጠቀምን እንዲሸፍን ነው፡፡ “sextorition” በገንዘብ ፋንታ ወሲብ በጉቦነት ጥቅም ላይ የሚውልበት ማንኛውም አይነት ሙስና ይጠቀልላል፡፡ ይሁንና ይህ ቃል በአንዳንድ የአሜሪካ ግዛቶች ሕግ የተለየ ትርጉም አለው፡፡ ለምሳሌ በፔንሲልቬኒያ አንድ ሰው ሌላን ሰው የግል ጉዳይን ወይም ሚስጥርን አወጣለሁ በሚል ማስፈራሪያ ወሲብ ነክ ፎቶ እንዲልኩ ማስገደድን ይገልጻል፡፡ ዩናይትድ ኪንግደም (UK) የብሄራዊ ወንጀል ኤጀንሲ ይህንኑ ቃል አንድን ሰው በበይነ መረብ አማካኝነት የሀሰት ማንነትን በመጠቀም ከሌላ ሰው ጋር ጓደኝነት ከመሰረተ በኋላ በ “ዌብ ካም ” በኩል የወሲብ ተግባራትን እንዲፈጸሙ ማሳመንን ይገልጻል፡፡ UNODC ከ “sextorition” ይልቅ ወሲባዊ ሙስና የሚለውን ቃል መጠቀምን ይመርጣል፡፡

ምንጭ: Based on UNODC, The Time is Now: Addressing the Gender Dimensions of Corruption (Vienna 2020) (see chapter 2) and United Nations Development Programme and United Nations Development Fund for Women, Corruption, Accountability and Gender: Understanding the Connections” (New York, 2010) (see chapter 1).

## የባህልና የማህበራዊ ደንቦችን ሚና መረዳት

ሐቀኝነትን የተመለከተ ትምህርት ሲሰጥ ሊታሰብ የሚገባው ሌላው ነገር ባህል እና የማህበረሰብ ህግጋት (ደንቦች) የእሴቶች ፣ እምነቶች እና ልምዶች ላይ ያላቸው ተጽዕኖ ነው፡፡ ትምህርት ሁሌም የሚከናወነው ለትምህርቱ ትርጉም በሚሰጡ የማህበራዊና ባህላዊ አውድ ነው፡፡ ያለ በቂ የባህል ወይም ቋንቋ መነሻ ወይም ማጣቀሻ መማር ስለማይቻል የባህል እሴቶች የትምህርትና የመማር መሰረቶች ናቸው፡፡ ቋንቋና ባህል የትምህርትና የመማር መሰረቶች ናቸው፡፡ ብዙን ጊዜ ትምህርት አግላይ እና ከተማሪ የህይዎት ተሞክሮ እና የባህል አውድ የተፈታ ይሆንና ለመማር ፈጽሞ የማይቻል ይሆናል፡፡ ሐቀኝነትን በምናስተምር ጊዜ ለባህል አውድ የተለዩ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ምክንያቱም ስለ ሐቀኝነት መማር ውጤታማ የሚሆነው እንደ ቤተሰብ ፣ አንጋፋ ሰዎችና የማህበረሰብ መሪዎች የመሳሰሉ ልዩ ልዩ የህብረተሰብ አባላት ሐቀኝነትን እንደ አንድ ዋና የባህል አካል አድርገው ሲያዩት ነው፡፡

ቀጥሎ ያለው ሰንጠረዥ መምህራን ተማሪዎችቻቸው የባህልን ሚና እና በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ ባህል እንዴት በሐቀኝነት ላይ አወንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽእኖ ማሳረፍ እንደሚችል ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲያገኙ ለመረዳት የሚያስችሏቸውን ነጥቦች ይዘረዝራል፡፡

### ሰንጠረዥ 3
### የባህል ሚና እና በሐቀኝነት ላይ ያለውን ተጽእኖ መገንዘብ

ባህል ሰፊ ጽንሰ ሃሳብ እና በእሴቶች ፣ እምነቶች እና ልማዶች ላይ ተጽእኖ ያላቸው የአከባቢ ፣ የክልል እና የአገር አቀፍ አውዶች አካል ነው፡፡

ባህል ተለዋዋጭ ነው፡፡ ይህ ማለት ያለበት አከባቢ በሚለወጥበት ጊዜ ተከትሎ ቀስ በቀስ ይቀየራል፡፡ በአንድ በኩል ግልጸኝነት ፣ ተጠያቂነት ፣ ታማኝነት እና ፍትሃዊነት የሚከበሩበት ባህላዊና ማህበራዊ ሁኔታን ተከትሎ ሐቀኝነትን የሚያከብር እና የሚያበረታታ ባህል ይፈጠራል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እርስ በእርስ የሚጣረሱ ” ሕግጋት ” በአንድ ማበረሰብ ውስጥ ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ የባህልን (የልማድን) ሕግጋት በመንግስት ከወጡ ሕግጋት ጋር ሲጋጩ ግለሰቦች ሁለት የሚጣረሱ የማህበረሰባዊ ግዴታዎች ጋር ይጋፈጣሉ፡፡ ይህም ሐቀኝነትና የህግ የበላይነትን እንዲዳከሙ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ስለዚህ ሐቀኝነትና ባህል በልዩ ልዩ መንገድ የሚጠላለፉ ሲሆን ይህም ሐቀኝነትና ተያያዥ እሴቶችን የሚያጎለብቱ ወይም የሚያዳክሙ ልማዶችን ሊወልድ ይችላል፡፡ መምህራን ተማሪዎቻቸው የሐቀኝነት ተያያዥ እሴቶች ጽነሰ ሃሳብን እንዲሁም አብረው የሚሄዱ ወይም የሚጻረሩ ባህላዊ እምነቶችንና ልምዶችን ትክክለኛ ግንዛቤ እንዲይዙ የሚያግዛቸው የጠለቀ ትንታኔን ሊያሳልጡ (ሊመሩ) ይችላሉ፡፡

በተጨማሪም መምህራን እና ዳይሬክተሮች የአከባቢው ነዋሪዎችን በመጋበዝ የሰብአዊ መብቶችን የሚያከብሩ ነገር ግን በተመሳሳይ ጊዜ ባህልና ማንነትን የሚያከብሩ አወንታዊ ተዋናዮች ለመሆን መምህራን ፣ ተማሪዎች ፣ ወላጆች እና አጠቃላይ ማህበረሰብ ምን ማድረግ ይችላል በሚለው ጥያቄ ላይ በጥልቅ እንዲወያዩ ማድረግ ይችላል፡፡

መምህራን ሰዎች የጋራ ሰብአዊ ወገንተኝነት (የእኔነት) ስሜት እንዲሰማቸው የሚያደርጉ ፍትሃዊና አካታች ማህበረሰቦችን ለመፍጠር አስፈላጊ የሆኑ እንደ ፍትህ፣ ሚዛናዊነት ፣ ታማኝነት፣ የሃላፊነት ስሜት ፣ አክብሮት ፣ ትብብር ፣ ትህትና ፣ የሌሎችን ሁኔታ ለመረዳ መጣር (empathy) ፣ ርህራሄ ፣ ድፍረት ፣ ክብር እና መልካምነት ያሉ እሴቶችን በንቃትና ትጋት ማበረታታት እና ማስተዋወቅ ይችላል፡፡

## ሐቀኝነትን በተግባር ማስተማር

ስለ ሐቀኝነት መማር ማለት ስለ እውቀት ብቻ ሳይሆን ስለ መተግበርም ጭምር ነው፡፡ መምህራን በተወሰኑ ሁኔታዎች ውስጥ "ተገቢውን /ትክክለኛውን ነገር ማድረግ" ስላለው ጠቀሜታ ሊገልጽ እና በክፍል ውስጥ እና በጨዋታና ስፖርት ጊዜ የተማሪዎች መስተጋብር የተመለከቱ አወንታዊ ሕግጋት ላይ መወያየት ይችላሉ፡፡ መምህራንና ተማሪዎች በገሃዱ አለም የሚኖራቸውን ምላሽ (ውሳኔ) ለመፈተን ብሎም የራሳቸውን እሴት በጥልቀት ለመመርመር እንዲችሉ የሥነ-ምግባር (ሞራል) አጣብቂኝ (dilemma) ወይም የሞራል ፈተና ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ እነዚህ የሥነ-ምግባር አጣብቂኝ (ሞራል ፈተናዎች) ተማሪዎች ራሳቸው እዛው ሁኔታ ውስጥ እንዲያዩ እንዲችሉ በተቻለ አቅም ለእውነትነት የቀረቡ መሆን አለባቸው፡፡ በተጨማሪም የትምህርት ቤት አመራሮች እና መምህራን ተማሪዎቻቸው ድምጻቸውን ከፍ እንዲያደርጉና የራሳቸውን የሞራል አጣብቂኝ (ፈተና) እና ተሞክሮዎቻቸውን እንዲያጋሩ ማበረታታት አለባቸው፡ ፡ ይህም በክፍል ውስጥ መተማመን እንዲሰፍን እንዲሁም ተማሪዎች ሙስና ጋር የሚጋፈጡበት ሁኔታ ሲያጋጥማቸው በአግባቡ መያዝ የሚያስችል ብቃትን ይፈጥርላቸዋል። የተማሪዎች የአስተዳደር አካላት እና የትምህርት ቤት ካውንስል (ምክር ቤት) ተማሪዎች በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚሳተፉባቸው እድሎችን በመፍጠር በውሳኔ አሰጣጥ ወቅት ግልጸኝነት ስላለው ዋጋ የተግባር ተሞክሮ ይማራሉ፡፡ ይህም በበኩሉ በትምህርት ማህበረሰቡ ውስጥ ከፍ ያለ ሐቀኝነትና ተጠያቂነት ይፈጥራል፡፡ አወንታዊ የተማሪዎችን ማንነት ፣ ማሳደግ ፣ የሰላም ግንባታና የግጭት አፈታት ክህሎቶችን ማስተማር እንዲሁም በትምህርት ቤቶች ደህንነት ላይ ማተኮር መተማመን ፣ ተጠያቂነት እና ሐቀኝነትን ይገነባል፡፡ መምህራን ተማሪዎቻቸው ተግባራቸውን በሐቀኝነት ሲያከናውኑ ወይም ሀቀኛ ባህሪን በሚያሳዩ ጊዜ እውቅና ሊሰጧቸውና ይህንንም ባህሪ በምስጋና ሊያበረታቱ ይገባል፡፡ እንዲሁም ሌሎች ተማሪዎች ተመሳሳዩን እንዲያደርጉ ሊያበረታቷቸው ይገባል፡፡ በተጨማሪም የሐቀኝነት የተማሪዎች ምዘና ለተማሪዎች እንዲሰጥ ማድረግ ይቻላል፡፡ ምንምእንኳን ተማሪዎች ስለሐቀኝነት የተማሩትን መመዘን ቀላል ባይሆንም ሐቀኝነት የተማሪዎች የምዘና ማእቀፍ አካል ማድረግ ፣ እንዲሁም መምህራን በትምህርት ቤቱ የእለት ተእለት ሕይወት ውስጥ ሐቀኝነት ስላለው ጥቅም የሚያሳዩበት መንገድ መሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ እንደ ኩረጃ ፣ ዘረኝነት እና ጾታን መሰረት ያደረገ የተሳሳተ አመለካከት ያሉ ኢ- ስነምግባራዊ ድርጊቶችን እርምጃ የሚገልጹበት እድልን የሚሰጥ የምዘና መንገድ መፍጠር ይቻላል፡፡

## አሳታፊ የትምህርት ዘዴዎችን መጠቀም

ተማሪዎች ገንቢ የሆነ ግብአት እንዲሰጡ እና እርስ በእርስ እንዲከባበሩ እድል ሲሰጣቸው ተሳትፏቸውን እና የትምህርት ጊዜ ተሞክሯቸው ጠንካራ እንዲሆን ያግዛል፡፡ ተማሪዎች አንድን መልመጃ በጋራ በሚሰሩበት ጊዜ የመፍትሄ ሃሳቦችን የመለየት ፣ እነዚህን ሃሳቦች የመፈተሽ እና እነዚህም ሃሳቦች በሌሎች የመገምገም (የመፈተን) እድልን መፍጠር የሚያስችል ሲሆን ይህን በሚያደርጉበት ወቅት በጥልቀት የማሰላሰል ችግርን የመፍታት እና በትብብር የመስራት ክፍሎችን ያዳብራል፡፡ በእውነተኛ ህይወት ላይ የተመሰረቱ የሞራል አጣብቂኝ (ethical dilemma) መልመጃዎችን በመጠቀም የራሳቸውን ሐቀኝነት በሌሎች እንዲገመግም ሲያደርጉ እነሱም የሌሎችን ሐቀኝነት መመርመር ይችላሉ፡፡ በዚህም መንገድ እነዚህ የማስተማር ዘዴዎች ተማሪን ያማከለ አቀራረብን ይከተላሉ፡፡ በመሆኑም መምህራን የራሳቸውን ሃሳብ ከማቅብ ተቆጥበው ተማሪዎች በቂ ጊዜ ኖሯቸው በተደጋጋሚ ሙከራ መፍትሄ እንዲያገኙ እድሉን መስጠት አለባቸው፡፡

መምህራን ተማሪዎቻቸው በንቃት የሚሳተፉባቸው የትምህርት አሰጣጦችና ተግባራዊ መልመጃዎች እንዲጠቀሙ የሚያስችሉ የተለያዩ አሳታፊ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴዎች ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ በአብዛሃኛዎቹ መልመጃዎች እንደ የጥንድ ስራዎች ያሉ አሳታፊ መንገዶች (group work) ተመራጭ ናቸው፡፡ ምክንያቱም "ሂደቱ" (journey) ለችግሩ መፍትሄ እኩል ጠቀሜታ አለውና ነው፡፡ የትምህርት ቤት አመራር ላይ እንዲየሚና ጨዋታን (role play) እንዲሁም ልዩ ልዩ የፈጠራ ፣ የጥበብ ስራዎች (ስነጥበብና ኪነ -ጥበብ) ውስጥ መሳተፍ የተለያዩ አመለካከቶችን በተሻለ እንዲገነዘቡ ያግዛል፡፡ የሚና ጨዋታ (role play) ተማሪዎች በሁኔታዎች ውስጥ የተለያዩ እይታዎች ተሞክሮ እንዲኖራቸው ያግዛቸዋል (ለምሳሌ እንደ

### ሰንጠረዥ 4
### የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች ግብአቶች ከ "አለምአቀፋዊ ግብአት ለጸረ-ሙስና ትምህርት እና ወጣቶችን ማብቃት" የተገኘ (the Global Resource for Anti -Corruption Education and Youth Empowerment- GRACE)

ቪዲዮዎች የመምህሩ መምሪያዎች

- በክፍል ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ሙስናን ወንጀልንና ሌሎችን የሕግ የበላይነትን የሚመለከቱ ጉዳዮች የሚዳስሱ እና ምክንያታዊ አስተሳሰቦች እንዲሁም የሚዲያ ግንዛቤን የሚያዳብሩ ተከታታይ የካርቱን ፊልሞች እያንዳንዱ ፊልም ከሁለት ደቂቃ ያነሰ ርዝማኔ ያለው ፣ ቀላል ጭብጥ የያዘ ንግግር የሌለው እና አብሮት የሚሄድ የትምህርት እቅዶችና መልመጃዎችን የሚጠቁም የትምህርት መምሪያን ይይዛል፡፡
- የቪዲዮው ርዕሰ ጉዳዮች
  - ጸረ- ሙስና
  - የተደራጁ ወንጀሎች
  - የሰዎች ዝውውር
  - የጦር መሳሪያ ዝውውር
  - ሽብርተኝነት እና አውዳሚ ጽንፈኝነት

ጨዋታዎች

- የህግ የበላይነትን ሙስናን የተመለከቱ ርዕሰ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ኤሌክትሮኒክስ ያልሆኑ ጨዋታዎች እነዚህም ጨዋታዎች ወጣቶች የሥነ-ምግባር አጣብቂኝ (dilemma) ሲገጥማቸው በሐቀኝነት የተመራ ውሳኔ ላይ መድረስ እንዲያስችሏቸው እና የሙስናን ልዩ ልዩ መግለጫዎች (መልኮች) እንዲገነዘቡ አቅም እንዲፈጥርላቸው ታስበው የተዘጋጁ ናቸው፡፡
- ጨዋታዎቹ የሚከተሉትን ነጥቦች ይጨምራሉ
  - ለሐቀኝነት መጫወት - እንስሳትና መሰላሎች መሰል ጨዋታ (snakes and ladders – style) ይህም ጨዋታ የተጫዋቾች ቡድኖች የሐቀኝነት ጽንሰ ሃሳብን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመመለስ እና ሌሎች ተግባራትን በመፈጸም የቦርዱ ጫፍ (መጨረሻ) ላይ ለመድረስ የሚወዳደሩበት ጨዋታ ነው፡፡
  - ከጊዜ ጋር እሽቅድድም(Running out of time) - ተጨዋቾች በማህበረሰብ ውስጥ ልዩ ልዩ ሚናን ይዘው "ከወረርሽኝ " (infection)ጋር የሚፋጠጡበት ሲሆን ይህም ወረርሽኝ በፍጥነት የሚስፋፋ እና ተጨዋቾችን የሚያጠቃ ችግር ነው፡፡ ተጨዋቾቹ ችግሩ በቁጥጥር ስር እስኪውል ወይም ከቁጥጥር ውጭ ሆኖ እስኪሸነፉ ድረስ በትብብርና በስልት የሚሰሩበት ነው፡፡
  - "ፐርፓዚየም" የፍትህ ተገዳዳሪዎች (Purposyum- Challengers of justice) - የፍትህ ተግዳሮቶችን በህብረት ለመፍታት የሚያስችል እቅድን ማቀድና ስልታዊ ትብብርን የሚያበረታታ የትብብር ጨዋታ ነው፡፡ ከተግዳሮቶቹ መካከል አውዳሚ ፣ ጽንፈኝነት ፣ ዘር ማጥፋት ፣ሰፊ ሃሰተኛ ዜና ፣ ያለተገደበ ጦር መሳሪያ ዝውውርና የአለም የሙቀት መጨመር ይገኙበታል፡፡
  - "ላበሪንት ዩአ" (Labyrinth) - ተሳታፊዎች የተለያዩ አማራጭ ያሏቸው ውስብስብ መንገዶችን አልፈው የጀግና ክብር የሚያገኙበት ጨዋታ ሲሆን አንደኛው አማራጭ ወደ አውዳሚ ጽንፈኝነት እና አክራሪነት መንገድ ሲመራ ሌላኛው ወደ መቻቻልና ልዩነትን (Diversity) የሚወስድ ነው፡፡ ተጨዋቾች የጅምላ ፍርጃን (stereotype) በመመርመር ፣ ፕሮፖጋንዳን በመለየት የበይነ- መረብ መረጃዎችን (መልእክቶችን) በመገምገምና ሁኔታዎችን በመተንተን በጥልቀት የማሰብ ክህሎቶቻቸውንና ለአሳሳች መረጃዎች ያለመበገር አቅማቸውን ያጎለብታል፡፡
  - "ሳይበር ስትራይክ " (Cyberstrike) - ተጫዋቾች የበይነመረብ ወንጀልን ለመከላከል በትብብር የጋራ ስልት ይደግፋሉ፡፡
  - ኢንሮዳዶስ (Enrodados) - የሰዎች ዝውውርን በተመለከተ ግንዛቤን ለመፍጠር የሚውልና ትረካ ላይ ያተኮረ መስተጋብራዊ የካርድና ሴራ ጨዋታ ነው፡፡

ተጨማሪ ግብአቶችን ከ www.unesco.org እና grace.unodc.org ዌብ ሳይቶች ያገኛሉ፡፡:
https://grace.unodc.org/grace/en/secondary/index.html

የተጎጂ ሚና ፣ የወንጀለኛ ሚና ፣ የታዛቢ ሚና ወ.ዘ.ተ ሊጫወቱ ይችላሉ): : ይህም የሌሎችን ሁኔታ የመረዳት አቅማቸውን እና የማህበራዊና የስሜት ክህሎቶቻቸውን ለማሳደግ እጅግ ወሳኝ ነው::

በዚህም መምሪያ ለተጠቀሱት መልመጃዎች መምህራን ከወረቀት የትምህርት ግብአቶች በተጨማሪም መምህራን ተማሪዎችን ለማሳተፍ እንደ የሰሌዳ ጨዋታዎች (board games) የኢንተርኔት የኦንላይን ጨዋታዎች ፣ ቪዲዮዎች እና የሞባይል መተግበሪያዎች የመሳሰሉትን መሳሪያዎች (tools) እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ::

የ GRACE ኢኒሺየቲቭ (initiative) አካል ተደርገው ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በ UNESCO የተዘጋጁ ግብአቶች በሰንጠረዥ 4 ውስጥ ተካተዋል:: አሳታፊ የትምህርት ዘዴዎች የመምህራን ላቅ ያለ የክፍል ውስጥ አመራር (አያያዝ) ክህሎትን ይጠይቃሉ:: ተማሪዎች ለዚህ የትምህርት አቀራረብ አዲስ ከሆኑ ይህ ክህሎት በተለይ አስፈላጊ ይሆናል:: መምህራን አሳታፊ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ የመጠቀም ችሎታቸውን የሚያዳብሩበትን እድል በተጋት መፈለግ አለባቸው (ለምሳሌ በሙያ ማሻሻያ ፕሮግራሞች ላይ መሳተፍ አለባቸው)::

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ውይይት ያለመዱ ከሆነ መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር በመሆን በአክብሮት ላይ የተመሰረተ መስተጋብር የሚያበረታቱ የውይይት ሕግጋትን እና አካሄድ ስርአቶችን መቅረጽ አለባቸው:: በተጨማሪም መምህራን አንዳንድ ተማሪዎቻቸውን ጥያቄ መጠየቅን ሊፈሩ ወይም ይህን ማድረግ ሊያስቸግራቸው እንደሚችል ሊገነዘቡ ይገባል:: ተማሪዎች ተሳትፏቸው ግዴታ ሳይሆን የሚበረታታ እና የተሳትፏቸው መጠንም በፍላጎታቸውና በተመቻቸው መጠን እንደሆነ እንዲሰማቸው ማድረግ ተገቢ ነው:: በዚህም መምሪያ በተጠቀሱት መልመጃዎች ከወረቀት የትምህርት ግብአቶች በተጨማሪ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ለማሳተፍ እንደ የሰሌዳ ጨዋታዎች (Board games) ፣ የኦንላይን ጨዋታዎች ፣ ቪዲዮዎች ፣ የሞባይል መተግበሪያዎችን የመሳሰሉ የትምህርት መሳሪያዎችን እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ::

## 2.4 የትምህርት መልመጃዎችን መምረጥ

ይህ የትምህርት መምሪያ መምህራን መርጠው ለተፈለገው አላማ እንዲጠቀሙ የሚያስችሉ የመልመጃ (ተግባር) ስብስቦችን ይዟል:: በክፍል ሶስት መጀመሪያ ላይ ጠቅለል ያለ የመጀመሪያዎቹ ቅኝት ይገኛል:: በተጨማሪም በክፍል 4 ለተሰጠው ትምህርት መመዘኛ የሚውሉ ሃሳቦችም (ምክሮች) ይገኛሉ::

በዚህ የመመሪያ መጽሐፍ ውስጥ ባሉ መልመጃዎች መምህራን በወረቀት ላይ ከተመሰረቱ የትምህርት ግብአቶች በተጨማሪ እንደ ቦርድ ጨዋታዎች፣ የበይነ መረብ ጨዋታዎች፣ ቪዲዮዎች እና የሞባይል መተግበሪያዎች ያሉ የመማሪያ ግብአቶችን በመጠቀም ተማሪዎችን ይበልጥ እንዲያሳትፉ ይበረታታሉ።

በዚህም መምሪያ ውስጥ መምህራን ለክፍላቸው ጠቃሚና አስፈላጊ የሆኑ የማስተማሪያ መልመጃዎችን የሚያገኙባቸው የተለያዩ መንገዶች ተቀምጠዋል:: እነዚህም :-

- በትምህርት ውጤት (ክፍል 3.1 ይመልከቱ)
  ይህ ሰንጠረዥ እያንዳንዱን ትምህርት ውጤት የተዘጋጁ መልመጃዎችን የተመለከተ መረጃ ይዟል::
- የቁልፍ ቃላት ማውጫ (አባሪ I ን ይመልከቱ)
  መምህራን ቁልፍ ቃላትን በመጠቀም ለአንድ የተለየ ርእሰ ጉዳይ ወይም ጽንሰ ሃሳብ የሚሆን የትምህርት መልመጃን ፈልጎ በማግኘት መጠቀም ይችላሉ (ምሳሌ ሥነ-ምግባር ላይ የተመሰረተ ውሳኔ አሰጣጥ ወይም ስለ ሙስና)::
- የርዕስ ጉዳይ ማውጫ (አባሪ II ን ይመልከቱ)
  በእያንዳንዱ መልመጃ መምህራን የሚከተሉትን መረጃዎች ያገኛሉ:
  - የትምህርት ውጤት (Learning outcome): ተማሪው ያወቀው ፣ የተረዳው እና የትምህርት መልመጃዎች በሚጠናቀቁበት ጊዜ ምን ማድረግ ይችላል (ክፍል 1 ገጽ 20ን ይመልከቱ)
  - ምክንያት (Rationale): ይህ የትምህርት መልመጃ አስፈላጊ ወይም ጠቃሚ ነው ተብሉት ምክንያት እና የመልመጃ የሚያመጣው ውጤት::
  - ሂደት (Procedure): መምህሩ መልመጃዎችን ሲጠቀም እንዲከተላቸው የሚመከረው ደረጃቸው (steps) እና የቀረበ ይዘት (ለምሳሌ የተለያዩ ሁኔታዎች (scenarios)) እዚህ ላይ ይገለጻል::
  - ማስማማት ጠቃሚ ምክሮች (Adaptation/tips): አንድ አስፈላጊ ግብአት ካልተሟላ መልመጃው እንት ሊቀየር (ሊስተካከል) የሚቀየርባቸው ልዩ መንገዶች እንዲሁም እንቅስቃሴው በተቃና ሁኔታ እንዲሄድ ለማድረግ ጠቃሚ ምክሮች ናቸው።
  - ቅጥያ (Extension): ለማጠናከር ሊደረጉ የሚችሉ ተጨማሪ መልመጃዎች
  - ቁሳቁሶች (Materials): የመልመጃው የሚያስፈልጉ ግብአቶች (ቁሳቁሶች)
  - የሚፈጀው ጊዜ (Duration): ለመልመጃው የሚያስፈልገው ጊዜ ግምት
  - የታለሙት ተማሪዎች (Target learners): መልመጃው የተዘጋጀው ለየትኞቹ ተማሪዎች ነው? በ2ኛ ደረጃ ጀማሪዎች (ክፍል 9 እና 10) ወይስ ከፍ ባለው ደረጃ (ክፍል 11 እና 12) ለሚገኙት ነው?
  - የትምህርት አይነት (Subject(s)): መልመጃው የሚሰጥበት የትምህርት ዓይነት (በየትኛው የትምህርት አይነት ውስጥ ነው መልመጃው የሚቀርበው?
  - ቁልፍ ቃላት (Keywords): መልመጃዎች የሚመለከታቸው ወሳኝ ጽንፈ ሃሳቦች

መምህሩ በእያንዳንዱ መልመጃ ውስጥ ያሉትን ጽንሰ ሃሳቦች እና ሂደቶች ከባህል አውዱ የክፍል አከባቢ እንዲሁም ካለው ግብአት ጋር እንዴት ማጣጣም እንዳለበት ማሰብ ይጠበቅበታል::ግብአቶች አይነታቸው እና ያለው አቅርቦት በሰፊው ሊለያይ ይችላል:: ለምሳሌ ከኢንተርኔት ተደራሽነት እስከ ጥቁር ሰሌዳ መጠቀም እስከ ጨርሶ የአቅርቦት ያለመኖር ሊደርስ ይችላል::

## 2.5 መልመጃዎቹን ማስማማት (ማስተካከል)

መልመጃዎችን ማስማማት ማለት ቀላል ማስተካከያ (ለውጥ) ማድረግ ሊሆን ይችላል:: ነገር ግን ከዚህ በተቃራኒ መምህራን ከት/ቤታችን ወይም ክፍላቸው አውድ ጋር የተስማማ ፈጽሞ የተለየ መልመጃ ለመቅረጽ ሊነሱ ይችላሉ: : በእያንዳንዱ መልመጃ የተቀመጡ ውስን ተፈፃሚነት ያላቸው የማስተካከያ (ማስማሚያ) ምስክሮች እንዳሉ ሆኖ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ምክሮች ለሁሉም መልመጃዎች ተፈጻሚ የሚሆኑ ናቸው::

## የክፍል ውስጥ ተግዳሮቶች

- ከፍተኛ የተማሪዎች ቁጥር
  በትንንሽ ቡድኖች ወይም በጥንዶች መካከል ውይይት ማድረግና ማሰብ አስተማሪው ለጠቅላላው የክፍሉ ተማሪዎች ድጋፍ ከማድረግ ይልቅ እንደአስፈላጊነቱ ለቡድኑ እገዛ መስጠት ይመረጣል፡፡

- ያለው ጊዜ
  የመልመጃውን ጊዜ ማሳጠር ወይም ማስረዘም መልመጃዎቹን ለተለያዩ ክፍሎች ማደል ፣ ማካፈል ፣ የመልመጃዎቹን የተለያዩ ክፍሎች ለተለያዩ ቡድኖች መመደብ (ማከፋል) ወይም የተወሰነውን የስራ ክፍል በቤትስራነት ለተማሪዎች መስጠት፡፡

- ቁሳቁሶችን ማስተካከል (ማሻሻል)
  አስፈላጊ ቁሳቁሶችን (Materials) ማግኘት ፣ መስራት ወይም መተኪያ (አማራጭ) ማዘጋጀት ለምሳሌ፡- መልመጃው ተማሪዎች በካርቶን ወይም በኮምፒዩተር ፖስተር እንዲሰሩ የሚጠይቅ ከሆነና እነዚህ ግብአቶች ከሌሉ ተማሪዎች በምትካቸው የመልመጃ ደብተራቸውን ወይም ጥቁር ሰሌዳ መጠቀም ይችላሉ፡፡ የፎቶ ኮፒ ማሽን የማይኖር ከሆነ ጠንካራ ወረቀት ወይም ካርድ ላይ ማተም ወይም መጻፍና ከተቻለ ማሸግ ይህም ወረቀቱን መልሶ ጥቅም ላይ ለማዋል ይጠቅማ፡፡ የመጫወቻ ሰሌዳና መጫወቻዎቹን (pieces) ፣ የእንቆቅልሽ መጫወቻ ፣ ልጆች እየተጫወቱ የሚማሩባቸው ካርዶች (flash cards) እና ሌሎች የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በአካባቢያችን ከሚገኙ ቁሳቁሶች ማለትም እንደ ጣሳ ፣ የጠርሙስ ክዳኖች ካርቶኖች እናየፕላስቲክ ጠርሙሶች ወ.ዘ.ተ ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ተማሪዎች የወረቀት ላይ መልመጃዎችን

  በቀላሉ ከሚገኙ ቁሳቁሶች ማለትም እንደ ጣሳ ፣ የጠርሙስ ክዳኖች ፣ ካርቶኖች እና የፕላስቲክ ጠርሙሶች ወ.ዘ.ተ ማዘጋጀት ይችላል፡፡ ተማሪዎች የወረቀት ላይ መልመጃዎችን በቀላሉ ከሚገኙ እንደ ቪዲዮ የማህበራዊ ሚዲያ ወ.ዘ.ተ በመጠቀም ወደ ዲጂታል የትምህርት መልመጃ እንዲቀየሩ ያድርጉ፡፡

- አማራጭ የምርምር ጥናት ግብዓቶች (በት/ቤት በቀረበ የመረጃ ቴክኖሎጂ ምትክ)
  እውቀት ያላቸው የሕብረተሰብ አባላትን ለንግግር መጋበዝ በትምህርት ቤቱ ፈቃድ ተማሪዎች ሞባይል ስልካቸውን (ሞባይል ዳታ) እንዲጠቀሙ ያድርጉ፡ ፡ ወይም መርምርና ጥናቱን በቤት ስራ መልክ እንዲሰጥ ያድርጉ፡፡ መምህሩ ቪዲዮ ማሳየት ካልቻለ በምትኩ ተመሳሳይ ሁኔታን የሚያሳይ የሚና ጨዋታን መፍጠር ይችላሉ፡፡

- አስፈላጊ የቦታ መጠን
  የክፍል ውስጥ መቀመጫዎች ጠረጴዛዎች ወ.ዘ.ተ በሚፈላገው መንገድ ያደራጁ ወይም አማራጭ ሰፊ ክፍል ይጠቀሙ፡፡ አለበለዚያ መልመጃውን ከክፍል ውጭ ያሰሯቸው ይህን ማድረግ በተለይም ለቡድን ውይይት ጠቃሚ ነው፡፡ ምክንያቱም የአንዱ ቡድን ድምጽ እንዳይረብሽ ይከላከላልና፡፡

## ከባህል ጋር ማስማማት

- ስሞችን የሌሎች ቁሳቁሶችን መጠሪያ ተማሪዎች ሊያውቋቸው በሚችል መልኩ መቀየር
- የቀረቡ ፅሁፎችና ስነ-ጥበቦች በአከባቢው (በሚታወቁ) ፅሑፍና ስነ- ጥበቦች ይተኩ (ታሪክ ፣ሙዚቃዎች ፣አፈታሪኮች ጨዋታዎች ስዕል ወ.ዘ.ተ)

**መምህሩ በእያንዳንዱ መልመጃ ውስጥ ያሉትን ጽንሰ ሃሳቦችንና ሂደቶችን ከባህል አውድ ፣ የክፍል አካባቢ ፣ እንዲሁም ካሉት ግብአቶች ጋር እንዴት ማስማማት (ማጣጣም) እነዳለበት ማሰብ ይጠበቅበታል፡፡**

## አከባቢያዊና ፖለቲካዊ አስፈላጊነት

- እንደ እሴቶች ፣ ሐቀኝነትና ተጠያቂነት የመሳሰሉ ረቂቅ ፅንሰ ኃሳቦችን ለመግለፅ የአካባቢውን ቋንቋ ይጠቀሙ ቀጥተኛ ቃላት ማግኘት ባይቻል ሃረጎችን መጠቀም ይችላሉ፡፡ የአካባቢው ተቋማትን ስምና ሂደት ይጠቀሙ (ምሳሌ ፡- ፖሊስ እና የአካባቢው አመራር የስልጣን መጠሪያዎች)፡፡
- የአካባቢውን ባህልና አኗኗር ደንቦችን (ምሳሌ፡- እድሜንና ጾታን የተመለከቱ) ከግምት ውስጥ ያስገቡ፡፡ የመልመጃዎቹ ይዘት በማህበረሰቡ የሚስተዋለውን የሐቀኝነት መጠንን (የሙስና መኖር ፣ በአመራሮችና ተቋማት ላይ ያለ እምነት ፣ ያለው የወንጀል መጠን ወ.ዘ.ተ) ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይገባዋል፡ ፡ ለምሳሌ፡- የአካባቢው አመራሮች ሐቀኝነት የሚጎድላቸው ከሆነና ሙስና የተንሰራፋ በሚሆንበት ጊዜ መምህሩ መልመጃዎቹን የዜጎችን ተደራጅቶ ሙስናን የመቃወም ችሎታ ላይ እንደያተኩሩ ከማድረግ ይልቅ መልካም ለማድረግ የሚያስፈልጉ እሴቶች ፣ ክህሎቶች ፣ የሌሎችን መብቶች ማክበር እንዲሁም በግጭት አፈታት ዙሪያ እንዲያጠነጥኑ ቢያደርጋቸው ይመረጣል፡፡

## በሚገኙበት ሁኔታና በአስተዳደጋቸው የተለያዩ ተማሪዎችን ማካተት

- የተማሪዎች የማንበብ ክህሎት ደረጃ:
  አብዛኞቹ መልመጃዎች ጽሁፍን አንብቦ መረዳት የሚጠይቁ በመሆናቸው መምህራን የተማሪዎቻቸውን የንባብ ብቃት መፈተሽ ያስፈልጋቸዋል:
  - ምንባቡን ከተማሪው የማንበብ አቅም ጋ ለማጣጣም የ "ቅድመ ማንበብ ቴክኒክ" (Pre-technique) ተጠቀም።
  - ምንባቡን በቀላል ምንገድ ማቅረብ
  - ስለ ርእሰ ጉዳይ ቀላል ወይም ውስብስብ ምንባብ አቅርብ
  - ምንባቡን እራስህ ወይም የተሻለ የማንበብ አቅም ያለው ተማሪ ለክፍሉ እንዲያነቡ አድርግ
  - ምንባቡን በተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ መተርጎም፡፡

- መልመጃዎችን ልዩ ፍላጎት ላላቸው ተማሪዎች ማስማማት:
  - ተፈጻሚ ማድረግ ከተቻለ በግለሰብ ደረጃ በሚቀርብ የትምህርት አሰጣጥ እቅድ የሚፈፀመው ማስተካከያወች እና ማሻሻያዎችን መከተል (ለምሳሌ:- የሚጠበቅ ውጤት አይነትን ከፅሁፍ ወደ ቃል መቀየር ፣ አካላዊ እንቅስቃሴን እንደ አስፈላጊነቱ ማስተካከል ወ.ዘ.ተ)።
  - ተማሪዎች በማንበብ እና መፃፍ ተግባራት ከረዳት ወይም ጓደኛ ድጋፍ እንዲያገኙ መፍቀድ እነዲሁም ስራውን ለማጠናቀቅ በተመደበው ጊዜ ላይ ተጨማሪ ሰአት መስጠት
  - ዝቅተኛ የማንበብ ክህሎት ላላቸው ወይም ትምህርቱ የሚሰጥበትን ቋንቋ በደንብ ለማይችሉ ተማሪዎች ተጨማሪ የምስል እገዛ (ስዕሎች ፣ፎቶዎች ፣ ምልክቶች ማቅረብ)

- ለጾታ ትኩረት መስጠት (Gender sensitivity):
  ጾታ ነክ አስተሳሰቦችን (የጅምላ ፍርጃን)አስወግድ፣ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ የሚመሰረቱ ቡድኖች የጾታ ስብጥር እንዲኖሯቸው አድርግ፣ ሁሉም ተማሪዎች በተለይ ሴቶች በክፍል ውይይቶች እና በት/ቤት ተግባራት ላይ በንቃት እነንዲሳተፉ አበረታታ፡፡

- ለባህል ብሔር እና የቋንቋ ልዩነቶች ትኩረት መስጠት:
  ስህተት አመለካከት ወይም የጅምላ ፍርጃን (stereotype) አሰወግድ ፣ ተገቢ በሆነበት ሁኔታ ሁሉ ቡድኖች የባህል ፣ ብሔርና ቋንቋ ስብጥር እንዲኖራቸው አድርግ፡፡

- ለተማሪዎች ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ትኩረት መስጠት:
  ከተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ደረጃዎች የመጡ ተማሪዎች ሊያጋጥሟቸው የሚችሉትን የተለያዩ የሙስና ዓይነቶች ማሰብ፣ ለምሳሌ ጉቦ መስጠት ወይም መቀበል።

**ሙስና በተንሰራፋባቸው አውዶች መምህራንና የት/ቤት ሰራተኞች ከት/ቤት ውጭ የሚያሳትፏቸውን ድርጅቶች (ተቋማት) በጥንቃቄ መምረጥ አለባቸው እንዲሁም ስለሚያስገኙት እድሎችና ስለሚደቅኑት አደጋዎች በጥንቃቄ መገምገም አለባቸው፡፡**

## የአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ተደራሽነት

- አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የሚጠቀሙ መልመጃዎች ሲኖ ተማሪዎች ከልዩ ልዩ ሚዲያዎች (ለምሳሌ:- የወረቀት ፣ ቲቪ ፣ ራዲዮ ሞባይል) መካከል እንዲመርጡ በመፍቀድ አማራጭ እንዲያገኙ አድርግ፡፡

- ተማሪዎች የዲጂታል መሳሪያዎችን እንዲጋሩ ከተቻለ ስራውን በቡድን እንዲሰሩ አድርግ

- ሁኔታው የሚፈቅድ (አስቻይ) ከሆነ የትምህርት አሰጣጥ ቅይጥ (በተለያየ መንገድ) እንዲሆን አበረታታ፡፡ ለምሳሌ:- ትምህርት በተለምዶ ከሚሰጥበት ቦታ (ክፍል) በተጨማሪ "አንላይን" እንዲቀርብ ማድረግ ይቻላል፡፡

## የትምህርት አሰጣጥ ዘዴዎች (መንገዶች)

- እንደ አጭር ታሪክ ፣ ትንታኔዎች እና ከሬዲዮ ፣ ፊልሞች ፣ ካርቶኖች ፣ቪዲዮዎች የተወሰዱ የድምጽ ምስል የመሳሰሉ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን አበረታታ፡፡

- ተማሪዎች፣ በተለይም እኩል ተጠቃሚ የማህበረሰብ ክፍል፣ የሚመጡትንተማሪዎች ፣ በውይይት እንዲሳተፍና መልመጃዎቹን በመቅረጽ እረገድ አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ በትጋት አበረታታ፡፡

- በትምህርቱ መጨረሻ ያልተፈቱ ጉዳዮችን ወይም ጥያቄዎችን (ስጋቶችን) ለማስተናገድ የሚያስችል ትርፍ ጊዜ መድብ፡፡

መምህራንና ሌሎች የት/ቤቱ ሰራተኞች ሐቀኝነትን የሚያጎለብቱባቸውን ተጨማሪ ተግበራትን ለመፈጸም ማቀድ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም ሐቀኝነትን ለማስፈን ሕብረተሰብ አቀፍ አቀራረብን ለማስተዋወቅ ወይም ለማበረታታት ተማሪዎቻቸውን ብቻ ሳይሆን ቤተሰቦቻቸውን ፣ማህበረሰቡንና በአካባቢው የሚገኙ ድርጅቶችን ማሳተፍ አለባቸው፡፡ የተወሰኑ በመምሪያው ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎችን ለዚህ አላማ የተዘጋጁ ሲሆኑ ሌሎቹ ከክፍል ውስጥ መልመጃዎቹ በመነሳት እንዲሰፉ ወይም እንዲሻሻሉ (እንዲያድጉ) ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ሙስና በተሰራፋባቸው አውዶች መምህራን እና የት/ቤቱ ሰራተኞች ከት/ቤት ውጭ የሚያሳትፏቸውን ድርጅቶ (ተቋማት) በጥንቃቄ መምረጥ አለባቸው፡፡ እንዲሁም ስለሚያስገኙት እድሎች እና ስለሚደቅኑት አደጋዎች በጥንቃቄ መገምገም አለባቸው፡፡

## 2.6 መዘጋጀት፦ የመምህራን ዝግጁነት

ሐቀኝነትን እና እንደ ታማኝነት፣ ሚዛናዊነት፣ ግልፅኝነት እና ተጠያቂነት ያሉትን ተጓዳኝ እሴቶችን ለማስተማር መምህራን በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ተጨማሪ ዝግጅት ይጠበቅባቸዋል፡፡

### ምክንያታዊ ያልሆነ ድምዳሜዎችን ስሁት አመለካከቶን እና የጅምላ ፍርጃዎችን ማስወገድ

መምህራን በትምህርት ግብአቶች (ማቴሪያሎች) በትምህርት ስርአት እና አተገባበር ውስጥ ግልፅም ይሁን ስውር ስሁት አመለካከቶች እና ድምዳሜዎችን በጥንቃቄ ማስወገድ አለባቸው፡፡[1] መምህራን ስሁት አመለካከትን ወይም አድሎን (ለምሳሌ፡- የተለየ ባህል ያላቸውን ተማሪዎች በተመለከተ) በሚያንጸባርቁበት ጊዜ የግልፅነትና ትብብር መንፈስ እንዲዳከም የሚያደርግ ብቻ ሳይሆን አድሎና ሌሎች ኢ-ሥነምግባራዊ ባህርያትንም ያስከትላል፡፡

### የትምህርትን ርዕሰ ጉዳይ በተመለከተ በቂ እውቀት (ግንዛቤ) መኖሩን ማረጋገጥ

አንዳንድ መልመጃዎች መምህራን በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ተጨማሪ እውቀት እንዲኖራቸው ያስገድዳሉ፡፡ ለምሳሌ፡- መምህራን የአካባቢውን እና የብሔራዊ ህግጋትን ፣ ሐቀኝነትን ለማጎልበት ተቋማት ስላላቸው ሚና ወይም ስለ አለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ማወቅ ሊጠበቅባቸው ይችላል፡፡ በሌላ በኩል አንድ ተማሪ መምህሩ ሊመልሰው የማይችለውን ጥያቄ ቢያነሳ መምህሩ መልሱን እንደማያውቅ በግልፅ በመመለስ ታማኝነትን ማሳየት አለበት፡፡ በተጨማሪም መምህሩ ለተነሳው ጥያቄ ምላሽ ሊሰጥ የሚገባው በቂ ጥናት ካደረገ እና መረጃ ከሰበሰበ በኋላ ነው፡፡

### ከማሕበረሰቡ ግብአቶችን ማሰባሰብ

መምህራን አዲስ ርዕሰ ጉዳይ በሚያስተምሩበት ጊዜ እና በጉዳዩ ላይ በቂ ተጨባጭ እውቀት በማይኖራቸው ጊዜ በማህበረሰቡ የሚገኙ ግብአቶችን (ምንጮችን) መፈተሽ ጠቃሚ ነው፡፡ እንደየ ትምህርቱ አላማዎች ግብአቶች እንደ ፀረ-ሙስና ባለስልጣናት ፣ የሚመለከታቸው መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን፣ የአካባቢው መንግስት ወኪሎች የመሳሰሉትን ሊይዝ ይችላል፡፡ እነዚህ ምንጮች (ግብአቶች) እረቂቅ የሆኑ ሃሳቦችን ተጨባጭ (ተግባራዊ) እይታን እንዲላበሱ በማድረግ ትምህርቱን ነፍስ እንዲዘራ በማድረግ ጠቃሚ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡

### ጥንቃቄ የሚያሻቸው ጉዳዮች አያያዝ

መምህራን ተማሪዎች ያልተረጋገጠ ፣ አስቸጋሪ ወይም ልዩ ጥንቃቄ የሚሻው (sensitivity) መረጃን በሚያጋሩ ወቅት ተገቢ የሆነ መልስ ለመስጠት ዝግጁ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ለምሳሌ፡- መምህራን በክፍል ውስጥ ውይይቶች ወቅት ያልተረጋገጡ የአመራሮች ሐቀኛ ያለመሆን አይነት ስሞታዎች (አሉቧልታዎች) የማይስተናገዱ ስለመሆኑ መግባባት እንዲኖር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ መምህራን ተማሪዎች የውይይት ጉዳዮችን ከሰዎች ጋር ማያያዝን (personalizing) እንዲያስወግዱ ሊያበረታቷቸው ይገባል፡፡ የአንድ ባለስልጣን (መሪ) ድርጊት ላይ ከማተኮር ይልቅ ከድርጊቱ (ውሳኔው) ጀርባ ስላለው መርህ ይጠይቋቸው፡፡

**መምህራን ተማሪዎቻቸው የውይይት ጉዳዮችን ከግለሰቦች ጋር ማያያዝ (personalizing) እንዲያስወግዱ ሊያበረታቷቸው ይገባል። የአንድ ባለስልጣን (መሪ) ድርጊት ላይ ከማተኮር ይልቅ ከድርጊቱ (ውሳኔው) ጀርባ ስላለው መርህ ይጠይቋቸው።**

1 UNESCO (2017), "Making text content inclusive: A focus on religion, gender, and culture".

ክፍል 3

# የትምህርት መለመጃዎች ዝርዝር



በሚከተለው ክፍል መልመጃዎች በሁለት ተመድበው (ተከፍለው) የቀረቡ ሲሆን በመጀመሪያው ምድብ በክፍል ውስጥ የሚከናወኑ እና በአጠቃላይ ውስን (አጭር) ጊዜ የተሰጣቸው ሲሆን በሁለተኛው ምድብ ከክፍል ውጭ የሚከናወኑ ፣ ረጅም ጊዜ የሚወስዱ እና ያልተገደቡ (open ended) መልመጃዎቹ ከአለም ዙሪያ በተገኙ ምንጮች መነሻነት የተዘጋጁ ወይም ከእነዚህ ምንጮች የተወሰዱ እና አስፈላጊው ለውጥ (ማስማማት) ተደርጎላቸው የቀረቡ ናቸው፡፡ መልመጃዎቹ ልዩ ልዩ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴዎችን ይይዛሉ፡፡

ከእነዚህም ዘዴዎች ውስጥ፡

- የጥንድና የቡድን ውይይት
- "ፊሊፕድ ክላስ ሩም" (flipped classroom)
- የተማሪ "ፕረዘንቴሽን"
- የሚና ጨዋታ
- መረጃን ከአንድ ወደ ሌላ መልክ የማዘዋወር ተግባር
- የመልቲ ሚዲያ አቀራረቦች

## 3.1 የክፍል ውስጥ እና የክፍል ውጭ መልመጃዎች ጠቅለል ያለ እይታ ዳሰሳ

ቀጣዩ ሰንጠረዥ የትምህርት መልመጃዎቹ ለተማሪዎች በሚያመጡት ዉጤት ላይ የተመሰረተ አጠቃላይ እይታን ያቀርባል፡፡


| | የትምህርት ውጤት | የመልመጃው ስም | ገፅ |
|---|---|---|---|
| 1 | ተማሪዎች ስለ ሐቀኝነትና ተያያዥ ፅንሰ ሃሳቦች ግንዘቤ ያገኛሉ | የሐቀኝነት ትርጉም ወይም ምንነት | 26 |
| | | ሐቀኝነት በስፖርት ውስጥ | 28 |
| | | ብሔራዊ የሐቀኝነት ስርአት | 29 |
| | | ሐቀኝነትን ከሚገነቡ ድርጅቶች ጋር የሚኖር መስተጋብር | 30 |
| 2 | ተማሪዎች የውሳኔ አሰጣጥ ሐቀኝነት ላይ ተፅዕኖ ያላቸው ጉዳዮችን ይመረምራሉ | ጾታ እና ሙስና | 31 |
| | | ሰበብ ፍለጋ ወይም መፍጠር? | 33 |
| 3 | ተማሪዎች ከሰው ልምዶች ጋር የውግንና መንፈስን (የእኔነት ስሜትን) እና ሐቀኝነትን የተመለከተ የሃላፊነት ስሜት ይጋራሉ | እኔ ምንም አልሆንኩም | 34 |
| | | የሐቀኝነት ምልክቶች | 35 |
| | | ከተመልካችነት ወደ ማገዝ (መርዳት) | 36 |
| | | የግጭት አያያዝ (አፈታት) | 37 |
| 4 | ተማሪዎች የሐቀኝነትን መሰረታዊ እሴትነት ይገነዘባሉ ፤እውቅና ይሰጣሉ፡፡ | ለዚህ ስያሜ (ቃል) አለን | 38 |
| | | አንተ ብትሆን ምን ታረጋለህ? | 39 |
| | | ሐቀኝነትን ማክበር | 40 |
| 5 | ተማሪዎች መልካም ሥነ-ምግባር የተላበሰ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ምክንያታዊ (የጠለቀ) አስተሳሰብ ይከተላሉ | ፈተናዎች (temptations) | 41 |
| | | ተግባሮቼ እሴቶቸን ያንጸባርቃሉ? | 42 |
| | | እውነቱ የትኛው ነው? | 43 |
| | | ተመጣጣኝ (ተገቢ) ወጭ ማውጣት | 44 |
| | | መብቱን አስረግጦ የሚናገር የሌሎችን መብት የሚያከብር (Assertive), አመለካከቱን ለመግለጽ የማይደፍር (Passive), የራሱን አመለካከት ሌሎች ላይ ለመጫን የሚሞክር (Aggressive) | 45 |
| 6 | በመልካም ሥነ-ምግባር የታነጸ ባህሪ ባለቤት በመሆ ተማሪዎች ሐቀኛ ህይዎት ይመራሉ | እሴቶቻችሁ ምንድን ናቸው? | 46 |
| | | የኔ ቃል ኪዳን | 48 |
| | | የሐቀኝነት ሱቅ | 49 |
| 7 | ሐቀኝነትን ለማጎልበት ወይም ለማጠናከር ተማሪዎች የነቃ ተሳትፎ እና የጋራ ርምጃ ይወስዳሉ | በጋራ መስራት | 50 |
| | | ለሚመለከተው በሙሉ | 51 |
| | | የኔ "ቴድቶክ" (MyTed talk) | 52 |
| | | ምስሎች! | 53 |
| | | የማህበራዊ ሚዲያ ሃይል | 54 |
| | | የዜና ጊዜ (ሰዓት) | 55 |
| | | አለሜን የሚቀይር እቅድ | 56 |
| | | አሳታፊ (interactive) ሚዲያ መፍጠር | 60 |
| | | የሐቀኝነት ክለቦች | 61 |
| | | መረጃን (Data) ለተሻለ አስተዳደር መጠቀም | 62 |

## 3.2 የክፍል መለመጃዎች

# የሐቀኝነት ትርጉም

### የትምህርት አይነት

- የስነ-ዜጋ ትምህርት
- ስነ መንግስት
- ቋንቋ
- ስነ ጽሁፍ

### ኢላማ የተድርጉ ተማሪዎች

ክፍል 9 እና 10 ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች
የተመደበ ጊዜ

### የተመደበው ጊዜ

60 ደቂቃ

### አስፈላጊ ቁሳቁሶች / ግብአቶች

ካርዶች ፣ወረቀቶች ፣የስእል መሳሪያዎች ፣ (ይህ አማራጭ ጥቅም ላይ ከዋለ)

### ቁልፍ ቃላት

ተጠያቂነት ፣ ሙስና እና ግልጸኝነት

## የትምህርቱ ውጤት

ሐቀኝነትና ተያያዥ ፅንሰ ሀሳቦችን መገንዘብ (መረዳት)

## ምክንያት (RATIONALE)

ሐቀኝነት በተገቢው ሁኔታ የተገነዘብነው (የተረዳነው) ፅንሰ ሃሳብ ወይም እሴት ላይሆን ይችላል፡፡ የሐቀኝነት እና ተጓዳኝ (ተያያዥ) ፅንሰ ሃሳቦን ትርጉም እና እንድምታቸውን (implications) የተሻለ በመረዳት ተማሪዎች ሐቀኝነት የሚለውን ቃል መጠቀም ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ምክንያታዊ (ጥልቅ) አስተሳሰብን በመጠቀም አንድ ውሳኔ ሐቀኝነትን ተመርኩዞ ስለመወሰንና ያለ መወሰን ማረጋገጥ ይችላሉ፡፡

## ሒደት (የአካሄድ ስርአት)

1. ሐቀኝነት ማለት ከሥነ-ምግባር መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ (መንገድ) የምታደርገውን መፈጸም ወይም ህይዎትህን መምራት በተለይም ጫናውን እና ፈተናውን (temptations) ተቋቁሞ ታማኝነትን በተግባር ማሳየት ማለት መሆኑን አስረዳ፡፡
2. ሐቀኝነትን የያዙ (የሚያሳዩ)እና ሐቀኝነት የጎደላቸው ተግባራትን በምሳሌነት አቅርብ ፣እንዲሁም ተግባራቱን (ድርጊቱን) እንዲተነትኑ (እንዲመረምሩ) እና በሐቀኝነት ላይ የተመሰረቱ ድርጊቶችን እንዲለዩ ተማሪዎቹን ጠይቅ፡፡

የሥነ-ምግባር መርሆዎችን ያለተከተሉ (የሚጥሱ) ድርጊቶች ምሳሌዎች ፡

- አንድ የእግር ኳስቡድን ካፒቴን ለእውነተኝነትና የጨዋታ ሕጎችን ማክበርን ዋጋ እንደምትሰጥ ትናገራለች ይሁንና ኳሱ ወደ ውጭ መውጣቱን ለመደበቅ ትሞክራለች፡፡
- መደበኛውን (ተራውን) ነዋሪ ለማገልገል እና ሙስናን ለመቀነስ አላማ አድርጎ ለከተማ ምክር ቤት በመወዳደር ላይ ያለ እጩ ተወዳዳሪ ዘመዶቹ ከምርጫ በኋላ ስራ ለማግኘት እንዲረዳቸው ጠየቀ ይሁንና ተወዳሪው የሕዝብ ስልጣን ከተረከቡ በኋላ የግል ውለታውን መፈጸም ከሥነ-ምግባር ጋር ተነጻጻሪ በመሆኑ ይህን ማድረግ የሱ የስራ ድርሻ እንዳልሆኑን በመግለጽ ፈቃደኛ እንዳልሆነ ገለጹ፡፡

3. ተማሪዎች የራሳቸውን ምሳሌዎች (ሊሆኑ የሚችሉ ልዩ ልዩ ሁኔታዎች) እንዲፈጠሩ እና በቡድን ሆነው እነዚህ ተግባራት በሐቀኝነት የተፈጸሙ መሆን ያለመሆናቸው ላይ እንዲወያዩ አበረታታ፡፡
4. ሕግንና ደንብን ማክበር ፣ ይህንን ለማድረግ የሚያስከትለው ቅጣት በሌለበት ሁኔታ ጭምር ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ተማሪዎችህ እንዲወያዩ አድርግ፡፡
5. ከታች የተቀመጡትን ጥቅሶች በካርዶች ወይም ወረቀቶች በመገልበጥ ለእያንዳንዱ ተማሪ አንዳንድ ካርድ ወረቀት አድል፡፡ እነዚህ ጥቅሶች ለምሳሌነት የቀረቡ ስለሆኑ ለሌሎች በተለይም ከተማሪዎቹ ባህልና ቋንቋ በተወሰዱ ሊተኩ ይችላሉ፡፡ሁሉም ተማሪዎች እነዚህ ጥቅሶች ስለሐቀኝነት ያላቸውን ትርጉም እና ከህይዎታቸው ጋር እንዴት እንደሚዛመዱ እንዲወያዩ አድርግ፡፡
6. ተማሪዎች እነዚህን ጥቅሶች የሚያስረዱ ፖስተሮችን እንዲዘጋጁ ፣ የሚና ጨዋታ እንዲፈጥሩ ወይም የማህበራዊ ሚዲያ ፅሁፎችን እንዲያወጡ ጋብዛቸው (ጠይቃቸው)፡፡ የት/ቤት ውድድር በማዘጋጀት ተማሪዎች ለወደዷቸው ፈጠራዎች ድምፅ እንዲሰጡ እና የመረጡትን መመዘኛ ምክንያት) ከሐቀኝነት አንጻር እንዲያስረዱ እድል ስጣቸው፡፡ የተማሪዎቹ ፈጠራ የሚታይበት አውደ ርዕይ በት/ቤት ውስጥ በማዘጋጀት የት/ቤቱን አመራሮች የማህበረሰብ አባላት እና ወላጆችን እንዲጋበዙ አድርግ፡፡

ሐቀኝነትን የተመለከቱ ጥቅሶች:

ሀ/ "ልክ የሆነውን ነገር ለማድረግ ጊዜው ሁሌም ልክ ነው" – ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር
ለ/ "ትክክል የሆ ነገር ሁሉ ሁሌም ተወዳጅ አይደለም ተወዳጅ የሆነ ሁሉ ሁሌም ትክክል አይደለም" – ኤች ጃክሰን ብራውን ጁኒየር
ሐ/ "ሐቀኝነት ቀላል (ምቹ) በሆነና ትክክል (ልክ) በሆው መካከል ምርጫ ነው፡፡" – ቶኒ ደንጊ

ማሳሰቢያ፡-እነዚህ ጥቅሶች በምሳሌየቀረበ ብቻ ናቸው፡፡ መምህራን ከራሳቸው አውድ ጋር የሚጣጣሙ ጥቅሶችን እንዲፈልጉ ይበረታታሉ፡፡

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

መምህሩ መልመጃውን ተማሪዎችበቡድን እንዲሰሩ በማድረግ እና የራሳቸውን የሐቀኝነት ትርጉም እንዲያቀርቡ መጠየቅ መጀመር ይችላል፡፡ይህንን ማድረግ መምህሩ ተማሪዎች ቀደመው በሚያውቁት ላይ ለመገንባት (ለመጨመር) ያግዘዋል፡፡ በዚህ መልኩ ቅደም ተከተሉን መገልበጥ ጊዜን የሚፈጅ እና መምህሩን ተጨማሪ የማሳለጥ ስራን የሚጠይቀው ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁንና ይህንን ማድረግ ይመረጣል፡፡ምክንያቱም ከፍ ያለ ለውጥ የሚያስገኝ በመሆኑ ነው፡፡

ተማሪዎች የሚማሩበት ቋንቋ ከአፍ መፍቻ ቋንቋ የተለየ በሚሆንበት ጊዜ ከሐቀኝነት ጋር የተያያዙ እሴቶችን ለመግለጽ የሚያስችል በቂ ቃላት ላይራኖቸው (ላያውቁ) ይችላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ መልመጃዎን ከመስራታቸው በፊት መምህሩ ሐቀኝነት ጋር የተገናኙ ቃላት ዝርዝር (ለምሳሌ፡- ተጠያቂነት ፣ ታማኝነት ፣ ግልፀኝነት ፣ ደፋር እና ቆራጥ)ሊያዘጋጅ እና ተማሪዎቹን ለእነዚህ ቃላት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተመሳሳይ (እኩያ) እንዲፈልጉላቸው ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ይህን በሚያደርግበት ጊዜ ቋንቋውን ከሚችል የስራ ባልደረባ ወይም የቋንቋ ባለሙያ እገዛ መጠየቅ ሊያስፈልገው ይችላል፡፡ በተጨማሪም መምህሩ ሥነ-ምግባር እና ሐቀኝነትን የተመለከቱ የአካባቢው ተሰሚና ታዋቂ ሰዎች ጥቅሶችን እንዲያሰባስብ ይመከራል፡፡

የመናገርና የማንበብ ተግዳሮት ላለባቸው ተማሪዎች መልመጃው ጥቅሶችን ሐቀኝነትን በሚያሳዩ በምስሎች በመተካት ማስተካከልና ተማሪዎች ሐቀኝነት ያንጸባርቃል የሚሉትን ምስል እንዲስሉ ማድረግ ይችላል፡፡

## ማጠናከሪያ

ተማሪዎች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የተነገሩ ሐቀኝነትን የተመለከቱ ጥቅሶችን ወይም ሐቀኝነትን የሚያሳዩ ቪዲዮዎችን መፈለግ ይችላሉ፡፡ ይህ ካልተቻለ በመዝገበ ቃላት ውስጥ የሚካተት የሐቀኝነት ትርጓሜ እንዲያዘጋጁ (እንዲፈጥሩ) ተማሪዎቹን መጠየቅ ይችላል፡፡

ሌላ የማጠናከሪያ መልመጃ (ተግባር) የሙስና ትርጓሜ ላይ የሚሰራ መልመጃ ሊሆን ይችላል፡፡ ተማሪዎች በCOC ህትመት ላይ የተቀመጠውን የሙስናን ትርጓሜ የሚመለከተው መልመጃ (ተግባር) መመልከት ይችላሉ፡፡ የህትመት ርዕስ ” ትምህርት ለሐቀኝነት ፣ ፀረ-ሙስናና እሴቶችንና የሕግ የበላይነትን ማስተማር” የሚል ነው፡፡ (Education for integrity teaching on anti–corruption, values and the rule of law)

# ሐቀኝነት በስፖርት ውስጥ

### የትምህርት አይነት

- ሐቀኝነት በስፖርት ውስጥ

### ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

በታችኛው (9ኛ እና 10ኛ) እና በላይኛው ደረጃ ያሉ (11ኛ እና 12ኛ) 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

### የተመደበው ጊዜ

ለውይይቱ 30 ደቂቃ ሁለተኛው ተግባር የተመረጠ ከሆነ ተጨማሪ ሰአታት

### አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ለውይይት ምንም አይነት ቁሳቁስ አያስፈልግም። ለማጠናከሪያ መልመጃ ካርድ እና ማርከር ሊያስፈልግ ይችላል።

### ቁልፍ ቃላት

- ኢኮኖሚክስ
- ታሪክ
- የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት
- ሳይንስ

## የትምህርቱ ውጤት

ሐቀኝነትና ተያያዥ ፅንሰ ሃሳቦችን መገንዘብ (መረዳት)

## ምክንያት (RATIONALE)

ሐቀኝነት ዋጋ አጣ ማለት ብዙ የእለት ተዕለት ተግባራት አሉታዊ የሆነ ተጽእኖ ይደርስባቸዋል ማለት ነው፡፡ ይህ መልመጃ (አለም አቀፋዊ ፀረ-ዶፒንግ ኤጀንሲ ግብአቶችን ይወስዳል፡፡) ተማሪዎች ሐቀኝነት በሁሉም ደረጃ ባሉ ስፖርቶች ለምን አስፈላጊ እንደሆነ እንዲመረምሩ ይጋበብዛል፡፡

## ሒደት

1. ተማሪዎችን በቡድን ከፍለህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ አድርግ
   ሀ/ ሕግጋት እና ዳኞ በስፖርት ውስጥ ለምን አስፈለጉ? ሚዛናዊነት (quiness) ምንድን ነው?
   ለ/ ሕጎች ባይኖሩ የምትወዷቸው ስፖርቶች ምን ይመስሉ ነበር?
   ሐ/ በስፖርቶች ውስጥ ምን አይነት ድርጊቶች እንደ ማጭበርበር ይቆጠራሉ?
   መ/ አንድ ተማሪ ህግጋትን ማክበር ለማቆም ቢሞክር ውስን የስፖርቱ አዝናኝነት ይቀየራል? እንዴት?
   ሠ/ ለማሸነፍ ብላችሁ የስፖርት ሕግጋትን ጥሳችሁ ታውቃላችሁ?
   ረ/ በስፖርት ውስጥ የሚያጭበረብር ሰው በጨዋታው ለምን ያህል ጊዜ ይዝናናሉ?
   ሰ/ የጨዋታውን ህግ አክብራችሁ ተጫውታችሁ ስታሸንፉ ምን ይሰማችኋል?
2. በስፖርት ውስጥ የጨዋታዎች ሐቀኝነት ያለውን ጥቅም ለመገንዘብ የሚያስችሏቸው ፖስተር የሰሌዳ ጨዋታ ወይም የካርድ ጨዋታ እንዲያዘጋጁ ይጠይቋቸው ት/ቤቱ የኢንተርኔት ተደራሽነት ካለው የፖስተር ወይም ካርድ ጨዋታ እንዴት ሊዘጋጅ እንደሚችል ምሳሌ ለማየት ተማሪዎች የአለም ፀረ-ዶፒንግ ኤጀንሲ የፀረ- ዶፒንግ ጌም እንዲጎበኙ አድርግ፡፡

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

ፖስተር ከማዘጋጀት ወ.ዘ.ተ ይልቅ በማዘገጀት ፋንታ ተማሪዎችና አሰልጣኞች ከቡድናቸው ጋር "አዲስ የሚዛናዊነት ሕግጋት" ሲወያዩ የሚያሳይ የሚና ጨዋታ ሊያዘጋጁ ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች ለምን በስፖርት ውስጥ ዶፒንግ ኢ-ፍትሃዊ (ሚዛናዊነት የጎደለው) እንደሆነ እና ውጤቱ ምን እንደሆነ እንዲመረምሩ አበረታታቸው። ሌላው የውይይት ርዕስ የጨዋታዎች ውጤት አስቀድሞ መወሰን (Match fixing) ሊሆን ይችላል፡፡ ይህን ጉዳይ ተማሪዎች በቀላሉ ከህይዎታቸው ጋር ሊያገናኙት የሚችሉት ነው፡፡ በተጨማሪ ተማሪዎች ሐቀኝነት ለፓራ ኦሊምፒክ ስፖርት የሚጨምረው ነገር እና በዚህ አውድ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ በጥልቅ እንዲያሰላስሉ ልታበረታታቸው ትችላለህ፡፡

## ማጠናከሪያ

የአለም አቀፉን ፀረ ዶፒንግ እና ኤጀንሲ የፀረ ዶፒንግ የካርድ ጨዋታ በወረቀት ላይ በማተም ተማሪዎች እነንዲጫወቱ ጋብዛቸው ተማሪዎች ኢንተርኔት የሚያገኙ ከሆነ የአለም አቀፉን ጸረ ዶፒንግ እና ኤጀንሲ ድህረ ገጽ አድራሻ በመጎብኘት በብዙ ቋንቋዎች የቀረቡ በስፖርት ውስጥ ሐቀኝነት ስላለው ሚና ተጨማሪ የትምህርት ግብአቶችን መጠቀም ይችላሉ፡፡

# ብሄራዊ የሐቀኝነት ስርአት

የትምህርት አይነት

- የስነ ዜጋ ትምህርት
- ስነ -መንግስት
- ታሪክ
- ቋንቋ እና ስነ- ጽሁፍ

**ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች**

11ኛ እና 12ኛ ክፍል 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

**የተመደበው ጊዜ**

40 ደቂቃ

**አስፈላጊ ቁሳቁሶች**

የወረቀት ሰሌዳ እና ማርከር

**ቁልፍ ቃላት**

- የሲቪክ ተግባራት
- ጾታ
- የሐቀኝነት ስርአት
- ሰብአዊ መብቶች

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ጨምሮ የተለመዱ የሲቪል ማህበረሰብ አባላትን ተማሪዎችህ እንዲዘረዝሩ ጠይቅ

## ማጠናከሪያ

ከአንድ ብሄራዊ ስርአት አንድ ወኪል በመጋበዝ ሐቀኝነትን በማህበረሰቡ ውስጥ ለማጠናከር ያላቸውን ሚና እንዴት እንደሚያዩት ጠይቅ፡፡

## የትምህርቱ ውጤት

ሐቀኝነት እና ጽንሰ ሃሳቦችን መገንዘብ (መረዳት)

## ምክንያት (RATIONALE)

በዚህ መልመጃ ተማሪዎች የሕዝባዊ ሐቀኝነት (public integrity) ጽንሰ ሃሳብን የተመለከተ ጠቅለል ያለ ዳሰሳ (እይታ) ይቀርብላቸዋል ፣ ተቋማት ለብሄራዊ ሐቀኝነት የሚያበረክቱትን ቁልፍ አስተዋጽኦዎች እና አጠቃላይ የነገርን ሐቀኝነት የሚጠብቁበት እና የሚገነቡባቸውን መንገዶች ይለያሉ፡፡

## ሒደት

1. ተማሪዎቹን በማህበረሰብ ውስጥ ለሐቀኝነት አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ተቋማትን እንዲዘረዝሩ ጠይቅ፡፡
2. ተማሪዎችህን የቤት ስዕል እንዲስሉ ካደረግክ በኋላ እንዴት አውራጆችና አግዳሚ (Beam) ቤትን በሕብረት እንደሚያቆሙ ጠይቃቸው፡፡
3. ተማሪዎችህ ለተቋማት ያላቸውን ጥንካሬ እና ዜጎች ለነሱ ያላቸው ክብር የሚመነጨው ከሚከተሉት መሃል ከየትኛው እንደሆነ ጠይቃቸው ፣ ከሰራተኞቻቸው? ከስራቸው? ከሚከተሉት ሂደት?
4. ተማሪዎች የብሄራዊ ሐቀኝነት ስርአት የሚወክል የቤት ሞዴል እንዲገነቡ ወይም እንዲስሉ አድርግ እንዲሁም የቤቶቹ ምሰሶዎች እያንዳንዳቸው ከላይ የተጠቀሱትን ተቋማት እንደሚወክሉ ንገራቸው፡፡
5. ከምሰሶዎቹ መሃል አንዱ ሚናውን ባይወጣ ምን እንደሚከሰት ጠይቃቸው፡፡
6. የሚቀጥለውን ሰንጠረዥ ለክፍሉ አጋራ ፣ (እንደየ አገሩ የመንግስት አወቃቀር ማስተካከያ ሊያስፈልገው ይችላል) ቀጥሎም የተዘረዘሩት ተቋማት ስራዎች ምን እንደሆነ ተማሪዎቹን ጠይቅ (የማያውቁ ከሆነ የተቋማት ዝርዝር አዘጋጅ ከዚያም ለብቻው ሌላ የተግባር ዝርዝር በማዘጋጀት ተቋማቱንና የተግባር ዝርዝሩን እንዲያዛምዱ ጠይቃቸው)
7. ተማሪዎችህን አንድ የሕብረተሰብ አካል (ለምሳሌ፡- ሴቶች) በእነዚህ ተቋማት እንዳይሳተፍ ወይም ከተቋማቱ ጋር እንዳይገናኙ ቢደረግ በሐቀኝነት ስርአቱ ጥንካሬ ላይ ስለሚያስከትለው ተጽእኖ እንዲያስቡ ጠይቃቸው፡፡
8. ሴቶች ወይም ሌሎች የተጎዱ የማህበረሰብ ክፍሎች በተቋማቱ እንዳይሳተፉ ወይም ግንኙነት እንዳይኖራቸው ምክንያት የሚሆኑ አካሄዶች ፣ ስርአቶች ወይም ጉዳዮች ምንድን ናቸው ብለህ ጠይቅ፡፡

| ተቋማት | በብሔራዊ ስርአቱ ምን ይዟል? | ሐቀኝነት እንዴት አስተዋጽኦ ያበረክታል? |
|---|---|---|
| ሕግ አውጭ | ፓርላማ/ኮንግሬስ/ሴኔት | ሕግ ያወጣል በዚህም የሕግ የበላይነት እና ብሔራዊ ሐቀኝነት ያግዛሉ |
| ሕግ አስፈጻሚ | ልዩ ልዩ የሚኒስቴር መ/ቤቶች | ደንብ ያረቃሉ መንግስት ወጭ ላይ ውሳኔ ያስልፋሉ |
| የሕግ ተርጓሚ | ፍርድ ቤቶች | ህግ መጣስ ያለመጣሱን ይወስናሉ የጣሱት ላይ ቅጣት ይወስናሉ፡፡ በዚህም የህግ የበላይነትን እና ብሄራዊ ሐቀኝነትን ያረጋግጣሉ፡፡ |
| ተቆጣጣሪ ኤጀንሲዎች | Pየመንግስት ሂሳብ ተቆጣጣሪ ኮሚቴ ፣ ኦዲተር ጀነራል ፣ እንባ ጠባቂ (ኦምዱስማን) | መንግስት ሕግን ተከትሎ እየሰራ መሆኑን ይከታተላሉ፡፡ መንግስት ሕግ ጥሶ ከሆነ ለሕዝብ ያሳውቃሉ፡፡ |
| የሕዝብ | የመንግስት ሰራተኞ | የሕግ አስፈጻሚውን ውሳኔዎችና እቅዶች ይተገብራሉ፡፡ |
| ሚዲያ አገልግሎት | ቲቪ ፣ራዲዮ ፣ጋዜጦች ፣ማህበራዊ ሚዲያ ካምፓኒዎች | በማህበረሰብ ውስጥ ሐቀኝነትን በተመለከተ ዘገባ ያቀርባሉ በመሆኑም ዜጎች በመረጃ ላይ ተመስርተው ድምጽ ይሰጣሉ (ይወስናሉ) |
| ሲቪል ማህበረሰብ (ማህበራት) | ሁሉም ዜጎች (ጾታ ፣ እድሜ ፣ ዘር ሳይለይ) ብዙውን ጊዜ በመንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ታቅፈው (ተደራጅተው) | ሁሉም የማህበረሰብ አምዶች (ምሰሶዎች)የሚጠበቅባቸውን ማድረጋቸውን ይከታተላሉ ፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የተቃውሞ ሰልፍ እና የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻ በማደራጀት ለለውጥ ይታገላሉ፡፡ |
| የግል ሴክተር | የንግድ ድርጅቶች (ለባለቤቶቻቸው ትርፍ ለማስገኘት የተቋቋሙ) | የንግድ ድርጅቶች የሕግ የበላይነት እንዲከበር ይፈልጋሉ በመሆኑም ብዙ ጊዜ ሙስናን ለሚታገሉና ልማትን ለሚያበረታቱ ለልማት የሚታገሉ መንግስታዊ ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ |



# ከሐቀኝነት ገንቢ ድርጅቶች ጋር መስተጋብር መፍጠር

## የትምህርት አይነት

- ስነ ዜጋ ትምህርት
- ስነ መንግስት
- ታሪክ

## አላማ የተደረጉ ተማሪዎች

በታችኛው (9ኛ እና 10ኛ) እና በላይኛው ደረጃ ያሉ (11ኛ እና 12ኛ) 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

## የተመደበው ጊዜ

60 ደቂቃ

## አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ኢንተርኔት ወይም ቤተ መጽሃፍት

## ቁልፍ ቃላት

- የሲቪክ ተሳትፎ
- ጸታ
- ስርአት የሐቀኝነት ስርአት

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

የተቋማት ወኪሎችን ጠርቶ ለክፍል ተማሪዎች ንግግር እንዲያደርጉ መጋበዝ ወይም ተማሪዎች የመንግስት ተቋማትን እንዲጎኙ ማድረግ የተለመደበ ቢሆንም እነዚህ መርሃ ግብሮች የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ የተቋማቱ ተወካዮች ስላላቸው ግንዛቤና የሚኖራቸውን ጥያቄዎች ቀድመው እንዲያውቁ ማድረግ ይመከራል

## ማጠናከሪያ

ተማሪዎቹ ከጉብኝቱ ወይም ከተጋባዥ እንግዳው ጋር ከነበሩ ውይይቶች ተመስርተው የራሳቸውን ፕረዘንቴሽን ሊያዘጋጁ ይችላሉ፡፡

## የትምህርቱ ውጤት

ሐቀኝነትና ተያያዥ ጽነሰ ሃሳቦች መገንዘብ (መረዳት)

## ምክንያት (RATIONALE)

በዚህ መልመጃ ተማሪዎች ስለ ሕዝባዊ ሐቀኝነት እና ለብሔራዊ ሐቀኝነት ስርአት አስተዋጽኦ ስላላቸው ተቋማት ተግባርና አላማ ከተወካዮቻቸው ጋር በሚኖራቸው መስተጋብር አማካኝነት የጠለቀ እውቀት ያገኛሉ፡፡ ይህም ተማሪዎች ወደ ፊት ከእነዚህ ተቋማት ጋር እንዴት ግንኙነት መፍጠር እንዳለባቸው ግንዛቤ እንዲያገኙ ያግዛቸዋል፡፡

## ሒደት

1. መምህሩ ከተማሪዎቹ ጋር በመተባበር ሊፈጥሩት ለሚፈልጉት መስተጋብር ይመርጣሉ፡፡ ይህ ለክፍሉ የመጎብኘት እድል ሊፈጥርለት ይችላል ወይም ወደ ክፍል ሊመጣ የሚችል አለበለዚያም "በኦንላይን" ስብሰባ ሊሳተፍ የሚችል የተቋም ወኪል ለማግኘት እድል ይፈጥራል፡፡ እነዚህ ተቋማት ከሚከተሉት መሃል ሊሆን ይችላሉ፡፡ የብሄራዊ ፀረ- ሙስና አካል ፣ የሲቪል ማህበራት (ለምሳሌ:- የንግድ ድርጅት አመራሮች ሆነው ፀረ- ሙስና ጥረቶችን የሚደግፉ) የሕግ ተርጓሚ አካላት (ጠበቆች ፣ ዳኞች) እና ሚዲያ (ለምሳሌ:- ሙስና ላይ ሪፖርት የሚያደርጉ ጋዜጠኞች)፡፡
   ተማሪዎች የት/ቤቱን ቤተ መጻህፍት ወይም ኢንተርኔት በመጠቀም ስለመረጧቸው ተቋማት መሰረታዊ ተግባራትና ስለሚከተሏቸው ሂደቶች ሊያመጡ ይችላሉ፡፡ ሊያጠሯቸው ከሚፈልጓቸው መረጃዎች መሃል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡
   - የተቋሙ አድራሻ የት ነው?
   - ቅርንጫፍ ቢሮዎች አሏቸው፡፡
   - ምን ያህል ሰራተኞች አሉት?
   - የተቋሙ ተቀዳሚ አላማ ምንድን ነው?
   - መቼ ተመሰረተ?
   - ለመመስረቱ ምክንያት የሆነው ታሪካዊ ክስተት ምንድን ነው ? (ካለ)
2. መርሃግብሩ (event) እንደጸደቀ ተማሪዎች ለተቋሙ ተወካይ ቀድመው የሚላኩ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት አለባቸው፡፡ መምህሩ የሚከተሉትን ፣ናሙናዎች ለተማሪዎች ሊያጋራ ይችላል፡፡
   ሀ/ ለዚህ ድርጅት ለመስራት ያነሳሳዎት ምንድን ነው ? የድርጅቱ ማህበራዊ አላማ ምንድን ነው?
   ለ/በስራዎ ውስጥ ሐቀኝነት ያለው ሚና ምንድን ነው?
   ሐ/ የድርጅትዎ ስኬቶች ምንድን ናቸው? እርስዎም ሆነ ድርጅትዎ የገጠማችሁ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው?
   መ/ በዋናነት ከየትኛው ድርጅት ጋር ትብብር አላችሁ?
   ሠ/ከሐቀኝነት ጋር በተያያዘ በስራችሁ ውስጥ የተለመዱ ደረጃዎች (እርምጃዎች)ምንድን ናቸው?
   ረ/ በድርጅትዎ ውስጥ ወጣቶችን እንዴት ነው የምታሳተፉት?
   ሰ/ በተቋማችሁ ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ሴቶች፣ ወጣቶች እና ሌሎች የተገለሉ የማህበረሰቡ አካላት በንቃት እንዲሳተፉ ድርጅታችሁ የሚያረጋግጠው እንዴት ነው?
3. መምህሩ ወይም ከተማሪዎቹ አንድ ወጣት በተቋሙ ስራ ውስጥ የሚሳተፉባቸውን መንገዶች ለመለየት በተጋባዥ እና ተማሪዎቹ መካከል ውይይት ይመራል፡፡ ለዚህ ተግባር መምህሩ ቀድሞ ከተጋባዡ ጋር መነጋገር ሊያስፈልገው ይችላል፡፡



# ጾታና ሙስና

## የትምህርት አይነት

- ስነ መንግስት
- ታሪክ
- ሳይንስ

## ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

11ኛ እና 12ኛ ክፍል 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

## የተመደበው ጊዜ

40 ደቂቃ

## አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ምንም አያስፈልግም

## ቁልፍ ቃላት

- ጉቦ
- ሚዛናዊነት
- ጾታ
- ሰብአዊ መብቶች

## የትምህርቱ ውጤት

በሐቀኝነት ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተጽእኖ ያላቸውን ጉዳዮች መመርመር

## ምክንያት (RATIONALE)

በዚህ ተግባር ተማሪዎች ስለ እኩልነት ያለመኖር ፣ ሴቶች እንዴት በሙስና የበለጠ ሊጎዱ እንደሚችሉ ይለያሉ፤ እናም ይህን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶችን ይመረምራሉ፡፡

## ሒደት

1. መምህሩ ተማሪዎች "ጾታ" የሚለውን ቃል እና የተወሰኑ የሕብረተሰብ አካላት ላይ ሴቶች የህዝብ አገልግሎት ለማግኘት እንዴት እንቅፋት እንደሚገጥማቸው ጥናት እንዲያደርጉ በቤት ስራ መልክ ይሰጣል፡፡
2. ተማሪዎችም የጥናታቸውን ግኝት በክላስ ያቀርባሉ ከዚያም ከመምህሩ ጋር በአገር ወይም በአለም አቀፍ ደረጃ ባለው ማስረጃ የተመሰረተ የማብራሪያ ይኖራቸዋል፡፡ (ሰንጠረዥ 5ን ተመልከት)
3. ተማሪዎችን በቡድን ከመደብክ በኋላ ከታች ያለውን ምናባዊ ሁኔታ (ወይም ከቀን ቀን ሕይወታቸው ጋር ተቀራራቢ የሆነ) አቅርብላቸው ከዚያም በመቀጠል ያሉትን ጥያቄዎች እንዲወያዩባቸው እና ግኝታቸውን ለሁሉም ተማሪ እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

ተማሪዎች ጾታና ተያያዥ ቃላት ላይ በሚያደርጉት ጥናት ላይ እገዛ እንዲደረግላቸው መምህሩ በዩኔስኮ ድህረ ገጽ ላይ ያለውን ህትመት "Glossary? Understanding concepts around geneder equality and inclution in education" (ቃላት መፍቻ ፤በትምህርት ውስጥ የጾታ እኩልነት እና አካታችነት ዙሪያ ያሉ ጽንሰ ሃሳቦችን መረዳት)

## ማጠናከሪያ

ተማሪዎች በማህበረሰባቸው ውስጥ ያለ መዋቅራዊ መዛባትን (imbalance) እና እንዴት የተወሰኑ የማህበረሰብ ክፍሎች እንዲገለገሉ ሊያሳይ የሚችሉ ማስረጃዎችን እንዲለዩ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡ የተገለገሉ የህብረተሰብ ክፍሎችን ከሚወክል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት አንድ ባለሙያ በመጋበዝ በክፍል ውስጥ ገለጻ እንዲያደርግ ጋብዝ፡፡

በተጨማሪም ሴትና ወንድ ተማሪዎ ከጾታ ልምዶች (ደንቦች) እና ግዴታዎ ጋር የሚያያዙ ተግዳሮቶች እና እነዚህ ተግዳሮቶች በሰብአዊ መብቶች ላይ ያላቸው አሉታዊ ተጽእኖን እንዲረዱ የሚያስችላቸው የሚና ጨዋታ ላይ እንዲሳተፉ ላደረጉ ይችላሉ፡ ፡ ለዚህም UNODC GRACE publication, "Knowledge tools for academic and professionals. Module Series on Integrity and Ethics – Module 9: Gender Dimension of Ethics".የሚለው ሞጁል መነሻ ሊሆን ይችላል፡፡ ወይም ተማሪዎች እንዴትሙስና ተጎጂ የሆነውን የማህበረሰብ ክፍል (ለምሳሌ የአካል ጉዳተኞችን ዝቅተኛ በሆነ የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ) ተለየ ሁኔታ እንደሚያጠቃ በጥልቀት እንዲያሰላስሉ ልታበረታታቸው ትችላለህ፡፡

## ምናባዊ ሁነት (SCENARIO)

ወንድሟን ለመንከባከብ የ2ኛ ደረጃ ትምህርቷን ያቋረጠች ልጃገረድ እየባሰ የሚሄድ ከባድ የሆድ ህመም አጋጥሟታል፡፡መነሻው የጠጣችው ውሃ እንደሆነ ትጠረጥራለች፡፡ መንደሩ የውሃ መቅጃ ቢኖረውም የሰሞን ውሃው እንደበፊቱ የጠራ አይደለም፡፡ ይህ የጀመረው አንድ የውጭ ካምፓኒ ለአካባቢው የፓርላማ አባል ጉቦ ከፍሎ ጫካ መመንጠር ከጀመረ ጀምሮ ነው፡፡

በመንደሩ ክሊኒክ ቢኖርም ለአለፉት 5 ዓመታት ያህል ነርስ አልነበረውም፡፡በቅርብ የሚገነው ዶክተር በሳምንት አንድ ጊዜ ወደ ሆፒታል የሚመጣ ሲሆን ሆስታሉም የሁለት ቀን መንገድ የሚፈጅ እና መሄድ የሚቻለውም የአካባቢው ወንዝ በማይሞላ ጊዜ ብቻ ነው፡፡እዚያ ለመድረስም የሳምንት ደመወዝ ያክል ያስወጣል፡፡ይህም ሆኖ ሆስፒታሉ መድሃኒት ላይኖረው እንደሚችል ከኖረውም በጣም ውድ እንደሚሆ ታውቃለች፡፡

አክስቷ የህመሟ መነሻ የሰራችው ስራ(ጥፋት) እንደሆነና የፋርማሲ መድሃኒት ሊያሽላት እንደማይችል ይልቁንም የባህል መድሃኒት ትወስድ ዘንድ መከረቻት ነገር ግን ህመሙ ሊቆም አልቻለም፡፡ ከ6 ሳምንት በኋላ ልጅቷ ሞተች፡፡ ምክንያቱን ማወቅ የቻለ አልተገኘም፡፡

## ጥያቄዎች

1. በዚህ አገር ዝቅተኛ የጤና አገልግሎ ምክንያት የሚጎዳው የተኛው የህብረተሰብ ክፍል ነው?
2. ልጃገረድ ሕይወት አድን የጤና አገልግሎት ለማግኘት የገጠሟት እንቅፋቶች ምንድን ናቸው?
3. ሙስናና የሐቀኝነት ጉድለት እንዴት እነዚህን ሙስና ከፍሎች ሊያስከትሉ(ሊያመጡ) ይችላሉ?
4. ለምንድን ነው ድሆች ፣ ሴቶች ፣ አካል ጉዳተኞች ማንበብ እና መጻፍ የማይችሉ እንዲሁም መሰል የሕብረተሰብ ክፍሎች የሙስና ከፍተኛ ገፈት ቀማሾች የሚሆኑት? (በሙስና ምክንያት ከፍተኛውን ዋጋ የሚከፍሉት)
5. በዚህ ሃገር የምትኖር ቢሆን ይህ ነገር ከሌሎች ላይ እንዳይከሰት ምን ታደርግ ነበር?

ማስታወሻ:- እንቅፋቶቹ (መሰናከሎቹ) ጤና ፣ ትምህርት ፣ የትራንስፖርት መሰረታዊ ልማት እና ድህነትን ይጨምራል፡፡

### ሰንጠረዥ 5
### ጾታ እና የመሰረታዊ አገልግሎቶች ተደራሽነት እንቅፋቶች

ብዙውን ጊዜ ሴቶች ከመሰረታዊ የሕዝብ አገልግሎቶች አቅራቢዎች ጋር በሚኖራቸው ተራክቦ (መስተጋብር) የሙስና ሰለባ ይሆናሉ፡፡ሴቶች ከየትኛውም ሕብረተሰብ በበለጠ እንደ ትምህርት እና ጤና ያሉ መሰረታዊ የህዝብ አገልግሎቶች ላይ ጥገኞች ናቸው፡፡

የሚከተለው ዳታ (መረጃ) ሙስና በተነጻጻሪነት እንዴት የሴቶችን የመሰረታዊ አገልግሎቶች ተደራሽነትን በከፍተኛ መጠን እንደሚጎዳ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ማስረጃ ይሆናል፡፡ በ2001 በቦትስዋና በተከናወነ ጥናት መሰረት በጥናቱ የተካተቱ ሴቶች 67 % የሚሆኑት በወንድ አስተማሪዎቻቸው ወሲባዊ ትንኮሳ እንደደረሰባቸው ሲያሳውቁ 10 % የሚሆኑት ውጤታቸው (ግሬዳቸው) እንዳይጎዳ በመፍራት የወሲብ ግንኙነት ለማድረግ ፈቃደኛ ሆነዋል፡፡

ሌሎች ጥናቶች እንደሚያሳዩት ተማሪዎች በሚያረግዙበት ጊዜ ከትምህርት እንዲገለሉ ስለሚገደዱ የሚጎዱት (የሚቀጡት) እነሱው ናቸው፡፡

በኡጋንዳ በንግዱ ሴክተር የ2006 የአለም ባንክ ዳሰሳ መሰረት ምንም እንኳን ወንዶችንና ሴቶችን የመንግስት ባለስልጣናት ትንኮሳ ተጠቂ ቢሆኑም ፣ 43% የሚሆኑትን ሴት የንግድ ባለቤቶች የጥቃቱ ሰለባ ሲሆኑ ይህ በተነጻጻሪ 25 % አጠቃላይ የንግድ ሰዎች ጋር ሲወዳደር በጣም ከፍተኛ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡

**ምንጭ፡** United Nations Development Programme and United Nations Development Fund for Women, Corruption, Accountability and Gender: Understanding the Connections" (New York, 2010) (see chapter 1) and UNODC, The Time is Now: Addressing the Gender Dimensions of Corruption (Vienna 2020).

# ሰበብ (ምክንያት) መፍጠር?

## የትምህርት አይነት

- ስነ መንግስት
- ታሪክ
- ሳይንስ

## ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

በታችኛው (9ኛ እና 10ኛ) እና በላይኛው ደረጃ ያሉ (11ኛ እና 12ኛ) 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

## የተመደበው ጊዜ

45 ደቂቃ

## አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ምንም አያስፈልግም

## ቁልፍ ቃላት

- ጉቦ
- ሚዛናዊነት
- ጾታ
- ሰብአዊ መብቶች

## ማጠናከሪያ

ተማሪዎች የሐቀኝነት ፍርድ ቤት ሊመሰርቱ ይችላሉ። ተማሪዎች በቡድን ይከፋፈላሉ እያንዳንዱ ቡድን ወደ ንኡስ ቡድኖች "አቃቤ ሕግ "እና " የተከላለካይ ቡድን ይከፋፈላል":: አቃቤ ሕግና ተከሳሽ ይመረጣሉ:: " የተከላካይ ቡድን " ተከላካይ ጠበቃ ይመርጣል:: እያንዳንዱ ቡድን "በሐቀኝነት ላይ የተፈጸመ ወንጀል" ካርድ ይሰጠዋል:: (ለምሳሌ:- ስራ በዝምድና መቀጠር ከተፈቀደለት ፍጥነት በላይ በማሽከርከር የሚመጣ ቅጣት በጉቦ ማምለጥ) የአቃቤ ሕግ ሚና ተከሳሹን ሐቀኝነት በጎደለው ተግባር ጥፋተኛ ማስባል ሲሆን ተከሳሽ ወይም ጠበቃው ክሱን በመረጡት ሙግት መከላከል ነው:: ነገር ግን ተከሳሽ ስራህ የተባለው ተግባር እንደተከሰተ አምኗል ስለዚህ የቀረው ተከሳሹ በቂ ምክንያት አለው ያለውም የሚለው ነው: : ዳኞቹ ታዳሚዎቹ ናቸው::ተከሳሽ ጥፋተኛ ከተባለ ታዳሚዎቹ ለተፈጸመው ወንጀል ተመጣጣኝ የሆነ ጥፋትን የሚያርም እምጃ ያሉትን ሃሳብ ያቀርባሉ::

## የትምህርቱ ውጤት

ሐቀኛ የውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተጽዕኖ የሚያደርሱ ጉዳዮችን መመርመር

## ምክንያት (RATIONALE)

ይህ መልመጃ ሰዎች ስራዎቻቸውን በሐቀኝነት ለመፈጸም እና ሐቀኝነት የሚጎለው ምርጫ ሲመርጡ ከሚያቀርቧቸው ምክንያቶች መካከል የተወሰኑትን ይመረምራል::

## ሒደት

1. መምህሩ የአንድ ሰው ሐቀኝነት የጎደለው ድርጊት በምሳሌነት ያቀርባል (ለምሳሌ አንድ ሰው ስለ አካባቢው ደህንነት እንደሚቆረቆር ሲናገር ቆይቶ የመኖሪያ አካባቢውን በቆሻሻ የሚበክል ሲሆን)
2. ተማሪዎችህን ሰዎች እናደርጋለን ብለው ቃል የገቡትን ላለማድረጋቸው የሚያቀርቧቸውን የተለመዱ ምክንያቶች እንዲነግሩህ ጠይቅ አስፈላጊ ከሆነ መምህሩ ከትክክለኛ ክስተቶች ጋር የሚያያዙ ጥቂት ምሳሌዎችን ሊሰጥ ይችላል:: እና /ወይም ታች ተቀምጠው ሰንጠረዥ ውስጥ የተዘረዘሩትን ምክንያቶችን መጠቀም ይችላል::መምህሩ ተማሪዎቹን ሰዎች ትክክል ነው:: ብለው ከተናገሩት ነገር በተቃራኒው ስለሚፈጸሙበት (ስለሚተገበሩበት) ምክንያቶች እንዲያስቡ ያበረታታል:: እንዲሁም ከነዚህ ምክንያቶች መካከል የትኞቹ ተቀባይነት እንደሌላቸው እንዲያሰላስሉ አሳስብ::
3. ተማሪዎህን ሰንጠረዥ (ከታች እንደተቀመጠው) ሰርተው እንዲያሰፍሩ አድርግ እንዲሁም ምክንያቶቻቸው ከ1-5 የተቀባይነት ደረጃ እንዲያወጡላቸው አድርግ:: በዚህ መሰረት 5 ፈጽሞ ተቀባይነት የሌላቸው ስለመሆኑ ያመለክታል: : ተማሪዎች አንድን ምክንያት ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ ያመለክታል:: ተማሪዎች አንድን ምክንያት ተቀባይነት እንዲኖረው የሚያደርግ የተለየ ሁኔታ አለ ብለው ካመኑ ይህንኑ በሶስተኛው አምድ እንዲመዘግቡ ንገራቸው:: በአራተኛው አምድ ምክንያቱን ተቀባይ የሚያደርገው ልዩ ሁኔታን ወይም የቀረበው ተቀባይነት ለምን እንደሌለው ያስፍሩ::
4. ቀጥሎ መምህሩ ከተማሪዎቹ ጋር የተማሪዎቹን መልሶች የሚያስተያዩበት በእነርሱም ላይ ውይይት የሚያደርጉበትና የተገኘውን ትምህርት የሚለዩበት አጠር ያለ የውይይት ክፍለ ጊዜ ያዘጋጃል::

| ምክንያት | ደረጃ | ማብራሪያ | ነገር ግን… |
|---|---|---|---|
| በጣም ስራ በዝቶብኛል እናም አቋራጩ ያግዛል | | | |
| ምርጫ አልነበረኝም | | | |
| ሁሉም የሚያደርገው ነገር ነው | | | |
| እኔ የማደረገው ነገር የሚለውጠው ነገር ለውም | | | |
| ተገቢ ያልሆነውን ነገር የማደርገው አሁን ብቻ ነው ከዚህ በኋላ ፈጽሞ አላደርገውም | | | |
| ይህን ማድረግ ለደህንነት አስተማማኝ አይደለም | | | |
| ባህላችን ነው | | | |
| ብዙ ሰው ከእኔ የከፋ ነገር ያደርጋል | | | |

# ግን እኮ ምንም አልሆነኩም (But I am OK)

### የትምህርት አይነት

- ስነ ጥበብ (ቲያትር)
- የስነ ዜጋ ትምህርት

### ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

9ኛ እና 10ኛ ክፍል 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

### የተመደበው ጊዜ

35 ደቂቃ

### አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ምንም አያስፈልግም

### ቁልፍ ቃላት

- ሙስና
- ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ
- ሰብአዊ መብቶች
- ሀላፊነት

## የትምህርቱ ውጤት

ከሰዎች ልጆች ጋር ይወግንና መንፈስ (የእኔነት ስሜት) እና ለሐቀኝነት ሃላፊነት መስማትን መጋራት፡፡

## ምክንያት (RATIONALE)

ተማሪዎች ሙስናና የሐቀኝነት አለመኖርን ሌሎችን ብቻ የሚጎዳ ችግር እንጂ እነሱን የማይነካ ቢያንስ በቅርብ ጊዜ አድርገው ሊያዩት ይችላሉ፡፡ ይህ መልመጃ ተማሪዎች የሐቀኝነት ጉድለት እነርሱን ጨምሮ ሁሉም ላይ አስከፊ ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል እንዲገነዘቡ ያግዛል፡፡

## ሒደት

1. የሚከተለውን ታሪክ መንጃ ፈቃድ ማውጣት ይፈልጋል፡፡ የአጎትህን መኪና በመንደር አካባቢ ባለ ባዶ መንገድ ላይ ከነዳ በኋላ መንዳት እንደሚችል እርግጠኝነት ተሰማው፡፡ ይህ መተማመን ያደረበት ምንም አይነት ተገቢ የማሽከርከር ስልጠና የክፍል ውስጥ ትምህርትና ልምምድ ሳያደርግ ነው፡፡ በመቀጠልም ፈተና ሳይወስድ ጉቦ በመክፈል ፈቃዱን ወሰደ፡፡ በሚቀጥለው ቀን ከት/ቤትህ አካባቢ አደጋ መድረሱን ሰማህ፣ የአጎትህ ልጅ የትራፊክ መብራት በመጣስ መንገድ በማቋረጥ ላይ የነበረን ወንድምህን ከፉኛ አቆሰለው፣ ወንድምህ ጉዳት የደረሰበት አንተም ለከፍተኛ ድንጋጤ እና ሀዘን ተዳረግክ።
2. ተማሪዎቹን የሚከተሉትን ጥያቄዎችን ጠይቅ:
   ሀ/ ይህን ሁሉ ከመከሰት ምን ሊያስቆመው ይችል ነበር?
   ለ/ ለዚህ ሁሉ ሀላፊነት ማን ሊወስድ ይገባል?
   ሐ/ ምን ማድረግ ትችል/ትችይ ነበር?
3. ተማሪዎችህን ሰዎች ስራቸውን በሐቀኝነት የሚያከናውኑ ከሆነ የትኛው የእለት ከእለት ህይወታቸው ገጽታ ወደ ሀዘን ሊቀይር እንደሚችል እንዲያሰላስሉ አሳስብ፡፡

   ከግምት ሊገቡ የሚችሉ ሃሳቦች ለምሳሌ:
   ሀ/ የኤሌክትሪክ መስመሮችና ደህንነት(በኤሌክትሪክ ልትያዝ ትችላለህ)
   ለ/ የአውቶብስ አውታሮች እና መርከቦች ደህንነት(የአውሮፕላን ፍሬኖች አልተፈተኑም)
   ሐ/ የህዝብ ገንዘብ በጤና ላይ ማዋል (ዶክተሩ ተፈላጊውን የሙያ መመዘኛ አለሟላም)
   መ/ የህዝብ መገልገያ ቦታዎች ደህንነት (ሕንጻ ተደረመሰ)
4. ተማሪዎች በቡድን ሆነው ጎጅ ውጤት ሊያስከትሉ ይችሉ የነበረ ከዚህም በፊት ተቀብለዋቸው የነበሩ የራሳቸውና የሌሎች ልምዶችን (ተግባራት)እንዲለዩና በነሱ ላይም እናዲወያዩ ያድርጉ፡፡ አሁን ለተመሳሳይ ባህሪ ተባባሪ ያሆናሉ? ለምን?
5. ተማሪዎቹ የቡድን ውይያታቸው ለአጠቃላይ ተማሪዎች (ክፍሉ)ሪፖርት እናዲያደርጉ ጠይቅ፡፡

## ማጠናከሪያ

ተማሪዎች ሐቀኛ ውጤት አሰጣጥ በማይኖርበት ጊዜ አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ የዕለት ተዕለት ክስተቶች ማሳሌዎችም በድራማ መልክ እናዲያቀርቡ ማድረግ፡፡



# የሐቀኝነት ምልክቶች

## የትምህርት አይነት

- ታሪክ ፣ቋንቋ ፣ ስነፅሁፍ ፣ስነ-ዜጋ ትምህርት የመረጃ ቴክኖሎጂ ስነ ጥበብ

## ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

የላይኛው (11ኛ እና 12ኛ) እና ታችኛው (9ኛ እና 10ኛ) 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

## የተመደበው ጊዜ

2 x 60 ደቂቃ

## አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ኢንተርኔትና ኮምፒውተሮች

## ቁልፍ ቃላት

- የሲቪክ ተሳትፎ ስነምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ
- ሰባአዊ መብቶች

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ አውደ ራዕይ በማዘጋጀት ስራቸውን ማቅረብ ይችላሉ፡፡ ይህን በማድረግም ስራቸው ለክፍሉ ተማሪዎች በሞላ ማሳየት እና ለሚያነሱት ጥያቄዎች መልስ መስጠት ይችላሉ፡፡ አቅረቡ በፅሁፍ መልክ ሊሆን ይችላልወያነሱት ጥያቄዎች መልስ መስጠት ይችላሉ፡፡ አቅረቡ በፅሁፍ መልክ ሊሆን ይችላል ወይንም የተወሰነው በተለየ መንገድ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ለምሳሌ:-በንግግር መልክ ፣ያቀረቡ ተማሪዎች ቀጥለው ሙዚቃ ፣ስዕል ወይንም ድህረ ገጽ ሊፈጥሩ ይችላሉ

## ማጠናከሪያ

ቀደም ሲል ከተብራሩት ስብዕናዎች ውጭ፣ በህዝባዊ መንገድ ንጹሕ አቋማቸውን ለመጠበቅ መስዋዕትነት ከፍለዋል ብለው የሚያስቡትን ሰው ተማሪዎች እንዲለዩ ጠይቋቸው። ተማሪዎች ታሪካቸውን የሚገልጹበት ቪዲዮ፣ ተንሸራታች ትዕይንት ወይም የታሪክ መጽሐፍ ያዘጋጁ። ሲጨርሱ ተማሪዎች ስራቸውን ከነሱ ለምያንሱ ተማሪዎች ያቅርቡ። ይህንን እንዴት ለማድረግ እንደሚቻል ምሳሌዎች በ Step Up ናይጀሪያ መጽሃፍ, የሃሊማ ድምጽ ውስጥ ይገኛሉ።

## የትምህርቱ ውጤት

ከሰው ልጆች ጋር የውግንና መንፈስ (የእኔነት ስሜት) እና ሐቀኝነት የህላፊነት ስሜት መሰማትን ማጋራት፡፡

## ምክንያት (RATIONALE)

ይህ መልመጃ ተማሪዎች ለሐቀኝነት ሲሉ ነጻነታቸውንና ደህንነታቸውን አደጋ ላይ እየጣሉ የሰዎችን ህይወት ለመመርመር እድል እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

## ሒደት

1. ለተማሪዎች የተለያዩ ከሀገር ውስጥና በአለም አቀፍ ደረጃ ለእሴታቸው በመታመን ሐቀኛ ህይወትን የመሩ ሴቶች እና ወንዶች በምሳሌነት አቅርብ፡፡ ለነዚህ ምሳሌዎች ምንጭ ሊሆኑ ከሚችሉ መሀል የሚከተሉት ይገኙበታል:-
   ሀ/ በአካባቢ የሚገኙ ሚዲያዎች
   ለ/ በት/ቤቱ ወይም በአካባቢ የህዝብ መፅሀፍ ቤት ውስጥ የሚገኙ የታዋቂ ሰዎች ግለ - ታሪኮች (የሕይዎት ታሪኮች)
   ሐ/ የሐቀኝነት ተምሳሌቶች (ምልክቶች) ድረ-ገጽ የሐቀኛ ሰዎችን ታሪክ የያዙ ቪዲዮዎች ሊንክ የያዘ ሲሆን ሰዎቹም ከሚከተሉት አገሮች የተውጣጡ ናቸው፡፡ የኮንጎ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ ፣ ላይቤሪያ ፣ ማሊ ፣ ሜክሲኮ ፣ ኔፓል ፣ ኒጀር ፣ ናይጀሪያ፣ ፓኪስታን ፣ ሱማሊያ ፣ ሲሪላንካ ፣ ደቡብ አፍሪካ ፣ ዩክሬን ፣ ዩ ኤስ ኤ እና ዚንባቡዌ፡፡ ለእያንዳንዱ በአገራቸው ቋንቋ የተነገሩ ታሪኮችን ታገኛላችሁ፡፡
   መ/ የ Allard prize ድረ ገጽ ላይም ከመላው አለም የተውጣጡ ሐቀኛ ተግባራት የፈጸሙ ሰዎች ታሪክ ይዟል፡ ፡ ቪዲዮዎቹ በእንግሊዝኛ ብቻ ቢሆኑም ጽሁፎቹ በቻይንኛ ፣ በእንጊሊዝኛ ፣ ፈረንሳይኛ ፣ ጀርመንኛ ፣ ሮማንኛ ፣ ራሺያኛ እና በእስፓኒሽኛ ቀርበል፡፡
   ሠ/ የትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ህትመት "Real Lives : true stories"(እውነተኛ ሂወቶች ፣ እውነተኛ ታሪኮች)
   ረ/ የUS Development of states (ዩኤስ የውጭ ጉዳይ መ/ቤት) " Recognizing the 2021 Anti- corruption champions" (የ 2021 ጸረ- ሙስና ሻምፒዮናዎች የተሰጠ እውቅና)
   ሰ/ የናይጀሪያ ጸረ- ሙስና ኮኮቦች ሽልማት (step-up Nigerian " Anti- corruption star Awards")
   ሽ/ "Anti- corruption Awards"ና " Integrity Awards " የሚሉ ቁልፍ ቃልን ተጠቅሞ የኢንተርኔት ፍለጋ ማከናወን እና የአገር ውስጥ እና አለም አቀፍ ድርጅቶች ድረገጾችን ማማከር፡፡
   ቀ/ በማሕበረሰቡ የሚገኙ ሰዎች
   በ/ ታሪካዊ የባህል እና የሃይማኖት ታዋቂ ሰዎች፡፡
2. ተማሪዎች እንደ ሰው እንዲመርጡ እና የሚከተሉትን ነጥቦች የሚሸፍን የ 5 ደቂቃ ገለጻ (ፕረዘንቴሽን) እንዲያዘጋጁ ጠይቅ (የተዘረዘሩትን ነጥቦች ብቻ እንዲከተሉ ወይም ቅደም ተከተሉን እንዲጠብቁ አይገደዱም)፡፡
   ሀ/ ሰዎቹ የተገኙት ከየት ነው ? ታሪኩ ምን ይመስላል ?
   ለ/ ሊፈቱት የሞከሩት ችግር ምንድን ነው ?
   ሐ/ አርፈው ከመቀመጥ (ዝም ከማለት) ይልቅ የሆነ ነገር ለማድረግ የወሰኑት ለምንድን ነው ?
   መ/ አላማዎቹ ምንድን ናቸው?
   ሠ/ የገጠሙ መሰናክሎች /ችግሮች / ምንድን ናቸው?
   ረ/ አላማዎቹን ያሳካው እንዴት ነው?
   ሰ/ ይህ ሰው ያነሳሳህ (ጠንካራ ፍላጎት ያሳደረብህ)ለምንድን ነው ?
3. ተማሪዎችን በየ ሃገራቸው ለውጥ ያመጡ ታዋቂ ሰዎችን እና ሙስናን በቆራጥነት የተቃወሙ (ለምሳሌ፡- ጉቦ ባለመስጠት ወይም ባለመቀበል) ተራ ሰዎችን እኩል ማክበር እና ማድነቅ ያለብን ለምንድን እንደሆነ ጠይቃቸው፡፡[1]

ማስታወሻ፡ ገለጻው (ፕረዘንቴሽኑ)በፖስተር ፣ በንግግር ፣ በቪዲዮ ፣ በቃለ መጠይቅ ፣ በስላይድ ሾው ፣ በወግ (essay) ወይም በማቀላቀል ሊሆን ይችላል፡፡ ስራውም በቡድን ወይም በጥንድ ሊሰራ ይችላል፡፡

1 የተመድ ጸረ-ሙስና ስምምነት (UN convertion against corruptions) አንቀጽ 15 ጉቦን" አንድ የመንግስት ባለ ስልጣን የተሰጠውን የስራ ሃላፊነት እንዲፈጽም ወይም እንዲያስፈጽም ለማድረግ ተብሎ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለእሱ ወይም ለእሷ ወይም ለሌላ ሰው ወይም ለሌላ አካል ለመስጠት ቃል መግባት ለስጦታ ማቅረብ ወይም መስጠት ማለት ነው" ተብሎ ተተርጉሟል፡፡

# ከተመልካችነት(ታዛቢነት) ወደ ረዳት አጋዥነት

### የትምህርት አይነት

### ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

የላይኛው (11ኛ እና 12ኛ) እና ታችኛው (9ኛ እና 10ኛ) 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

### የተመደበው ጊዜ

40 ደቂቃ

### አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ምንም አያስፈልግም

### ቁልፍ ቃላት

- የሲቪክ ተሳትፎ
- ሌሎች እንደራስ ለመረዳት መጣር (EMPATHY)
- ስነ -ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ
- ጾታ
- ኃላፊነት

### ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

ይህ መልመጃ ተማሪዎች ለሲቪክ ተግባራት ያሉ አማራጮችን የሚያውቁ ሲሆን ተስማሚ ይሆናል፡፡ (ለምሳሌ፡- የማህበራዊ ሚዲያ ዘመቻዎችና የጎዳና ተቃውሞ)፡፡

በዝቅተኛ እርከን ላይ ላሉ ተማሪዎች ግላዊ ሐቀኝነት ላይ በማትኮር ሁኔታዎቹን የማያስተካል ሊሆንበት ይችላል፡፡

### የትምህርቱ ውጤት

ለሰው ልጆች ወገንተኝነት መንፈስ (ስሜት)እና ለሐቀኝነት የሚኖር የሃላፊነት ስሜት፡፡

### ምክንያት (RATIONALE)

ይህ መልመጃ ተማሪዎች የሞራል አጣብቂኝ (Ethical Dialemma) ሲያሰጥማቸው ለመረዳት ውይም ያለመርዳት ስላላቸው ምርጫ እንዲያስቡ እና እነዚህ አማራጮች በግለሰብ ፣በማህበረሰብ ፣በክልል እና በአገር ደረጃ ያላቸውን እንዲዳስሱ ያደርጋቸዋል፡፡

### ሒደት

1. መምህሩ ለተማሪዎቹ አውድ የሚስማማ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች መርጦ ይሰጣል፡፡ (ማስታዎሻ፡- የተወሰኑት በተሸለ ከግላዊ ሐቀኝነት ጋር የሚሄዱ ሲሆን የተቀሩት ከማህበረሰባዊ ሐቀኝነት ጋር የሚስማሙ ናቸው፡፡)

   ሁኔታዎች (scenarios):
   አንድ የክፍል ጓደኛህ የፈተና ወረቀቱን ቀድሞ እንዳገኘ ሰማህ

   የክፍልህ ሴት ተማሪዎች በወንድ አስተማሪህ ትንኮሳ እየደረሰባቸው መሆኑን ሰማህ

   አንድ ትልቅ ሰው የሸመቱትን እቃ ለመሸከም እየታገሉ (ሲቸገሩ) ታያለህ

   የሰከረ ዘመድህ የሴት ጓደኛውን የሃይል ጥቃት ሲያደርስባ ትመለከታለህ፡፡

   የምትሳተፍበት እስፖርት ውስጥ ዳኛው በሻምፒዮን ጨዋታው ከሌላው ቡድን ጉቦ እንደተቀበለ ትሰማለህ፡፡

   ምንም እንኳን የተሸለ ሃሳብ እና ፖሊሲ ያላቸው እነሱ ቢሆኑም ሴት እጩዎች እየተደመጡ እንዳልሆነ ትታዘባለህ፡፡

   በመንግስት ም/ቤት ውስጥ አንድ ግለሰብ ለመስሪያ ቤቱ ሰራተኛ ጉቦ ሲሰጥ ታያለህ፡፡

   ስለ አንድ ሚሊየኖች ሳልሰረቀ ባለስልጣን እና ይህን ስላጋለጠው ጋዜጠኛ እስር ቤት መግባት አነበብክ፡፡

   በአገርህ ያሉ የሌላ ሃይማኖት ዜግነታቸውን እንደሚነጠቁ እና በዚህም የተነሳ የመምረጥ መብታቸውን እና የመንግስት አገልግሎት የማግኘት መብታቸውን እንደሚያጡ አነበብክ፡፡

2. ቀጥሎ ተማሪዎች ጥንድ ጥንድ እየሆሙ ይወያዩ
   ሀ. እንደ የህብረተሰብ አባልነታቸው እና የአገር ዜጋ መሆናቸው የሆነ እርምጃ መውሰድ" ሃላፊነት" ወይም" ግዴታ" እንዳለባቸው
   ለ. በዝምታ የሚመለከቱ (የሚታዘቡ) እንደሆነ ወይም እነዚህን ችግሮች ለመፍታት እገዛ ያደረጉ እንደ ሆነ (መምህሩ መርዳት ማለት ወዲያውኑ ጣልቃ መግባት ማለት እንዳልሆነ እና ወደ ኋላ ላይ ሊደረግ እንደሚችል መግለጽ አለበት)
   ሐ. አጋዥ ከመረጡ ምን አይነት ተግባር እንደሚፈጽሙ ተመልካችነትን ከመረጡ ለዚህ ምክንያቶቻቸው ምን እንደሆነ

3. መምህሩ የተማሪዎቹን ውሳኔ በጠቅላላ ተማሪዎች ውይይት ጊዜ እዲያጋru ይጠይቃቸዋል፣ የሆነ እርምጃ እንዲወስዱ የሚያስገድድ ጫና ባለመኖሩ አብዛኞቹ ጣልቃ እነገባለን ማለታቸው ከፍ ያለ ነው፡፡ በውይይት ወቅት ይህ ምርጫ ሊፈተን ይችላል፡፡ በእውነተኛ ሁኔታ ውስጥ ምን ሊያደርጉ ይችላሉ? እንዴት ውጤታማ በሆነ መንገድ ጣልቃ ሊገቡ ይችላሉ?

### ማጠናከሪያ

ተማሪዎች በጥልቀት እንዲያነቡ የሚከተሉትን አይነት ተጨማሪ ጥያቄዎች መጠየቅ ይመለከታል፡፡አጋዥ ከመሆን ይልቅ ተመልካች መሆን ውጤቱ ምን ይሆን? በተለይም ሁላችንም ተመልካች ከሆንን? ይህ እንዴት ሌሎችን እና ማህበረሰቡን ሊጎዳ ይችላል? አንዳንዶች እንዳያግዙ (እንዳይረዱ) መሰናክል የሚሆኑባቸው ነገሮች ምንድን ናቸው? እነዚህን መሰናክሎች (እንቅፋቶች) እንዴት ልናስወግዳቸው እንችላለን?



# የግጭት አፈታት(አያያዝ)

## የትምህርት አይነት

- ታሪክ
- ቋንቋ እና ከስነ ጽሁፍ
- የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት አላማ የተደረጉ

## አላማ የተደረጉ ተማሪዎች

ዝቅተኛ (9ኛ እና 10ኛ) እና ከፍተኛ (11ኛ እና 12ኛ) ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

## የተመደበው ጊዜ

60 ደቂቃ

## አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ምንም አያስፈልግም (ምንአልባ ማርከር እና ቀለም ለማጠናከሪያ መልመጃዎች)

## ቁልፍ ቃላት

- ግጭት
- ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

ተማሪዎች የወቅቱን የአካባቢ ፣ የአገር እና የአለም አቀፍ ግጭቶችን ሊመለከቱ እና አመለካከቶችም ሊገለጹ ፣ ሊወስድ የሚችለው ርምጃ እና እነዴት ግጭቶቹ ሊፈቱ እንደሚችሉ ሊያስቡ ይችላሉ፡ ፡ በተጨማሪም በሰላምና ግጭት የሚመለከቱ ጥቅሶችን በመፈለግ ጥቅሶቹን ትርጉም የሚያስረዳ የስነ ጥበብ ስራ ሊፈጥር ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ፡- ይህ የደሮቺ ቶምሰን ጥቅስን" ሰላም የግጭት ያለመኖር ማለት ሳይሆን ግጭትን ለመፍታት ብለህ (creative)"አማራጮች መኖር ማለት ነው፡፡ ለፓሲቭ ወይም አገርሲቭ(ተንኳሽ) ምላሾች አማራጭ ፣ ሃይል ለተሞላበት ምላሽ አማራጭ" እና ይህኛው ከጋንዲ አይን ለአይን መላውን አለም ስውር ያደርጋል፡፡ ትርጉማቸውን የሚገልጽ የስነ-ጥበብ ስራ ሊያዘጋጁ ይችላሉ፡፡

## የትምህርቱ ውጤት

ለሰው ልጆች የወገንተኝነት (የኔነት)ስሜት እና ለሐቀኝነት የሚኖር የሃላፊነት ስሜት

## ምክንያት (RATIONALE)

ሙስና ማስቀምና ሐቀኝነትን መደገፍ ወደ ግጭት ሊመራ ይችላል፡፡ በዚህ መልመጃዎች በድጋፍ እና ሰጥቶ በመቀበል ግጭትን በሰላም የሚፈታበትን ሂደት ይለያሉ፡፡

## ሒደት

1. ተማሪዎቹን በቡድን በመከፈል በየቡድናቸው የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ጠይቅ:
   ሀ/ ግምት የሚለውን ቃል ትርጉም እና መነሻዎች ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮችን ግለጹ፡፡
   ለ/ ሁሉም አይነት ግጭቶች መወገድ እንዳለባቸው ወይም የተወሰኑ አይነት ግጭቶች ብቻ ሊወገዱ ይገባ እንደሆነ ተወያይ
   ሐ/ የግጭቶች ቁልፍ ደረጃዎችን ከነምሳሌያቸው ለዩ
   መ/ ግጭቶች ሐይል የቀላቀሉ ወይም ከብር የሚነኩ የሚሆኑበት ምክንያቶችን ለዩ፡፡
   ሠ/ አንዳንድ ጊዜ እንደተሳሳትን (ልክ እንዳልሆን) ማመን የማንፈልግበት ምክንያት ተወያዩ
   ረ/ ግጭቶችን እንዴት መፍታት እንዳለብን ተወያዩ
2. ተማሪዎች በየምድባቸው ከሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ አንዱን በሚና እንዲጫወቱ ጠይቃቸው፡፡ሁለቱንም ሚና በማቀያየር በመጫወት ከሁለቱም አኳያ ያለውን ሁኔታ እንዲያሳዩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ስለዚህ አንዱ ቡድን ሁኔታውን ከአንዱ ግለሰብ አንጻር ከተጫወተ ቀጣዩ ቡድን ሁኔታውን ከአንዱ ግለሰብ አንጻር መጫወት ይኖርበታል። (የክፍሉ መጠን ከፍ ያለ ከሆነ ተጨማሪ የግጭት ምሳሌዎች ያስፈልጋል ታዳሚዎቹ ምልሾቹ ምን ያህል እውነታን የሚያንጸባርቁ መሆናቸውን እና ከባህል እምነት ወይም እሳቤ የመነጩ መሆን ያለመሆናቸውን ሊያሰላስሉ ይችላሉ።)

## ሁኔታዎች (SCENARIOS)

ሀ/ አንድ የA ቡድን (የእግር ኳስ ቡድን) ተጨዋቾች ኳስ የሜዳውን መስመር አቋርጣ ከወጣች በኋላ ወደ ሜዳው እንደተመለሰች ያምናል፡፡ ኳሷን መጨረሻ የነካው የB ቡድን ተጫዋቾች መስመሩን ነካች እንጂ አላቋረጠችም የሚል እምነት አለው፡፡
ለ/ ፖስታ ቤት ተሳትፎ የነበረው A አብረውት የተሰለፉትን ሰዎች ቦታውን እንዲይዙሉት ተናግሮ ወደ መጸዳጃ ቤት ይሄዳል፡፡ከኋላ ተሰልፎ የነበረው B ፣A ወደ ቦታው ሲመለስ ተሰልፍ ለምን ሰልፍ ጣስከ በማለት ተናደደ
ሐ/ A የተባለው ጉሳ አንድ የውጭ ካምምፓኒ የብሄሩን ጫካ እንዲመነጥር እና ግንዶቹን ወደ ውጭ ገበያ እንዲያቀርብ ቢፈልግም የባህር ዳርቻውን አይቆጣጠርም፡፡ የተመሳሳይ ብሄር አባል የሆነው‹A ፡ B የሚባለውን ጎሳ የባህር ዳርቻውን የሚቆጣጠር ሲሆን መሬቱን ለእንግዶች ወደ ውጭ ገበያ መውጣት አይፈቅደም ምንክያቱም የደን ምንጠራን ይቃወማልና ነው፡፡

3. ተማሪዎች በቅርብ ጊዜ ውስጥ የገቡበት ግጭት ካለ እንዲነግሩህና በግጭቱ ውስጥ የተሳተፉትን አይት እንዲለዩ እዲንሁም ሊወስዷቸው ይችሏቸው የነበሩ እና ወደ ተሻለ ውጤት ሊመሩ የሚችሉ ወይም ጉዳት ሊያስወግዱ ይችሉ የነበሩ እርምጃዎችን እንዲለዩ ጠይቃቸው፡፡

ሌላ አማራጭ የተመድ ፣ ጸረ ሙስና ስምምነት መግቢያ (United Nations Convention against Corruption preamble) አንብበው ተመሳሳይ ማድረግ ይችላሉ፡፡ መግቢያው እንዲህ በማለት ይጀምራል፡ "የስምምነቱ ተፈራራሚ አገሮች ሙስና በማህበረሰቦች ላይ በደቀናቸው ችግሮችና አደጋዎች እስከፊነት በተቋማትና የዴሞክራሲ እሴቶች የሥነ-ምግባር እሴቶችና ፍትህ ማዳከሙ፣ ዘላቂ እድገትና የሕግ የበላይነትን አደጋ ላይ መጣሉ ስላሳሰባቸው ... "

## ማጠናከሪያ

ተማሪዎች የወቅቱን የአካባቢ ፣ የአገር እና የአለም አቀፍ ግጭቶችን ሊመለከቱ እና አመለካከቶችም ሊገለጹ ፣ ሊወስድ የሚችለው ርምጃ እና እነዴት ግጭቶቹ ሊፈቱ እንደሚችሉ ሊያስቡ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም በሰላምና ግጭት የሚመለከቱ ጥቅሶችን በመፈለግ ጥቅሶቹን ትርጉም የሚያስረዳ የስነ ጥበብ ስራ ሊፈጥር ይችላሉ፡ ለምሳሌ ፡- ይህ የደሮቺ ቶምሰን ጥቅስን "ሰላም የግጭት ያለመኖር ማለት ሳይሆን ግጭትን ለመፍታት ብለህ (creative)" አማራጮች መኖር ማለት ነው፡፡ ለፓሲቭ ወይም አገርሲቭ(ተንኳሽ) ምላሾች አማራጭ ፣ ሃይል ለተሞላበት ምላሽ አማራጭ" እና ይህኛው ከጋንዲ አይን ለአይን መላውን አለም ስውር ያደርጋል፡፡ ትርጉማቸውን የሚገልጽ የስነ-ጥበብ ስራ ሊያዘጋጁ ይችላሉ፡፡

# ለዚህ ቃል (ስያሜ) አለን

### የትምህርት አይነት

- ስነ ጥበብ (ቲያትር)
- ቋንቋ እና ስነ ጽሁፍ

### ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

ዝቅተኛ (9ኛ እና 10ኛ) እና ከፍተኛ (11ኛ እና 12ኛ) ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

### የተመደበው ጊዜ

30 ደቂቃ

### አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ምንም አያስፈልግም

### ቁልፍ ቃላት

- ተጠያቂነት
- ጉቦ
- የጠቅም ግጭት
- ሙስና

### ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

ተማሪዎች በሌሎች ባህሎች ጥቅም ላይ የሚውሉ ማላሽ እና ሃረጎችን ሊፈትሹ ይችላሉ፡፡

መናገር እና ማንበብ ለሚያስቸግራቸው ተማሪዎች በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ያሉ የሙስና እና የታማኝነት ልማዶችን ሁኔታዎች እንዲያሳዩ በሚያስችል መልኩ መልመጃው ሊሻሻል ይችላል።

### የትምህርቱ ውጤት

ሐቀኝነትን በመሰረታዊ እሴትነት መቀበል (ዋጋ መስጠት)

### ምክንያት (RATIONALE)

ኢ-ሥነ-ምግባራዊ ልምዶች የማህበረሰባዊ ደንብ(እምነት) አካል ሊሆን ይችላሉ፡፡ በአንዳንድ አገሮች እነዚህን ልምዶች የሚገልጽ ግልጽ የሆኑ ቃላት አሉ፡፡ ይህ መልመጃ ተማሪዎችን እነዚህን ልምዶች በአዲስ መልክ እንዲመለከቱ እና እነዚህን ቃላት እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ በአዲስ መልክ እንዲያዩ እንዲሁም የባህል ግንዛቤ እንዲያገኙ ማበረታታትን ያለመ ነው፡፡

### ሒደት

1. መምህሩ የሙስና ተግባራትን ወይም ልምዶችን ሃረጎችን እና ምሳሌያዊ አነጋገሮች ጥቂት ምሳሌዎችን ይሰጣል፡፡ ከእነዚህም ልምዶች ማካከል ፡-
   ሀ/ ”ለማስወሰን ሲባል ስጦታ ማቅረብ ”(የምንፈልገውን ውሳኔ ለማግኘት ጉቦ መስጠት)
   ለ/ "ዘመዶቻቸውን ስራ እነዲያገኙ ወይም ጨረታ እንዲያሸንፉ መረዳት" (ለጓደኛ ወይም ዘመዶች ማዳላት)
   ሐ. "የጠረጴዛ ስር ክፍያ"(ድብቅ ክፍያ)
   መ/ "የማለስለሻ /ማሳለጫ/ክፍያ ”(አስፈላጊ ሂደቶችን /ደረጃዎችን /ለማለፍ ጉቦ መጠየቅ)
   ሠ/ "ልገሳ መጠየቅ" (ጉቦ መጠየቅ)

2. መምህሩ ከዚያ ተማሪዎቹን በራሳቸው ማህበረሰብ እና ቋንቋ ኢ-ሥነ-ምግባራዊ ልምዶችን ወይም ተግባራትን የሚገልፁ ቃላትን ወይም ሀረጎችን የሚያወቁ እነደሆነ ይጠይቃል፡፡

3. በመቀጠልም ተማሪዎች የሚከተሉትን በሙሉ ወይም የተወሰኑትን ላይ ላዩን ይወያያሉ፡፡
   ሀ/ እነዚህን ቃላት የሚገልጻቸው ተግባራት (ልምዶች) በኛ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድሩት እንዴት ነው?
   ለ/ ለተግባሩ (ልምድ) ተለይተው የተቀመጡ ቃላት ያሉን ለምንድን ነው? ታሪካዊና ባህላዊ ትርክቶች አሉ?
   ሐ/ እንዲህ አይነት ቃላት ወይም ሃረግ በሚኖሩን ጊዜ ለእንዚህ ልምዶች የሚኖረን ምላሽ ይቀይራል? ለምሳሌ እነዚህን ተግባራት /ልምዶች / አምርረን እንድንይዘው ያደርገናል? እነዚህ ተግባራት / ልምዶች/ የባህላችና አካል አድረገን እንድናስብ ያደርገናል?
   መ/ የባህል ልምድ ከሆነ ይህ ተቀባይነት እንኖረው ወይም የማይቀር እንዲሆን ያደርገዋል? የሁሉም የባህል ተግባራት እና ልምዶች (ደንቦች) ሁሉ ተቀባይ መሆን አለብን?
   ሠ/ ባህሎች ሁሌም የሚቀይሩ በመሆናቸው፣ እነዚህን ከመልካም ሥነ-ምግባር ውጭ የሆነ ተግባረትን ለማስቆም ምን ማድረግ አለብን?

### ማጠናከሪያ

ተማሪዎች በማህበረሰባቸው ያሉ ሰዎችን ስለእነዚህ ሀረጎች እንዲጠይቁ አበረታታ እና ተማሪዎች ባህላዊ ቅቡልነት አላቸው ብለው ያምኑ እነደሆነ ጠይቃቸው፡፡ የሚከተለው ተጨማሪ መልመጃዎች የተማሪውን የመቋቋም አቅም (Resilence) ለማሳደግ ሊተግብሩ ይችላሉ፡፡

ተማሪዎቹ በሶስት ቡድን ይከፋፈላሉ፡፡ ሁለቱ ቡድኖች በክፍሉ ጫፍ ላይ የተቃራኒው ያሉ ግድግዳዎችን ተከትለው ዳርና ዳር ይደረደራሉ፡፡ እያንዳንዱ የቡድኑ አባል በተቃራኒው ቡድን ውስጥ አጣማሪ (Counter part) ይኖረዋል፡፡

ቡድን ” ሀ ”የተመረጠ ወይም የተሰጠውን ሃረግ ወይም ምሳሌያዊ አነጋገር ይጠቀማል፡ ፡ ሁሉም የቡድኑ አባላት በአንድ ላይ ወደ ፊት በመራመድ የተሰጠውን ምሳሌያዊ አነጋገር በአንድ ላይ ይናገራሉ፡፡ በመቀጠል በቡድን ” ለ” በአንድ ላይ ወደ ፊት አንድ ርምጃ በመራመድ ከቆሙ በኋላ አይሆንም እንላለን፡፡ በማለት ይመልሳሉ፡፡

ቡድን ” ሀ”ሌላ ርምጃ ወደ ፊት በመራመድ ምሳሌያዊ አባባሉን ይደግማሉ፡፡ ቡድን ለ በበኩሉ ወደ ፊት በመራመድ ” አይሆንም እንላለን ” በማለት ይመልሳሉ፡፡ ሶስተኛ እና የመጨረሻ ርምጃ ከወሰዱ በኋላ ሁሉም የየራሳቸውን አባባሎች ይደግማሉ፡፡ ተማሪዎች /ቡድኖች/ አሁን በቅርብ እርቀት ፊት ለፊት ተፋጠዋል፡፡ ንግግሮቻቸውን በሚደግሙበት ወቅት ድምጻቸው እየጨመረ ሊመጣ ይችላል፡፡

ተማሪዎች ያደረባቸውን ስሜት ከልዩ ልዩ አቅጣጫዎች (ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፣ ተቃውሞ ታዳሚ) አንጻር ይወያያሉ፡፡ አይሆንም ወይም እምቢ ማለት ምን አይነት ስሜት አሳደረባችሁ? ከባድ ነው ወይስ ቀላል? መልመጃው እያንዳንዱ ተማሪ በሶስቱም ቦታ የመገኘት እድል እስኪኖረው ድረስ እና ሶስቱንም እይታዎችን ለማወዳደር እስኪችል ድረስ ለሶስት ጊዜ ሊደገም ይችላል፡፡



# እናንተ ብትሆኑ ምን ታደርጋላችሁ?

## የትምህርት አይነት

- ስነ ጥበብ (ቲያትር)
- የሲቪክስ ትምህርት
- ቋንቋ እና ስነ ጽሁፍ

## ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

ዝቅተኛ (9ኛ እና 10ኛ) እና ከፍተኛ (11ኛ እና 12ኛ) ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

## የተመደበው ጊዜ

30 ደቂቃ

## አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ምንም አያስፈልግም

## ቁልፍ ቃላት

- የጥቅም ግጭት
- ሙስና
- በሥነ-ምግባር የተመራ ውሳኔ አሰጣጥ

## ማጠናከሪያ

ተማሪዎች የራሳቸውን ሁኔታዎች እንዲፈጥሩና መልመጃዎችን እንዲደግሙት ጠይቅ ሁኔታዎቹ ወደ ሰድራማ ተቀይረው ለሌሎች ክፍሎች የሐቀኝነት ማስተማሪያ ሊሆኑ ይችላሉ።

## የትምህርቱ ውጤት

ሐቀኝነትን በመሰረታዊ እሴትነት መቀበል (ዋጋ መስጠት)

## ምክንያት (RATIONALE)

በዚህ መልመጃ ውስጥ ተማሪዎች እንደ ወጣት ሊያጋጥሟቸው በሚችሉ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ምርጫ ማድረግ እንዳለባቸው እናያለን።

## ሒደት

ተማሪዎች ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ሁኔታዎችመካከል በመምረጥ ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ በቡድን እንዲወያዩ ጠይቃቸው። መምህሩ ባህላዊ ተገቢነትና አስፈላጊነት ያላቸውን ሌሎች ሁኔታዎች እንዲፈጥር ይመከራል።

1. ሞባይል ስልክ ትገዛለህ የአንድ ወር ዋስትና አለው። ከሶስት ቀን በኋላ መሬት ላይ ጣልከው። ከውጭ ምንም አይነት ምልክት የለውም ይሁንና መስራት አቁሟል። ወደ ገዛህበት ሱቅ ወሰድከው። መሬት ላይ እንደጣልከው ታምናለህ?
2. ከባድ ጎርፍ ተከስተ እና በከልሉ ያሉ ብዙ መንደሮች ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉንም ነገር አጡ። ከጎርፉ በኋላ በመንደርህ ውስጥ ላሉ ሁሉም ቤተሰቦች ከአንድ የአለም አቀፍ ድርጅት ምግብ ገንዘብ እና ቁሳቁስ በነጻ ተሰጠ። አንተ በኮረብታ ላይ በተሰራው ብቸኛው ቤት ትኖራለህ። ቤትህ በጎርፍ ምንም አልተጎዳም ጓሮህም (የአትክልት ስፍራህ ቢሆን በአብዛኛው ምንም አልተጎዳም። የእርዳታ ሰራተኛው ገንዘብ፣ ምግብና ቁሳቁስ ለቤተሰብህ ለማቅረብ ቢሞክር (ቢጠይቅ)ምን ታደርጋለህ?
3. የአመቱ መጨረሻ ነው እናም በት/ቤትህ ፈተና አለ። ፈተናውን ካለፍክ ወደ ውጭ ሄደህ የመማር እድል ታገኛለህ። ሌላ ተማሪ ከፈተናው ሁለት ቀን አስቀድሞ የፈተናውን ቅጂ ሊሰጥህ ይጠይቅሃል? ምን ታደርጋለህ?
4. ትምህርትህን አጠናቀሃል እናም ስራ ትፈልጋለህ። ለቃለ መጠይቅ ወደ አንድ ቢሮ ትሄዳለህ። ከሁለት ሳምንት በኋላ ስራወን እንዳገኘህ ይነገርሃል። ከሁለት ቀን በኋላ በቢሮው ውስጥ አንድ ሰው ወደ አንተ ይመጣል። ሰውየው ቃለ መጠይቁን ያቀረበልህ እንደሆነ አስታወስከ ሰውየውም" ይህን ስራውን የሰጠሁህ እኔ እንደሆንኩ ታውቃለህ? እዚህ ያለው ልምድ / አሰራር/ የመጀመሪያ ደመወዝህን ለእኔ መስጠት ነው" አለህ። ምን ታደርጋለህ።
5. አዲስ ላፕቶፖች ትፈልጋለህ። ወደ ሱቅ ትሄዳለህ ይሁንና በጣም ውድ ሆነው ስታገኛቸው አሮጌውን ላፕቶፕህን ይዘህ ለመቀጠል ትወስናለህ። ከጥቂት ቀናት በኋላ አንድ ሰው አዲስ ላፕቶፕ የዋጋውን 10% በሚሆን ክፍያ ለሽያጭ ያቀርብልሃል። ምን ታደርጋለህ?
6. ፈቃድ ለማውጣት በአንድ የመንግስት መስሪያ ቤት ሰልፍ ይዘህ እየጠበቅክ ነው። ከዚህ በፊት እዚህ መጥተህ ስለማታውቅ የከፍያውን መጠን እና ፈቃዱም በፍጥነት እንደሚደርስ ታውቃለህ። አንድ ሴት ከፊትህ ተሰልፋለች። ሴትዮዋ ከዋናው ከተማ እንዳልመጣች እና የስራ ቋንቋውንም እንደማታውቀው ግልጽ ነው። እሷም የምትፈልገው ተማሳሳይ ፈቃድ ነው። የመንግስት ሰራተኛው አንተ ከምታውቀው ዋጋ በጣም ከፍ ያለ ክፍያ ሲጠይቅ ሰማህ ምን ታደርጋለህ?

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

መልመጃ ጊዜ የሚወስድ ነገር ግን ሳቢና ጉጉትን የሚጨምር እንዲሆን ከተፈለገ ተማሪዎቹን በቡድን በመከፈል የተለያዩ ሁኔታዎችን የያዙ ካርዶችን በማደል ይጀመራል፡ ፡እያንዳንዱ ተማሪ የቁራጭ ወረቀቱን ገልብጠው ያስቀምጡ። ከዚያ አንድ ተማሪ የሁኔታ ካርድ ይመረጥና ለቡድኑ ያነብና የካርዱ ባለቤት የሆነውን ተማሪ በዛ ሁኔታ ውስጥ ምን እንደሚያደርግ እውነቱን ወይም ውሸቱን እንዲነግረው ያዘዋል። ከዚያ የቀሩት የቡድኑ አባላት ተማሪው የተናገረው ነገር እውነት ወይም ውሸት መሆኑን የተለያዩ ጥያቄዎችን በማቅረብ መወሰን አለባቸው። ከ5 ደቂቃዎችን በኋላ ተማሪው ወረቀቱን ገልብጦ ሌሎች ተማሪዎች በማሳየት የተናገሩት እውነት ወይም ውሸት መሆን ያለመሆኑን ያረጋግጣሉ።ይህ መልመጃ ከዚያ በሌሎች ሁኔታዎች በሌሎች ተማሪዎች ሊደገም ይችላል።

ተማሪዎች በነጻነት እውነቱን መናገራቸው ወይም ውሸት መሆኑን በነጻ እንዲናገሩ አበረታታቸው ምክንያቱም ተግባሩ ጨዋታ ብቻ ነውና ነው። ዋና አላማው ተማሪዎቹ የእያንዳንዳቸው ባህሪ ማወቅ ያለማወቃቸውን መፈተሽ ነው። መምህሩ ተማሪዎቹ የተናገሩት እውነት መሆኑን ከገለጡ በኋላ መልሳቸው ተቀባይነት ማግኘቱና ማረጋገጥ አለበት።፡መልመጃው ካለቀ በኋላ በዚህ ዙሪያ ተጨማሪ ውይይት እንዳይቀጥል መጣር አለበት። ምክንያቱም ተማሪዎች የሌለውን ተማሪ የቀደመ የግል ምሳሌዎች ማንሳት ሊጀምሩ እና ልጁ ምቾት እንዲያጣ ሊያደርጉት ይችላሉ።

# ሐቀኝነትን ማክበር (Celebrate Integrity)

### የትምህርት አይነት

- ስነ ጥበብ (ቲያትር)
- ታሪክ
- ቋንቋ እና ስነ ጽሁፍ

### ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

ዝቅተኛ (9ኛ እና 10ኛ) እና ከፍተኛ (11ኛ እና 12ኛ) ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

### የተመደበው ጊዜ

90 ደቂቃ

### አስፈላጊ ቁሳቁሶች

እንደተፈጠረው(ተዘጋጀው)ሚዲያ ይወስናል፡፡

### ቁልፍ ቃላት

- የሲቪክስ ተሳትፎ
- ሙስና

## የትምህርቱ ውጤት

ሐቀኝነትን በመሰረታዊ እሴትነት መቀበል (ዋጋ መስጠት)

## ምክንያት (RATIONALE)

በዚህ መልመጃ ተማሪዎች ለብሄራዊ ሐቀኝነት ቀን የአንድ ቀን ፕሮግራም እቅድ ያዘጋጃሉ፡፡ እንዲሁም ሚዲያ ያዘጋጃሉ፡፡

## ሒደት

ተማሪዎች የባህል እና የሃይማኖት በአሎቻቸውን እንዲመረምሩ እና የትኞቹ ሐቀኝነትን የሚያከብሩ ወይም ለሐቀኝነት ትኩረት የሚሰጡ እንዲለዩ አድርግ፡፡ ለምሳሌ፡- አንድ ህይወቱን ለሚያምንበት ሁኔታ ወይም ዋጋ ለሚሰጠው እሴት የሰጠን ሰው ህይወትን ለማክበር የሚውል ቀን ወይም ነጻነትን ወይም መብትን የተቀዳጀበትን ቀን ማክበር፣ እንደ ማርቲን ሉተር ኪንግ ጁኒየር ቀን በዩ ኤስ ኤ፡፡

1. ተማሪዎች ከዚያ ብሄራዊ ሐቀኝነት የሚከብርበት ብሄራዊ በአል ያቋቁሙና የአንድ ቀን ክብረ በአል መርሃ ግብር ያቅዳሉ፡፡ የሚከተሉትን ነገሮች ሊያስቡባቸው ይገባል፡፡
   ሀ/ በበዓላቸው ሊካተቱ የሚችሉ በአገሪቱ ታሪክ ያሉ የሐቀኝነት ግንባታ ክስተቶች (ለምሳሌ ፡- የህገ መንግስት ቀን)
   ለ/ በዚህ ቀን ሊካሄድ የሚችሉ ተግባራት (ለምሳሌ፡- የቪዲዮ ውድድር)
   ሐ/ ተማሪዎቹ የሚዲያ ማቴሪያሎች (ምሳሌ ፡- ፖስተሮች /ባነሮች/ ሙዚቃ ወ.ዘ.ተ)

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

ተማሪዎች ለማክበር ያቀረቡት የብሔራዊ ሐቀኝነት ቀንን በዲሴምበር 9 ከተመድ የሚከበረው ፀረ- ሙስና ቀን ጋር ሊያገናኙት ይችላሉ፡፡

## ማጠናከሪያ

ተማሪዎች በአለም ዙሪያ የሚገኙ የብሄራዊ ባእላት (ለምሳሌ ፡- የህገ መንግስት ቀን) መፈተሽ እና የትኛው የበዓሉ ክፍል ከሐቀኝነት ጋር የተገናኘ መሆኑን መለየት ይችላሉ፡፡

# ፈተናዎች (Temptations)

## የትምህርት አይነት
- ስነ ጥበብ (ቲያትር)
- ቋንቋ እና ስነ ጽሁፍ

## ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች
ዝቅተኛ (9ኛ እና 10ኛ) እና ከፍተኛ (11ኛ እና 12ኛ) ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

## የተመደበው ጊዜ
40 ደቂቃ

## አስፈላጊ ቁሳቁሶች
የስነ ጥበብ መሳሪያዎች

## ቁልፍ ቃላት
- ተጠያቂነት
- ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ
- ሚዛናዊነት
- ሃላፊነት

## የትምህርቱ ውጤት
ምክንያታዊ ወይም የተሟላ(ጥልቅ) አስተሳሰብን ለሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ማዋል (ተፈጻሚ ማድረግ)

## ምክንያት (RATIONALE)
ይህ መልመጃ ተማሪዎች ለፈተና ከመሸነፍ እና ጽኑ ያልሆነ አቋም ከመውሰድ ጊዜ ይልቅ በቅንነትና በሃቀኝነት ያሳለፉትን ጊዜ እና ውሳኔ ላይ እንዲያተኩር ታስቦ የተዘጋጀ ነው።

## ሒደት
1. ተማሪዎች በቀድሞ ህይዎታቸው በአንድ ወቅት እራሳቸውን ለመጥቀም በማሰብ እሴቶቻቸውን የሚጥስ ተግባር የመፈጸም ማለትም መዋሸትና ጥፋቱንም የመሸፈን ፈተና ውስጥ ገብተው ያዉቁ እንደሆነ ለጓደኞቻቸው ይግለጹ። መዋሸት እና ጥፋቱን መሸፈን ስለፈጠረው ስሜት ይወያዩ፡፡ ይህ ጠባይ ከእሴታቸው ጋር የሚጣረስ መሆኑን ያስገነዘባቸው ምንድን ነው? ጥፋታቸውን ለመካስ ምን አደረጉ?

   የሚከተሉትን መግለጽ አለባቸው:
   - ፈተናዎች
   - አማራጮችን መመዘን
   - ተገቢውን ነገር ለማድረግ ምን አነሳሳቸው?
   - ከዚያ በኋላ ምን እንደተሰማቸው
   - ከሐቀኝነት ተጻራሪ ተግባር መፈጸም ባትያዙ እንኳን ለምን ሁሌም ተገቢ እንዳልሆነ
2. በመቀጠል ተማሪዎች አንድ የስነጥበብ ስራን (ለምሳሌ ፖስተር፣ ስእላዊ መግለጫ ፣ ሃውልት ወ.ዘ.ተ) ያዘጋጃሉ፡፡ የስነ ጥበብ አይነቱ መምህሩ በስርአቱ በሚያስተምረው የስነ ጥበብ ዘዴ ወይም መንገድ (midum) ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ የስነ-ጥበብ ስራው ተማሪዎቹ የሐቅ ሰዎች አድረጎ ማሳየት አለበት፡፡ በተጨማሪም ሐቀኛ ተግባር ወደ መፈጸም የሚያደርጉትን ሽግግር ወይም ይህን እንዲያደርጉ ምክንያት በሆናቸው ግንዛቤ የሚመለከት ይሆናል፡፡

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)
ተማሪዎቹ መጀመሪያ ላይ ይህን የደረሰባቸው መቼ እንደሆነ መለየት አስቸጋሪ ሆኖ ሊያገኙት ይችላሉ፡፡ ይህን ለመቅረፍ መምህሩ አስቀድሞ መልመጃውን ሊነግራቸው እና የሚያስቡበት አንድ ቀን እንዲሰጣቸው ይመከራል፡፡

## ማጠናከሪያ
ተማሪዎቹ የስነ ጥበብ ስራወቸውን ለእይታ ሊያቀርቡ እና ምን እንዳነሳሳቸው እንዲሁም ስራው ስለያዘው ተምሳሌት ሊገልጹ ይችላሉ፡፡



# ተግባሮቼ /ስራዎቼ /እሴቶቼን ያንጸባርቃሉ?

## የትምህርት አይነት

- ስነ ጥበብ (ቲያትር)
- ቋንቋ እና ስነ ጽሁፍ
- የሃይማኖት ጥናት

## ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

ዝቅተኛ (9ኛ እና 10ኛ) እና ከፍተኛ (11ኛ እና 12ኛ) ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

## የተመደበው ጊዜ

45 ደቂቃ

## አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ምንም አያስፈልግም

## ቁልፍ ቃላት

- ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ
- ግጭት አፈታት
- ጾታ

## የትምህርቱ ውጤት

ምክንያታዊ ወይም የተሟላ (ጥልቅ) አስተሳሰብን ለሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ማዋል /ተፈጻሚ / ማድረግ፡፡

## ምክንያት (RATIONALE)

በዚህ መልመጃ ውስጥ ተማሪዎች የእለት ተእለት ተግባሮቻቸው የእራሳቸውን እሴት የሚያንፀባርቁ ከሆነ እና በታማኝነት የሚሰሩ መሆናቸውን ይመረምራል።

## ሒደት

1. ተማሪዎች የዛሬውን እለታዊ ውሏቸውን እንዴት እየመሩ እንደሆነ ማለትም የእለት ተግባራቸውን እንዴት እያከናወኑ እንደሆነ እና በግል እሴቶቻቸው መሰረት ወደ ፊት እንዴት ህይዎቸውን መምራት እንደሚፈልጉ ይመዝግቡ፡፡ የግል እሴቶቻቸው የቤተሰቦቻቸው ፣ የሃይማኖቶቻቸው ፣ የባህላቸው ወይም የአጠቃላይ ማህበረሰባቸው ተጽእኖ ውጤት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ከታች ካሉት ዝርዝሮች በመምረጥ መልመጃቸውን ሊጀምሩ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በዝርዝሩ ላይ ሊጨምሩ ይችላሉ፡፡
2. ተማሪዎች ለእያንዳንዳቸው እምነታቸውን የሚገልጽ አረፍተ ነገር በማስተካከል የሚወስዱት ርምጃ / የሚፈጽሙት ተግባር/ ምን እንደሆ ያስረዱ፡፡ በማስከተልም ምን ያህል በወጥነት ተግባራቸውን እንደሚፈጽሙ ከ1-5 ባለው መመዘኛ ራሳቸውን ይለኩ፡፡ ይህ ልኬት ቃላቸው ወደ ተግባር በመቀየር ረገድ በጣም ደካማ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ /ቀጥሎ ያለው ሰንጠረዥ ራሳቸውን ለከተው ሲጨርሱ አቻቸውን በተራው እንዲለካ ይጠይቁ፡፡

| የማምንባቸው ሁኔታዎች | እያደረኳቸው ያሉ ነገሮች | ልፍጽማቸው የሚገቡ ተግባራት | የራስ ምዘና | የአቻ ምዘና |
|---|---|---|---|---|
| ሀ/ ሌሎችን ማክበር | | አለመጨቆን/ አለማንገላታት / ሌሎች እንዲሰሙ እድል መስጠት | | |
| ለ/ የአካባቢ ደህንነትን መጠበቅ /environmental proportion | | በእግር ወይም በብስክሌት መጓዝ መልሰው ጥቅም ላይ የሚውሉ ምርቶችን መግዛት፣ ቆሻሻን በሃላፊነት ማስወገድ ፣ሃይል መቆጠብ | | |
| ሐ/ የሴቶች እኩልነት | | ለሴት ተውዳዳሪዎ ድምጽ መስጠት፣የሴቶችን ትንኮሳ ማስቆም፣ ልጃገረዶችን ከወንዶች እኩል መመልከት | | |
| መ/ ስፖርት ውስጥ ሚዛናዊነት | | የጨዋታ ህግ ማክበር፣ በሚዛናዊ አጨዋወት ማመን፣ ተጋጣሚህን እንኳን ደስ አለህ ማለት | | |
| ሠ/ በት/ቤት ውስጥ አለማጭበርበር | | ከሌሎ አለመኮረጅ ፣ የቤት ስራዎችን በሌሎች ያለማሰራት | | |
| ረ/ አብሮእነትና ለሌች ማጋራት | | ችሎታየን፣ እውቀቴን እና ክህሎቶቼን ለሌሎች ማጋራት | | |

3. መልመጃውን ካጠናቀቁ በኋላ የሁለቱን ልኬት ውጤት ያወዳድራሉ፡፡ በመቀጠልም መምህሩ ተማሪዎቹን እናምንበታለን ብለን የምናደርገው ነገር ሁሌም በሚባል ደረጃ ለምን እንደማንተገብረው ይጠይቃሉ፡፡
4. በመቀጠል ተማሪዎች ተግባራቸው ከእሴቶቻቸው ጋር የሚያጣጥሙባቸውን ስልቶች ለመለየት ይወያያሉ፡፡

## ማጠናከሪያ

ለእያንዳንዱ አረፍተ ነገር "ይህን መተግበሪያን የሚያሳይ ማስረጃ" የሚል ክፍል መጨመር ይቻላል፡፡ ይህ በእውነት ላይ የተመሰረተ እና ተግባራቱ እንደሚፈጸሙ የሚያሳይ አካሄድ ነው፡፡ ጊዜ የሚፈቅድ ከሆነ ተማሪዎች ቁርጠኝነታቸውን የሚያሣይ ፖስተር ሊያዘጋጁ ይችላሉ፡፡

# እውነቱ የቱ ነው?

### የትምህርት አይነት

- ቋንቋ እና ስነ ጽሁፍ
- የመረጃ ቴክኖሎጂ

### ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

ዝቅተኛ (9ኛ እና 10ኛ) እና ከፍተኛ (11ኛ እና 12ኛ) ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

### የተመደበው ጊዜ

90 ደቂቃ

### አስፈላጊ ቁሳቁሶች

የስነ ጥበብ መሳሪያዎች

### ቁልፍ ቃላት

- ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ
- ሚዲያ

### ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

ኢንተርኔት ከሌለ ተማሪዎች የጋዜጣ እና ሬዲዮ ዘገባዎችን ማወዳደር ወይም የተለያዩ ሚዲያዎች ተማሳሳይ የዘገቡበት መንገድ ማወዳደር ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች የዜና አዘጋገቦችን እንዴት እንደሚለያዩ የሚያውቁ ከሆነ የታዋቂ ሰዎች ሕይዎት ታሪክ አዘጋገብ እንዴት እንደሚለያዩ እንዲያስቡ አድርግ የንባብ ወይም የንግግር መልመጃው የዜናዎችን እና ቪዲዮዎችን በመተንተን ላይ ሊያተኩር ይችላል፡፡

ማየት ለተሳናቸው ተማሪዎች መልመጃው የራዲዮ ዜና ትንተና ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ይችላል፡፡

### የትምህርቱ ውጤት

ምክንያታዊ ወይም የተሟላ (ጥልቅ) አስተሳሰብን ለሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ማዋል፡፡

### ምክንያት (RATIONALE)

የመረጃ አድሏዊነት ችግር / ጉዳይ / ነው፡፡ ለምሳሌ አንዳንድ ጋዜጠኞች በልዩ ልዩ ምክንያት ራሳቸውን ሳንሱር ሊያደርጉ ወይም በሚዘግቡበት ጊዜ ገለልተኝነት /objectivity /ሊጎድላቸው ይችላል፡፡ አሁን አሁን ጋዜጠኝነትን ጨምሮ በአሳሳች መረጃ ስርጭት / Disinformation / መጨመር የተነሳ መረጃ ሐቀኝነት አደጋ ላይ እየወደቀ ነው፡፡ በዚህ መልመጃ ተማሪዎች በሚዲያ የሚቀርቡ ዜናዎችን በጥንቃቄ ማየት እና መመርመርን እንዲሁም ልዩ ልዩ የሚዲያ አውታሮችን በመገምገም እና የዜና ዘገባዎችን በማወዳደር አድሎ መለየትን ይማራሉ፡፡

### ሒደት

1. ተማሪዎችን በቡድነ ከከፈሉ በኋላ በሐቀኝነት ላይ የተዘጋጁ ወቅታዊ የአገር ውስጥ ወይም አለም አቀፍ ዘገባ በመውሰድ የተለያዩ የፖለቲካ አመልካከት ያላቸው የዜና አዉታሮች (ድረገጾች፤ጋዜጦች፤ቲቪ፤ ራዲዮ ወዘተ...) እንዴት እነደዘገቡ እንዲመለከቱ አሳስባቸው፡፡ ቀጥሎም እያንዳነዱ አውታር ሽፋን የሰጠውን ቁልፍ ጉዳይ/ዮች እንዲለዩ ንገራቸው።
2. ተማሪዎች በሰንጠረዥ አዘጋጅተው በዘገባው የተንፀባረቁት አመለካከቶችን ፣ ጥቅም ላይ የዋለው የአዘጋገብ ዘየ (ፍሬ ነገር ወይስ የግል አመለካከት?)፣ ሊቀሰቅሱ የፈለጉት ስሜት እንዲሁም ከመረጡት የአዘጋገብ ዘዬ ጀርባ ያለውን አላማ በሰንጠረዡ ውስጥ እንዲዘረዝሩ አድርግ፡፡
3. ተማሪዎች በዜና ዉስጥ በእውነታ ላይ የተመረኮዘ ዘገባ እና በግል አስተያየት መሃል ያለውን ልዩነት እነዲገነዘቡ ያሰፈልጋል፡፡
4. ተማሪዎች የተለያዩ የአተራረክ ዘዴዎችን እና ዜና የሚያዘጋጁ ሰዎች ያላቸውን ፍላጎት እና አላማ (አጀንዳ) የተመለከተ ውይይት እንዲያከናውኑ አበረታታ፡፡
5. ተማሪዎች በዘገባው ውስጥ ያሉ አሳሳች ክፍሎችን እንዲለዩ እና ሐቀኛ እና ሚዛናዊ አቋም መሆን አለበት በሚሉት ላይ በቡድን ሆነው ሃሳብ እንዲቀያየሩ ንገራቸው፡፡

### ማጠናከሪያ

መምህሩ ጋዜጠኛ ወይም የሚዲያ አዘጋጅ በመጋበዝ የጋዜጣ / ሚዲያ / ስራ እንዴት እነደሚመራ እና ጋዜጠኞች የዜና ዘገባ ሳቢ እንዲሆን በሚጠቀሟቸው ቴክኒኮች ገለጻ እንዲያደርጉ ያመቻች፡፡ በተጨማሪም ዜና በመጻፍ እና በማዘጋጀት ሂደት ውስጥ አድሎን እንዴት ማስወገድ እንደሚችል ምክሮች እንዲለግሱ መጠየቅም ያቻላል፡፡

ተማሪዎች በዜና ዘገባዎች ውስጥ ስሜትን የሚቀሰቅሱ የቋንቋ አጠቃቀሞችን ለይተው በማጉላት የተቀመጡትን ኦላይን ግብአቶች ተጠቅመው የሚከተሉትን ጉዳዮች ላይ ይወያዩ፡፡

- የበይነ መረብ ትንኮሳ: Ethics Unwrapped web article, “Cyber Harassment”
- የንግግር ነጻነት: Ethics Unwrapped web article, “Freedom of Speech on Campus”
- ሴራ ንድፈ ሃሳብ (Conspirecy Theory): UNESCO publication, “Addressing conspiracy theories: What teachers need to know” (Paris, 2022)
- የጥላቻ ንግግሮች: UNESCO web article, “Countering hate speech: It starts with words”

በተጨማሪም ተማሪዎች የሥነ-ምግባራዊ ትረካ ፣ ምንነት ፣ እውነት ላይ የተመሰረቱ ዘገባዎን ማወዳደር እና ሥነ-ምግባርን የተላበሰ ትረካን (ዘገባን) ከሥነ-ምግባር ከጎደለው ዘገባ የምንለይበትን መመዘኛ (criteria)መለየት የተመለከቱ ውይይቶች ሊያደረጉ ይችላሉ፡፡

# በተመጣጣኝ ወጪ ማውጣት

### የትምህርት አይነት

- ቋንቋ እና ስነ ጽሁፍ
- የመረጃ ቴክኖሎጂ

### ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

ዝቅተኛ (9ኛ እና 10ኛ) እና ከፍተኛ (11ኛ እና 12ኛ) ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

### የተመደበው ጊዜ

90 ደቂቃ

### አስፈላጊ ቁሳቁሶች

የስነ ጥበብ መሳሪያዎች

### ቁልፍ ቃላት

- ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ
- ሚዲያ

## የትምህርቱ ውጤት

ምክንያታዊ ወይም የተሟላ (ጥልቅ) አስተሳሰብን ለሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ማዋል፡፡

## ምክንያት (RATIONALE)

በዚህ መልመጃ ተማሪዎች ሐቀኝነት ላይ የተመሰረተ የህዝብ ገንዘብ አጠቃቀም ሂደትን ይለያሉ፡፡

## ሒደት (የአካሄድ ስርአት)

1. መምህሩ ተማሪዎችን በቡድን ከከፈለ በኋላ እያንዳንዱ ቡድን የአባላት መዋጮን ተጠቅሞ የሚያከናውነውና አባላቱ የሚያውቁት እንደ ስፖርት ዕቃዎች ግዥ የመሰለ የግዥ ሁኔታ ያቀርባል፡፡ ወይም ተማሪዎች የራሳቸውን አማራጭ ሁኔታ (የምናባዊ ሁነት/ senario) ሊፈጥር ይችላል፡፡
2. በመቀጠልም ቡድኖቹ በባለድርሻ አካላት ሊታመን የሚችል የሕዝብ ገንዘብ አያያዝ (አስተዳደር) ስነ ስርአት (ሂደት) ይዘረጋሉ፡፡ ከግምት ውስጥ

ሀ/ ፍላጎትን መለየት

- ተመጣጣኝ (ተገቢ) ወጭ ምን ያህል ነው ወይም ማውጣት የተፈቀደልን ምን ያህል ነው?
- ይህን በተመለከተ ማማከር ያለብን ማንን ነው?
- ተገቢ (ተመጣጣኝ) መመዘኛዎች (criteria) ተብለው የሚታሰቡት የትኞቹ ናቸው?

ለ/ ገንዘብ ወጭ ማድረግ

- እጅግ በጣም ጥሩ ዋጋ እንዳገኘን በምን እናውቃለን?
- የፈለግነውን ጥራት እንዳገኘን በምን እናውቃለን?

ሐ/ ሪፖርት ማቅረብ እና ቁጥጥር

- የእነዚህ ውሳኔዎች ውጤት የተጎዱ ወገኖችን ጨምሮ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሁሉ ምላሽ አግኝተናል?
- ባለድርሻ አካላት የወጪያችንን ውጤት እንድንከታተል በምን ዘዴ ሊረዱን ይችላሉ?

በመጠቀጠል መምህሩ እያንዳንዱ ቡድን ከላይ የተጠቀሱትን ደረጃዎች እንደተሰጣቸው የግዢ ሁኔታዎች በድራማ መልክ እንዲያቀርቡ ይጋብዛል የቀሩት ተማሪዎች በሂደት እንዴት ሊሻሻል እንደሚችል ምክር ሃሳቦች ለይተው ያስቀምጣሉ እንዲሁም ከእያንዳንዱ አቅርቦት (presenation) በኋላ ጥያቄ መጠየቅ ይችላሉ፡፡

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

ተማሪዎች ከልምዳቸው ተመሳሳይ ሁኔታን ማስታወስ ሊቸገሩ ስለሚችሉ መምህሩ ቀድሞ ስለመልመጃዎቹ ሊያሳውቃቸው ስለሁኔታው እንዲስቡ በትንሹ አንድ ቀን እንዲሰጣቸው ይመከራል፡፡

## ማጠናከሪያ

ከላይ ለተጠቀሱት ሄደቶች እንደ ት/ቤት ግንባታ ለመሳሳሉ ከፍ ያለ ወጭ የሚጠይቁ ስራዎች ሊደግሙ ይችላሉ፡፡ ተማሪዎቹ መልመጃውን ከመጀመራቸው በፊት የትምህርት ቤቱ አስተዳሪ ስለ ግዢ ሁደት ገላፃ እንደረግ ሊጋበዝ ይችላል፡፡

# አሰርቲቭ ፣ፓሲቭ ወይም አግሬሲቭ (Assertive, Passive or Aggressive)

### የትምህርት አይነት

- ቋንቋ እና ስነ ጽሁፍ
- ኪነ ጥበብ(ትያትር)

### ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

ዝቅተኛ (9ኛ እና 10ኛ) እና ከፍተኛ (11ኛ እና 12ኛ) ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

### የተመደበው ጊዜ

90 ደቂቃ

### አስፈላጊ ቁሳቁሶች

የሁኔታዎቹ ቅጂ (Copies of the Scenario)

### ቁልፍ ቃላት

- የግጭት አፈታት
- ጾታ

### የትምህርቱ ውጤት

ምክንያታዊ (የጠለቀ)አስተሳሰብን ለሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ ማዋል፡፡

### ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

መምህሩ የሚና ጨዋታውን በቪዲዮ በመቅረጽ ተማሪዎች በጭዋታው ጊዜ የሚኖራቸውን አካላዊ እንቅስቃሴ (body language) መልሰው እነዲመለከቱ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ይህን ከማድረጉ በፊት የተማሪዎቹን ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

### ማጠናከሪያ

ተማሪዎች የአግረሲቭ ወይም ፓሲቭ የተግባቦት ዘዴ ተጠቅመው ሊግባቡ ከሞከሩ ከታዘቡ ተግባቦቱ በአሰርቲቭ መንገድ እነዲያስተካክሉ ይምከሩ፡፡

### ምክንያት (RATIONALE)

በዚህ መልመጃ ተማሪዎች ልዩ ልዩ የተግባቦት ዘዩዎችን (styles) እና በሌሎች ድርጊት መነሻነት ለሚከሰቱ የሥነ-ምግባር ችግሮችንና ክብረነክነት አያያዥ የአሰርቲቭ ተግባቦት ጥቅሞችን ይለያሉ፡፡ የተግባቦት ዘዴዎች ጋር ለሚኖረን ተራክቦ(ግንኙነት) የምንመርጣቸው መንገዶች ወይም የተጋባቦት ዘዴዎች ናቸው፡፡ ሶስቱ የተለመዱ ዘዴዎች (መንገዶች) የሚከተሉት ናቸው፡፡

"ፓሲቭ"፡- በዚህ የተግባቦት ዘዴ ግለሰቡ ምላሽ መስጠት አይፈልግም ወይም ምልሽ ቢሰጥም አመለካካቱን ወይንም ስሜቱን በተለሳለሰ መልክ ማቅረብ ይመርጣል፡፡ ግጭትን በሚችለው መጠን ማሶገድ የሚመርጥ ሲሆን ለአመለካካቱ እምብዛም ዋጋ አይሰጥም፡፡

"አግሬሲቭ" ይህን መንገድ የሚጠቀሙ ግለሰቦች ሌላውን ወገን መጫንና አመለካከታቸውን የመተቸት እና የማጣጣል ባህሪን የሚያሳዩ ሲሆን ዋጋ የሚሰጡት ጉዳይ ማሸነፍን ብቻ ነው፡፡

"አሰርቲቭ"ይህንን ተግባቦት ዘዴን የሚጠቀሙ ሰዎች አመለካከታቸውን ሌሎች እንዲያውቁላቸው በአጽንኦት የሚጥሩ ሲሆን የሌሎችን የተለየ ሃሳብ የመያዝና የመግለጽ መብትን የሚያከብሩና ሌሎች ላይ ለመጫን የማይሚክሩ ናቸው፡፡

### ሒደት

1. ለሚና ጨዋታ ፈቃደኛ የሆኑ ስድስት ተማሪዎች ምረጥ
2. ለተቀሩት ተማሪዎች ወረቀት እና የስዕል መሳሪያዎችን ከሰጠህ በኋላ የፓሲቭ ፣ አሰርቲቪ ወይም አግረሲቭ የተግባቦት ዘዴዎች እንዲስሉ ጠይቅ (ማስታወሻ ፡- ይህ ተግባር ስድስቱ ተማሪዎች እንዲዘጋጁ ጊዜ ለመስጠት ተብሎ ተዘጋጀ ነው)፡፡
3. ስድስቱን ተማሪዎች በመያዝ ከክፍሉ ውጣ፡፡
4. ፈቃደኞቹ ተማሪዎች በሶስት ጥንድ እንዲጣመሩ ጠይቃቸው፡፡ በመቀጠልም በሁለት ጓደኞች ማለትም በአንድ ወጣት ወንድና በወጣት ልጃገረድ መሃል የሚከናወን ሚና ወክለው እንደሚጫወቱ ግለጽላቸው፡፡ የሚከተለውን ወይም ሌላ ተስማሚ የሚሆን ሁነት (scenario) አቅርብላቸው፡፡
   ሮዛ በሃገሪቱ ታዋቂ በሆነው ዩኒቨርሲቲ ገብታ የመማር ፍላጎት እና ተስፋ አላት፡፡ ይህን ለማሳካት በትምህርት ቤቱ የሚሰጡትን የሳይንስ ፈተናዎች በከፍተኛ ውጤት ማለፍ እና በአካባቢው የነጋዴዎች ማህበር የሚሰጠውን እስኮላርሽፕ ማሸነፍ ይጠበቅባታል፡፡ ይህን እስኮላርሽፕ ካገኘች ቤተሰቦቿ የዩኒቨርሲቲ ትምህርት ክፍያ (tuition fees) የመሸፈን አቅም እንደሌላቸው ታውቃለች፡፡ ትምህርቷን በርትታ የተከታተለችና ያጠናች በመሆኑ እስካሁን ያላት ውጤት (grades) እጅግ በጣም ጥሩ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዳለች ጓደኛዋ ከፍያለው ለትምህት ቤቱ የስራ ባልደረባ ጉቦ በመስጠት የፈተናውን ቅጂ አስቀድሞ ማግኘት እንደቻለ እና የጠየቀውን ክፍያ ማቅረብ ለሚችል ሁሉ ፈተናውን እየሸጠ እንደሆነ ሰማች፡፡ ሮዛ እንደዚህ አይነት የማጭበርበር ተግባር ውስጥ መሳተፍ አትፈልግም፡፡
5. እያንዳንዱ ሰጥንድ በሚከተሉት የቢሆን ሁነቶች ላይ በመመስረት በሮዛ እና በከፈለኝ መካከል ያለውን ውይይት በጭውውት (ድራማ) መልክ ያቅርብ (ለእያንዳንዱ ጥንድ 5 ደቂቃዎችን መድብ)፡፡
   **አንደኛው ጥንድ**: ሮዛ በፓሲቭ ዘዬ የከፈለኝ ተግባርን በተመለከተ የተሰማትን ወይም ያላትን አመለካከት እና እሱ ምን እንዲያደርግ እንደምትፈልግ እንደምትሻ ወይም ምን ማድርግ እንዳለበት ትገልጻለች፡፡ ፓሲቭ ተግባቦት ምን እንደሆነ የሚያሳዩ አንዳንድ ነጥቦችን ግለጽላቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ዝቅ ያለ ድምጽን መጠቀም ፣ ከአድማጩ ጋር የሚኖርን የአይን ግንኙነት (eye contact) መሸሻ ፣ ተናጋሪው የሚፈልገውን በግልጽ መናገር ይልቅ በጥያቄ መልክ ማቅረብ ወ.ዘ.ተ...
   **ሁለተኛው ጥንድ**: ሮዛ ሀይለቃል በተሞላበት መንገድ (የአግረሲቭ ዘዬ) ከፈለኝ ስላደረገው ነገር በተመለከተ ያላትን አመለካከት እና ምን ማድረግ እንዳለበት ወይም ምን እንዲያደርግ እንደምትፈልግ ትገልጻለች፡፡ አግረሲቭ ተግባቦት ብዙውን ጊዜ በጩኸት መናገር እና የሌሎችን አስተያየት መስማት ያለመፈለግ ወይም በራስ አቋም ድርቅ ማለት ወ.ዘ.ተ መግጫዎቹ መሆናቸውን አስታውሳቸው፡፡
   **ሶስተኛው ጥንድ**: ሮዛ ከፈለኝ ስለፈጸመው ተግባር ያላትን አመለካከት እንደዚሁም ምን እንዲያደርግ እንደምትፈልግ አስረግጣ ወይም በአስተዋጽኦ ትገልጻለች፡፡ (አሰርቲቭ ዘዬ)፡፡ አሰርቲቭ የተግባቦት ዘዬ ማለት ለያዝከው አቋም ያለህን ምክንያቶች ግለጽ በሆነ እና በተለመደው የአነጋገር ዘይቤ (ድምጸት) መግለጽ ብቻ ሳይሆን የሌሎችን ሃሳብ ለማስማማት ፈቃደኛ መሆን ማለት እንደሆነ እንዲገነዘቡ አድርግ፡፡
   ለእያንዳንዱ ጥንድ፡- ከፈለኝ በፈለገው መንገድ እና የፈለገውን መልክ መስጠት ይችላል፡፡ ይሁንና የመለሰበት መንገድ ሮዛ አስተያየቷን ከገለጸችበት ድምጽ (tone) ወይንም የአነጋገር ዘዬ አንጻር አብሮ የሚሄድ ወይም ትርጉም ሊሰጥ ይገባል፡፡
6. ፈቃደኛ ተሳታፊዎች የተሰጣቸውን የቢሆን ሁነት (scenario) ከክፍል ውጭ እንዲለማመዱ ጊዜ ስጣቸው፡፡ ከልምምዱ በኋላ ወደ ክፍል ውስጥ ተመልሰው ጭውውታቸውን እንዲያቀርቡ አድርግ፡፡
7. ሶስቱም የቢሆን ሁነቶች ከቀረቡ በኋላ የክፍሉን ተማሪዎች በእያንዳንዱ ሁነት ያስተዋሉትን እንዲነግሩህ ጥያቄ አቅርብ፡፡ በሚከተሉት ላይ ውይይት ይደረግ፡፡
   ሀ/ የ"ፓሲቭ"ተግባቦት የሚያስከትላቸው ውጤቶች ምንድን ናቸው ? የ"አግረሲቭ" ውጤቶችስ ?
   ለ/ ሰዎች የ"ፓሲቭ " ወይም የ"አግረሲቭ" የተግባቦት ዘዬን እንዲጠቀሙ የሚያነሳሳቸው ምንድን ነው?
   ሐ/ ማህበረሰቡ ከወጣት ወንዶችና ልጃገረዶች በዘልማድ የሚጠብቀው የተለያዩ የንግግር ዘይቤ (መንገድ) ከሚከተሉት የተግባቦት ዘዬ (style) ጋር ግንኙነት ያለ ይመስላችኋል? ግንኙነት አለው ካላችሁ እንዴት?
   መ/ ከፓሲቭ እና አግረሲቭ ተግባቦት ዘዬዎች አናጻር የአሰርቲቭ ተግባቦት ዘዬ ያሉት ጥቅሞች ምንድን ናቸው?



# እሴቶቻችሁ ምንድን ናቸው?

## የትምህርት አይነት

- የስነ ዜጋ ትምህርት
- ኢኮኖሚክሰ
- የመረጃ ቴክኖሎጂ

## ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

11ኛ እና 12ኛ ክፍል ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

## የተመደበው ጊዜ

60 ደቂቃ ዳታ ለመሰብሰብ እና ለመተንተን የሚያስፈልግ ስርአት

## አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ምንም እንኳን በትዕዛዙ መሰረት ከተሰራ በወረቀት ላይ ሊሰራ ቢችልም ተማሪዎች ኢንተርኔት ሊያስፈልጋቸው ይችላል፡፡

## ቁልፍ ቃላት

- እራስን በሌሎች ቦታ አድርጎ ማሰብ ወይም የሌሎችን ሁኔታ ለመረዳት መጣር
- ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ
- ሰብአዊ መብቶች
- የሃላፊነትን ስሜት

## የትምህርቱ ውጤት

ተማሪዎች መልካምሥነ-ምግባር በተላበሰ ባህሪ አማካኝነት ሐቀኛ አኗኗርን ይከተላሉ፡፡

## ምክንያት (RATIONALE)

በዚህ መልመጃ ተማሪዎች እሴቶቻቸውን በግልጽ ከተገነዘቡ በኋላ ልዩ ልዩ የሥነ-ምግባር (ሞራል) አጣብቂኞች (dilemmas) ሲገጥማቸው የሚወስዱትን እርምጃ ይወስናሉ፡፡

## ሒደት

1. ተማሪዎች የሃላፊነት ስሜት ፣ ታማኝነት ፣ ሚዛናዊነት ፣ ተጠያቂነት ፣ ግልጸኝነት እና ሐቀኝነት ለእነሱ አስፈላጊ ነው ብለው ያምኑ እንደሆነ እና የሚያምኑም ከሆነ የምክንያታቸውን ምንነት የሚመለከተው አጭር ውይይት ያድርጉ፡፡
2. የሚከተለውን ሰንጠረዥ ቅጂ ለእያንዳንዱ ተማሪ አዳርስ ካልሆነ ዝርዝሮቹን አንብብላቸው፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎች በሰንጠረዡ የተዘረዘሩትን በምን ያህል ድግግሞሽ እንደሚተባበሩ እንደሚያመላክቱ ጠይቃቸው፡፡ ይህ መልመጃ ተግባራቸውን ቀድመው ስለ እነዚህ እሴቶች ከተጠቀሱት ጋር እንደሚገጥም (እንደሚስማማ) ለመረዳት ያግዛል፡፡

| እሴት (Value) > መግለጫዎች/ አባባሎች (Statements) | ሁልጊዜ | አንዳንድ ጊዜ | ፈጽሞ |
|---|---|---|---|
| ኃላፊነትን መዉሰድ(የኃላፊነት ስሜት)<br>1.በብዙሃኑ የማይወደድ (የማይደገፍ) ቢሆን እንኳን ከትክክለኛ (ተገቢ) ከሆነው ጎን እቆማለሁ፡፡<br>2.የሌሎች አሉታዊ አመለካከት ወይም ደስተኛ ያለመሆን ፈጽሞ አያስቆመኝም<br>3.አይሳካም የሚል ፍርሃት ነገሮችን ከመሞከር አያግደኝም<br>4.ሌሎች በንግግሬ ባይስማሙም ወይም የመናገር መብት እንደሌለኝ ቢያስቡም የመናገር ቁርጠኝነት (ድፍረት) አለኝ፡፡<br>5.ኃይልን (ጉልበትን) ሳልጠቀም ችግሮችን እፈታለሁ፡፡<br>6.ሁልጊዜ ሌሎችን ከማሳፈር ፣ በሌሎች ላይ ከመቀለድ (ከማሾፍ)ወይም የሌሎችን ስሜት ከመጉዳት ለመቆጠብ እሞክራለሁ፡፡ | | | |
| እውነተኛነት<br>1. ሁሌም እውነት እናገራለሁ<br>2. አልሰርቅም ወይም አላጭበረብርም<br>3. ሌሎችን ሆነ ብየ አላሳስትም | | | |
| ሚዛናዊነት<br>1. እኔ ሌሎች ሊያደርጉብኝ የማልፈልገውን ነገር በሌሎች ላይ አላደርግም<br>2. ሰዎችን ከማወቄ በፊት በእኩል አይን እና ባለመፍረድ አያቸዋለሁ<br>3. የሌሎችን ሃሳብ ለመስማት ፈቃደኛ እና ምክንያታዊ ነኝ<br>4. ሕግጋት አከብራለሁ (ሕግጋት ለኔ የተለዩ እንዲሆኑ አልጠብቅም)<br>5. ለጥቅም ስል ሌሎችን አልበዘብዝም (ሌሎችን ለራሴ መጠቀሚያ አላደርግም)<br>6. በእኔ ድርጊቶችና ውሳኔዎች ሊጎዱ የሚችሉ ሰዎችን ስሜት ከግምት ውስጥ አስገባለሁ፡፡<br>7. ምንም እንኳን ተንኳሽ ሊሆኑ ቢችሉም ሰዎችን በአክብሮት እይዛለሁ፡፡ | | | |
| ተጠያቂነት<br>1. የፈጸምኩትን ተግባር ሁሌም በታማኝነት ሪፖርት አደርጋለሁ፡፡<br>2. ጥፋት በምፈጽምበት ጊዜ የሚመጣውን ትችት ወይም ሌላ እርምጃ ለመቀበል ዝግጁ ነኝ፡፡ | | | |
| ግልጸኝነት<br>1. ለሌሎች ሀላፊነት ሲኖርብኝ ነገሮችን ፈጽሞ አልደብቅም<br>2. መረጃ በድብቅ መያዝ ያለበት በጥቂት ሁኔታዎች ብቻ ነው ብየ አምናለሁ | | | |
| ሐቀኝነት<br>1. ተግባሮቼ በሥነ-ምግባር እሴቶች እንዲመሩ አደርጋለሁ<br>2. ከፍተኛውን የሥነ-ምግባር ደረጃዎችን የሚያሟላ ባህሪ አለኝ<br>3. ታዛቢ (ተመልካች)በማይኖርበት ጊዜ እንኳን ተገቢ (ትክክለኛ) የሆነውን ነገር አደርጋለሁ<br>4. ለፈተና (temptation) አልሸነፍም | | | |

3. ተማሪዎች ትምህርት ቤታቸውን ወይም ማህበረሰባቸውን በአግባቡ የሚወክል ናሙና በመውሰድ እሴቶችን ና ሐቀኝነትን የተመለከተ የሕዝብ አስተያየት ዳሰሳ (መጠይቅ) እንዲያከናውኑ አበረታታቸው:: ተማሪዎች ጥያቄዎችን ለማዘጋጀት እንዲረዳቸው መምህሩ ውይይት አመቻችቶ ሐቀኝነት ከሚጠይቃቸው (ከሚፈልጋቸው)ነገሮች መሃል የክፍሉ ተማሪዎች የበለጠ አስፈላጊ ናቸው የሚሏቸውን እንዲለዩ (እንዲወስኑ)ማድረግ ይችላል::

ለምሳሌ ጥያቄዎቹ የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላል::

| 1. በጣም አስፈላጊ | 2. አስፈላጊ | 3. ያን ያህል አስፈላጊ ያልሆነ | 4. ፈጽሞ አስፈላጊ ያልሆነ |
|---|---|---|---|

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሀ/ ፕላኔቴን እወዳለሁ:: | 1 | 2 | 3 | 4 |
| ለ/ ሁልጊዜ ቤተሰቦቼንና ጓደኞቼን አስባቸዋለሁ እንክብካቤም አደርግላቸዋለሁ:: | 1 | 2 | 3 | 4 |
| ሐ/ ባህሌንና ትውፊቴን አከብራለሁ:: | 1 | 2 | 3 | 4 |
| መ/ ለኔ ታማኝነትና እውነትነት ትልቅ ዋጋ አላቸው:: | 1 | 2 | 3 | 4 |
| ሠ/ ለሁሉም መሰረታዊ እና ሰብአዊ መብቶችን አክብሮት አለኝ:: | 1 | 2 | 3 | 4 |
| ረ/ የሃገሬን ህጎችና ደንቦች አከብራለሁ:: | 1 | 2 | 3 | 4 |
| ሰ/ የነሳችንና የቤተሰቦቻችን ክብር ከሁሉም በላይ ዋጋ አለው:: | 1 | 2 | 3 | 4 |
| ሸ/ የሃይል እርምጃ (ጥቃትን)አለመቀበል ወይም መቃወም ችግርን የመፍቻ መንገድ እንደሆነ አምናለሁ:: | 1 | 2 | 3 | 4 |
| ቀ/ የሌሎችን ባሕል እታገሳለሁ:: | 1 | 2 | 3 | 4 |
| በ/ ለሃብታምነትና በሌሎች ለመከበር ሰለሁሉም የላቀ ዋጋ እሰጣለሁ:: | 1 | 2 | 3 | 4 |
| ተ/ ለሌሎች ደግና ለጋስ (ቸር) ነኝ:: | 1 | 2 | 3 | 4 |
| ነ/ ችግሮች ሲከሰቱ ደፋርነትን (ጀግንነትን) እና ጥንካሬን በተግባር አሳያለሁ:: | 1 | 2 | 3 | 4 |

4. ተማሪዎቹ የሰበሰቡትን መልሶች ተንትነው ግኝታቸውን በዘገባ (ሪፖርት) መልክ እንዲያቀርቡ አድርግ::

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

የሕዝብ አስተያየት ዳሰሳው (መጠይቅ) እንደየተማሪዎቹ እድሜና ብስለት ደረጃ ለትምህርት ቤት ወይም ለማህበረሰቡ ሊዘጋጅ ይችላል::

የዳሰሳ ጥያቄዎች የተገደቡ (closed) እንዲሆኑ የተፈለገው ዳታውን በቀላሉ ለመተንተን እንዲያስችል ነው:: ዳታ ለመሰብሰብ የበይነ መረብ ምንጮችን ለመጠቀም የሚያግዙ እንደ " survey monkey" የመሳሰሉ መሳሪያዎችን (tools) ጥቅም ላይ ማዋል ይችላል::ይህን መንገድ የሚጠቀሙ ከሆነ የማህበራዊ ሚዲያ ጓደኞቻቸውን (contacts) በመጠቀም የናሙና መጠናቸውን ከፍ

# የእኔ ቃል ኪዳን

## የትምህርት አይነት

- ስነ-ጥበብ(ትያትር)
- የስነ ዜጋ ትምህርት
- ስነ መንግስት

## ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

ዝቅተኛ (9ኛ እና 10ኛ) እና ከፍተኛ (11ኛ እና 12ኛ) ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

## የተመደበው ጊዜ

90 ደቂቃ

## አስፈላጊ ቁሳቁሶች

የሁኔታዎቹ ቅጅዎች እንደተመረጠው ሚዲያም (መንገድ) የሚወሰን ይሆናል፡፡

## ቁልፍ ቃላት

- ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ
- የሐቀኝነት ስርአት

## የትምህርቱ ውጤት

መልካም ሥነ-ምግባር በተላበሰ ባህሪ አማካኝነት ሐቀኛ አኗኗር (ህይዎት)መምራት፡፡

## ምክንያት (RATIONALE)

በዚህ መልመጃ ተማሪዎች በክፍል እና ከክፍል ውጭ ተፈጻሚ የሚሆን የሥነ-ምግባር መመሪያን (ኮድ) በተመለከተ ውይይት ያካሄዳሉ፡፡

## ሒደት

1. መምህሩ ተማሪዎችን በቡድን ከከፈሉ በኋላ ቡድኖቹ በክፍል ውስጥ እና ከክፍሉ ውጭ በሚኖር የትምህርት ቤት ሕይዎት ላይ ተግባራዊ በሚደረግ የሥነ-ምግባር መመሪያ ላይ እንዲያደርጉና በመቀጠልም ይህን መመሪያ እንዲያረቁ ይጠይቅ፡፡ ይህን በማድረግ ሂደት ውስጥ የሚከተሉትን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ ያስገቡ፡፡
   ሀ/ በት/ቤት ውስጥ የሥነ-ምግባር መመሪያ የመኖር ጠቀሜታዎች ምንድን ናቸው?
   ለ/ ከዚህ በፊት የተነሱ (የተከሰቱ)የሥነ-ምግባር ጉዳዮች ምንድን ናቸው?
   ሐ/ መበረታት የሌለበት (ተገቢ ያልሆነ) ባህሪ ምንድን ነው?
   መ/ መበረታት ያለበት ባህሪ ምንድን ነው?
   ሠ/ የመመሪያውን ተፈጻሚነት እንዴት ይከተታሉ (ይቆጣጠራሉ) ?
2. የማርቀቁ ስራ እንደተጠናቀቀ ተማሪዎች ረቂቅ የሥነ-ምግባር መመሪያቸውን ለጠቅላው የክፍል ተማሪ እንዲያጋሩ ጠይቃቸው፡፡
3. ተማሪዎቹ በክፍላቸው ላይ ተፈጻሚ የሚሆን የሥነ-ምግባር መመሪያን በተመለከተ ውይይት እንዲያደርጉ እና በመመሪያው ላይ በስምምነት እንዲወስኑ አበረታታቸው፡፡ መመሪያው በፖስተር በማህበራዊ ሚዲያ ወይም በሌላ የስነ ጥበብ ስራ አማካኝነት እንዲጋሩ ማድረግ ይችላል፡፡

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

ተማሪዎች የሥነ-ምግባር መመሪያ ምንነት ግለጽ ካልሆላቸው የመምህሩን የሥነ-ምግባር መመሪያ ካለ መምህሩ ይህንን መመሪያ በምሳሌነት ሊሰጣቸው (ሊያጋራቸው)ይችላል፡፡ አለበለዚያ ከማህበረሰቡ ወይም ሌሎች የሥነ-ምግባር መመሪያዎችን በምሳሌነት ሊጠቀም ይችላል፡፡

## ማጠናከሪያ

የሥነ-ምግባር መመሪያ በክፍሉ ተማሪዎች ለተወሰነ ጊዜ ሙከራ ላይ ይውላል፡፡ የሙከራ ጊዜው ሲጠናቀቅ ተማሪዎች ስለተሞክሯቸው ሊወያዩ እና በመመሪያው አስፈላጊ ማሻሻያ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ የመጨረስ የመመሪያ ረቂቅ ለዳሬክተሩ ሊቀርብ ይችላል፡፡ በተማሪዎች የተዘጋጀው መመሪያ ለክፍሉ ወይም ለት/ቤቱ በአጠቃላይ ተፈጻሚ የሚሆን የሥነ-ምግባር መመሪያ ለማዘጋጀት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፡፡

ተማሪዎች እንደ ፖለቲከኞች ፣ጠበቆች ፣ፖሊሶች ፣ ዶክተሮች ፣ ነርሶች ፣ የመንግስት ሰራተኞች ፣ የግንባታ ሰራተኞች እና ስፖርተኞች የመሰሳሰሉት የተለያዩ ባለሙያዎች የተለያዩ የሥነ-ምግባር መመሪያ ሊኖራቸው ይገባ እንደሆነ እንዲያስቡበት ማበረታታት ይችላ፡፡ መመሪያ ከሙያ ሙያ ሊለያይ ይገባል ብለው የሚያምኑ ከሆነ ምክንያቱን ጠይቅ፡፡ የተለያዩት አንቀጾች የትኞቹ ናቸው? ተማሪዎች በይነ መረብን ተጠቅመው የተለያዩ ሙያዎች የሥነ-ምግባር መመሪያዎችን (ደንቦችን) በመፈለግ የሙያዎች ልዩ የሆኑ የሐቀኝነት ችግሮች (አደጋዎች) እንዴት መፍተሄ እንደተቀመጠላቸው ማየት ይችላሉ፡፡



# በጋራ መስራት

## የትምህርት አይነት

- የሰውነት ማጎልመሻ ትምህርት
- የስነ ዜጋ ትምህርት
- ስነ መንግስት

## ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

ዝቅተኛ (9ኛ እና 10ኛ) እና ከፍተኛ (11ኛ እና 12ኛ) ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

## የተመደበው ጊዜ

ለእያንዳንዱ ጨዋታ 40 ደቂቃ

## አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ለሳተላይት ፊኛዎች ለፒራና ወንዝ ጣውላ በትር (ዘንግ) ኮኖች፡፡

## ቁልፍ ቃላት

- የሲቪክ (ዜጎች) ተሳትፎ
- ትብብር
- የግጭት አፈታት
- የሃላፊነት ስሜት

## የትምህርቱ ውጤት

ሐቀኝነትን ለማጠናከር በንቃት መሳተፍ እና የጋራ እርምጃ መውሰድ ፡፡

## ምክንያት (RATIONALE)

ብዙውን ጊዜ ሙስና የሃይል (አቅም) ያለመመጣጠን ባለበት ሁኔታ ውስጥ ስለሚከሰት ሙስናን ለማስቆም ለሚደረግ ጥረት ባለ ድርሻ አካላት በትብብር እንዲሰሩ ማበረታታት ወሳኝ ነው፡፡ በዚህ መልመጃ ተማሪዎች በትብብር ብቻ ሊከናወኑ የሚችሉ ሁለት (ሳተላይት እና ፒራና አሳ) ተግባራት ይሰጧቸዋል፡፡ በዚህም አማካኝነት ሐቀኝነትን የተመለከቱ ጉዳዮችን ለማስተናገድ (ለመፍታት)በትብብር መስራት ያለውን ወሳኝ ጠቀሜታ ይማራል፡፡

## ሒደት

ሳተላይት: ተማሪዎች በቡድን ከተከፈሉ እያንዳንዱ ክብ በመስራት አባላቱ ጨዋታው በሚከናወንበት ጊዜ ሁሉ እጅ ለእጅ ተያይዘው ይቆያሉ፡፡ በመቀጠልም መምህሩ በእያንዳንዱ ክበብ (circle) ውስጥ ፊኛወች (ballons) ይወረውራል፡፡

እያንዳንዱ ቡድን ፊኛው መሬት እንዳይነካ መከላከል አለበት፡፡ ፊኛው መሬት እንዲነካ ያደረገ ወይም እጃቸው የተላቀቀ አባላት፣ ያጋጠሙት ከጨዋታው (ውድድሩ) ይወገዳል፡፡ ፊኛው መሬታ ያልነካበት ከአንድ በላይ ቡድን ሲኖር መምህሩ ተጨማሪ ፊኛ ይወረውራል፡፡ መምህሩ አንድ ቡድን እስኪቀር ድረስ ተጨማሪ ፊኛ መወርወሩን መቀጠል ይኖርበታል፡፡

የፒራና ወንዝ (Piranha river): መምህሩ ሁለት ገመዶችን በ4ሜትር ርቀት ያጋድማል፡፡ ለተማሪዎች ገመዶቹ በፒራና አሳዎች የተሞላ ወንዝ ዳርቻዎችን እንደሚወክሉ (እንደሚያሳይ) ይገልጻል፡፡ በመቀጠልም መምህሩ የተወሰኑ ጣውላዎች በገመዶቹ ላይ ያጋድማል፡፡ (ድልድዮቹ በጣውላዎቹ ፋንታ ካርቶን ወረቀት ወዘተ መጠቀም ይችላል)፡፡

መምህሩ በመቀጠልም የጨዋታው አላማ ወንዙን ማቋረጥ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ተማሪዎች በቡድን ሆነው በወንዙ በአንደኛው የወንዙ ዳርቻ ይቆማሉ፡፡በአንድ ጊዜ የቡድኑ ግማሽ የሚሆኑት ተማሪዎች ብቻ በማሻገሪያው (ጣውላው) ሊቆም ይገባል፡፡ ወንዙን በስኬት ለማቋረጥ ፣ ተማሪዎቹ ወደ ፊት እና ወደ ኋላ በቅብብሎሽ መሻገሪያው (plank)ላይ መመላለስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ መምህሩ በውድድሩ ጊዜ መነጋገር እንደሌለ ሊገልጽ ይገባል፡፡ (መምህሩ ከላይ በተጠቀሱት ቁሳቁሶች ፋንታ እንደ ጆንያ ወይም የካርቶን ሳጥን ሊጠቀም ይችላል፡፡)

ተማሪዎቹ መሻገሪያዎቹን ለቀው መሬት እስካልነኩ ድረስ የተራቡት አሳዎች አያገኛቸውም፡፡ አላማው አንዳቸውም ወደ ወንዙ ሳይወድቁ ሁሉንም የቡድን አባላት ማሻገር ነው፡፡ መልመጃዎቹ እንደተጠናቀቁ መምህሩ አጠር ያለ የገለጻ ክፍለ ጊዜ በማዘጋጀት ትብብር እንዴት ሙስናን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመዋጋት አቅም እንደሚፈጥር ውይይት እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡ ሙስናን ለማስቆም ትብብር (በሕብረት መስራት)አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት በሙሰኛው እጅ ያለው ስልጣን / ሃይል/ ነው፡፡ በመጨረሻዎቹ በጨዋታዎቹ ጊዜ የትኛውን ሂደት (መንገድ) እንደተጠቀሙና ስለ ማዳመጥ ጠቀሜታ ውይይት ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

ልዩ የእንቅስቃሴ ፍላጎት (special mobility needs) ላላቸው ተማሪዎች በቀላሉ እና ደህንነታቸው ተጠብቆ መንቀሳቀስ የሚያስችላቸው ቦታ መኖሩን አረጋግጥ፡፡

## ማጠናከሪያ

ተማሪዎች ማህበራዊ ንቅናቄዎችን እና ሐቀኝነትን በማስፋፋት እና ማጠናከር በሕብረት (የጋራ) ተሳትፎ ሙስናን ለመታገል ስለነበራቸው ሚና ምርምር (ጥናት) ሊያከናውኑ ይችላሉ፡፡

# ለሚመለከተው ሁሉ

## የትምህርት አይነት

- ቋንቋ እና ስነ ጽሁፍ
- የስነ ዜጋ ትምህርት

## ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

ዝቅተኛ (9ኛ እና 10ኛ) እና ከፍተኛ (11ኛ እና 12ኛ) ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

## የተመደበው ጊዜ

60 ደቂቃ

## አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ምንም አያስፈልግም

## ቁልፍ ቃላት

- የሲቪክ (ዜጎች) ተሳትፎ
- ሚዲያ

## ማጠናከሪያ

መምህሩ ምርጥ የሚባለውን ደብዳቤ ለመለየት ተማሪዎቹ ድምጽ እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ተገቢ ሆኖ ሲገኝ እና የደህንነት ችግር የሚያስከትል ሲሆን ደብዳቤው እንዲላክ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## የትምህርቱ ውጤት

ሐቀኝነትን ለማጠናከር በንቃት መሳተፍ እና የጋራ ርምጃ መውሰድ ፡፡

## ምክንያት (RATIONALE)

አንዳንድ ጊዜ ሙስና የሚስፋፋው (የሚሰፍነው)ማንም ባለመቃዎሙ ወይም ተቃውሞው በበቂ ሁኔታ ውጤታማ ወይም ጠንካራ ባለመሆኑነው፡፡ ስጋትን ወይም አሳሳቢ የሆነን ነገር ለውሳኔ ሰጭዎች በጽሁፍ ማሳወቅ ለውጥን ለማነሳሳት ጠቃሚ መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡ በውሳኔ ሰጭዎች አጥጋቢ ምላሽ ካልተገኘ እና የደህንነት ችግር የሚያስከትል ከሆነ ጉዳዩን በማህበረሰቡ ውስጥ በስፋት እንዲነሳ ማድረግ ይችላል፡፡ በዚህ መልመጃ ተማሪዎች አንድን ሊፈታ የሚገባው የሐቀኝነት ችግር የሚመለከት ደብዳቤ ይጽፋሉ፡፡ በመቀጠልም በጽሁፍ የቀረበው አቤቱታ (ጥያቄ) እንዴት ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚችል ይወያያሉ። (ለምሳሌ ፡- ህዝቡን ለማንቃት በጋዜጣ ማውጣት ወይም በትክክል ታማኝ ወደ ሆነ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ሊላክ ይችላል፡፡)

## ሒደት

1. ተማሪዎችን በቡድን ካካፈልክ በኋላ ቡድኖቹ ለማህበረሰባቸው አስፈላጊ የሚባሉ የሐቀኝነት ችግሮችን ዝርዝር እንዲያዘጋጁ ጠይቅ (ከሐቀኝነት ገንቢ ድርጅቶች ጋር ያለ መስተጋብር ከተመለከትከው መልመጃ መነሻ ማግኘት ይቻላል)፡፡
   በመቀጠልም በተለየ መንገድ አሳሳቢ ነው የሚሉትን ጉዳይ መርጠው በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ እንዲወያይ አድርግ፡፡
   ሀ/ ይህ ለምንድን የሐቀኝነት ችግር (ጉዳይ) ሆነ? ለምን አሳሳቢ (አስፈላጊ) ጉዳይ ሆነ?
   ለ/ ያሉት ባለድርሻ አካላት እነማን ናቸው?
   ሐ/ መፍትሄ ሊሆን የሚችለው ምንድን ነው?
   መ/ ጉዳያችሁን የምታቀርቡት ለማን ነው?
   ሠ/ ጉዳዩ በምን መልኩ ሊቀርብ (ሊተላለፍ)ይችላል?
   ረ/ ምን አይነት ሙግቶች (መከራከሪያ) ልንጠቀም እንችላለን? (ዝርዝሩን በጽሁፍ ያስፍሩ)
2. እያንዳንዱ ቡድን ሁለት ደብዳቤ እንዲጽፍ አድርግ የመጀመሪያው ውሳኔ ሰጭውን መፍትሄ ወይም ለውጥ እንዲያመጣ የሚጠይቅ ሲሆን ፣ ሁለተኛው አሳሳቢ ነው ስለሚሉት ጉዳይ ማህበረሰብን የሚያነቃ (የሚያሳውቅ) እና ድጋፍ እንዲያደርግ (እንዲያግዝ)ግፊት የሚያደርግ ነው፡፡ ሁለት ደብዳቤዎች የበለጠ ውጤታማ ስለሚሆኑበት መንገድ ስልት ቀይሱ፡፡

   የመጀመሪያው ደብዳቤ የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ያስገባ:
   ሀ/ ደብዳቤውን የምትጽፉት ለማን ነው?
   ለ/ የተከሰተው ምንድን ነው? (ይህ ለውሳኔ ሰጭው ደብዳቤ እስከሚላክበት ድረስ የነበሩትን ምላሾች ይጨምራል)
   ሐ/ ውሳኔ አሰጣጡ የሐቀኝነት ጉድለት ያለበት ለምንድን ነው?
   መ/ በውሳኔው የተጎዳው ማን ነው? (ማረጋገጥ የሚችሉ በማስረጃ የተደገፈ የአጭርና የረጅም ጊዜ ተጽዕኖዎች)
   ሠ/ ተቀባይነት ያለው መፍትሄ ምንድን ነው?

   በሁለተኛው ደብዳቤ ተማሪዎች ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦችና ለመጀመሪያ ደብዳቤ የተሰጠ መልስ ካለ ሊያካትቱ ይገባል፡፡

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

መመህሩ ሶስት ደረጃዎች ያሉት የደብዳቤ አጻጻፍ ማለትም የደብዳቤውን የይዘት ንድፍ (መዋቀር) ፣ የደብዳቤው ረቂቅ እና የተጠናቀቀውን (የመጨረሻውን) ደብዳቤ የሚያካትት ስልት እንዲያስተዋውቃቸው ይመከራል፡፡ በተጨማሪም መምህሩ ተማሪዎቹ በደብዳቤ የሚያቀርቡትን ጥያቄ በተጨባጭ እውነት እንዲያስደግፉና በውሳኔ ሰጭው አመኔታን እንዲያገኙ ሊያበረታታ ይገባል፡፡ መምህሩ ይህን መልመጃ በታችኛው እርከን ላሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች እንዲስማሙ ለማድረግ ለአንድ ኩባንያ የሰራተኞቹን የስራ ሁኔታ (አያያዝ)ከልጆቹ ጉልበት ወይም ስራ የሚተርፍ ስለመሆኑና ያለመሆኑ እና አካባቢውን ለመጠበቅ ስለሚሰራ ተግባር የሚጠይቅ ደብዳቤ እንዲፅፉ ሊያበረታታ (ሊጠይቅ)ይችላል፡፡

# የአየር ንብረት ለውጥና ሐቅኝነት

## የትምህርት አይነት

- ጂኦግራፊ
- የስነ ዜጋ ትምህርት

## ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

ዝቅተኛ (9ኛ እና 10ኛ) እና ከፍተኛ (11ኛ እና 12ኛ) ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

## የተመደበው ጊዜ

60 ደቂቃ

## አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ምንም አያስፈልግም

## ቁልፍ ቃላት

- የአየር ንብረት ለውጥ

## የትምህርቱ ውጤት

ሐቅኝነትን ለማጠናከር በንቃት መሳተፍ እና የጋራ እርምጃ መውሰድ ፡፡

## ምክንያት (RATIONALE)

አንዳንድ የአየር ንብረት ለውጥ ለሁሉም ማህበረሰቦች የሐቅኝነት ፈተና ይጋረጣል። ይህ ተግባር የወደፊት ህይወታችን እንዴት በሐቅኝነት መምራት እንዳለብን ይመረምራል፡፡ ተማሪዎችን በቡድኖች ካፋፈልናቸው በኋላ ቡድኖቹ የአየር ንብረት ለውጥ ማይገደብ ከሆነ (የማንቆጣጠረው ከሆነ) የወደፊት ህይወታችን በምን መልኩ ሊጎዳ እንገሚችል እንዲወያዩ ጠይቅ እያንዳንዱ ቡድን ሃሳብ ለመላው የክፍል ተማሪዎች እንዲያጋራ አድርግ ተማሪዎች ሃሳቡን ማፍለቅ ካልቻሉ የሚቀጥሉትን ቃላት እንደ መነሻ ስጣቸው ምግብ ፣ እህል እራስን መቻል (የምግብ አቅርቦት ችግር) ፣ የከፋ የአየር ጠባይ መቀያየር ፣ ውሃ ፣ የሰዎች ስደት እና ጦርነት፤

ተማሪዎች በበለፀገ ማህበረሰብ የሚኖሩ ከሆኑ በድህነት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት እንዴት ሊጎዱ እንደሚችሉ ጠይቃቸው፡፡

ቡድኖቹን የሚከተሉትን እንዲመረምሩ አሳስባቸው

- የሚገጥሙን አጣብቂኞች (dilemms) ምንድን ናቸው (በህዝብ ትራንስፖርት ከመጠቀም ይልቅ በግል መኪና መንቀሳቀስ ለአየር ንብረት ለውጥ አስተዋጽኦ ካላቸው ኩባንያዎች ድጋፍ/ sponsorship/ መቀበል ወዘተ)
- ለካርቦን ልቀት የምናደርገውን አስተዋጽኦ (carbon foot print) ለመቀነስ፣ አኗኗራችንን ለመቀየር ልንወስዳቸው የምንችላቸው ርምጃዎች ምንድን ናቸው ?
- ሌሎች ሰዎችን እንዲሁም መሪዎችን የአየር ንብረት ለውጥን ለመቆጣጠር እንዲሰሩ ለማበረታታት በጋራ ልንወስደው የምንችለው ርምጃ ምንድን ነው? ተማሪዎች ሌሎች ለአየር ንብረት ለውጥ መፍትሄ የሚሆኑ እርምጃ እንዲወስዱ የሚያነሳሳ የግንዘቤ ፈጠራ አወና የግፊት ዘመቻ (ለምሳሌ፡- የት/ቤት ፣ስፖርት " ብሎግ" የበይነ መረብ ዘመቻ) እንዲያዘጋጁ አበራታታቸው፡፡

# የኔ "ቴድ ቶክ" (My Ted Talk)

### የትምህርት አይነት

- የመረጃ ቴክኖሎጂ
- ቋንቋና ጽሁፍ

### ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

ዝቅተኛ (9ኛ እና 10ኛ) እና ከፍተኛ (11ኛ እና 12ኛ) ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

### የተመደበው ጊዜ

90 ደቂቃ

### አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ምንም አያስፈልግም

### ቁልፍ ቃላት

- የሲቪክ የዜጎች ተሳትፎ
- ሚዲያ

## የትምህርቱ ውጤት

ሐቀኝነትን ለማጠናከር በንቃት መሳተፍ እና የጋራ እርምጃ መውሰድ ፡፡

## ምክንያት (RATIONALE)

ይህ መልመጃ ተማሪዎች በአደባባይ (በሰዎች ፊት) ንግግር ማድረግን እንዲለማመዱ እድል ይሰጣቸዋል፡፡ ይህም ስለ ሐቀኝነት ውጤታማ የሆነ ገለጻ እንዲያደርጉ ሰዎች ስለ ሐቀኝነት ግንዛቤ እንዲኖራቸው እና ለስኬቱም የጋራ እርምጃ እንዲወስዱ ለማነሳሳት በልበ ሙሉነት እንዲናገሩ አቅም ይፈጥራል፡፡

## ሒደት

1. ተማሪዎች ስለሐቀኝነት ድንቅ ንግግሮችን ለማድረግ የሚያስችሉ ርእሰ ጉዳዮችን እንዲጠቁሙ ጠይቅ (ጋብዝ) ለምሳሌ:- "ዩቲዩብ" ላይ "ansa speech an anti corporation book for children " 11 july 2020 እንዲመለከቱ መምከር
2. ተማሪዎች ንግገር ለማዘጋጀት እና ለማቅረብ ተመራጭ የሆነውን መንገድ እና ንግግር ሲኖሩት የሚገባው ነገሮች እና መግለጫዎች ምንነት ሃሳብ እንዲያቀርቡ አድርግ
3. ተማሪዎች በመረጡት ርእስ ላይ ንግግር እንዲጽፉ እና በክፍል ተማሪዎች ፊት እንዲያቀርቡ እንዲሁም ግብረ መልስ እንዲያገኙ አድርግ፡፡የተዘጋጀው ንግግር በታችኛው እርከን ላሉ ተማሪዎች በትንሹ 2 ደቂቃ እንዲሁም በላይኛው እርከን ለሚገኙት 4 ደቂቃ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

ማስታወሻ፡ የታዳሚው ተሳትፎ እና ተደራሽነትን ከፍ ለማድረግ መልመጃዎችን በክፍል ወይም ትምህርት ቤት አቀፍ ውድድር ሊከናወን ይገባል፡፡

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

የተማሪዎች ተነሳሽነት ከፍ እንዲል መምህሩ እንደ "Ted Talk" መሳሰሉ የአደባባይ ንግግሮች እና ናሙናዎችን ሊያሳያቸው ይችላል፡፡ ለንግግራቸው ሐቀኝነትን በተመለከተ ጉዳዩ በሚመርጡ ጊዜ ከላይ የተጠቀሰው የYoutube ቪዲዮ ጥሩ መነሻ እንዲኖራቸው ሊያግዝ ይችላል፡፡

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በራስ መተማመን የሚጎድላቸውን ተማሪዎች በቅርበት በመሆን ድጋፍ አድርግ፡፡ እንዲሁም ድምጹን አጉልቶ በማውጣት ቴክኒኮችን በተግባር አሳያቸው፡፡ የክፍሉ ተማሪዎች በቁጥር አነስተኛ ከሆኑ እያንዳንዱ ተማሪ ንግግር ሊያደርግ ይችላል፡፡ ይሁን እና የበዛ ቁጥር ካላቸው በጥንድ ወይም በቡድን ንግግር ማዘጋጀት እና አንድ አባል መርጠው እንዲያቀርብ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡

## ማጠናከሪያ

በተማሪዎች የቀረቡት ንግግሮች ጥራት በተለይም ድምጽን እና የሰውነት እንቅስቃሴ የሚያስተላልፉትን መልእክት (Body language) በተመለከተ ሌሎች ተማሪዎች ግምገማቸውን እንዲያቀርቡ ሊጋብዙ ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች ንግግራቸውን ቀርጸው በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ሊለጥፉ እና በሃገራቸው ያሉ ሌሎች ተማሪዎች እንዲሁም ወጣቶች እይታቸውን እና ሃሳባቸውን እንዲያጋሯቸው ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

# ምስሎች!

## የትምህርት አይነት

- የስነ ዜጋ ትምህርት
- ስነ ጥበብ
- የመረጃ ቴክኖሎጂ

## ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

ዝቅተኛ (9ኛ እና 10ኛ) እና ከፍተኛ (11ኛ እና 12ኛ) ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

## የተመደበው ጊዜ

80 ደቂቃ

## አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ካሜራ (ስማርት ስልኮች) ፣ኢንተርኔት እና ኮምፒዩተሮች፡፡

## ቁልፍ ቃላት

- የሲቪክ (ዜጎች) ተሳትፎ
- ሚዲያ

## የትምህርቱ ውጤት

ሐቀኝነትን ለማጠናከር በንቃት መሳተፍ እና የጋራ እርምጃ መውሰድ።

## ምክንያት (RATIONALE)

እያንዳንዱ ጊዜ ሙስና ተጎጂ አልባ ወንጀል ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ የሐቀኝነት ጉድለት እና ሙስና በማህበረሰቦች የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እድገት ላይ የሚያሳድረውን አሉታዊ ተጽእኖ ለማሳየት ምስሎች እና ቪዲዮዎች ሃይለኛ መሳሪያዎች ናቸው፡ ፡ በዚህም መልመጃ ተማሪዎች ይህ አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳዩ ምስሎችን እንዲመርጡ ያበረታታሉ፡፡ እነዚህ የድምጽ እና የምስል ግብአቶች ታሪክን ለመተረክ እና ሙስና በማህበረሰባቸው፣ በአካባቢያቸው ወይም በት/ቤታቸው ላይ ስለሚያስከትለው አሉታዊ ውጤቶች ግንዛቤን ለማሳደግ ውጤታማ ናቸው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ መምህራን ተማሪዎቻቸውን ፎቶ እና ቪዲዮ በሚነሱበት እና በሚቀርጹበት እንዲሁም በሚያጋሩበት ወቅት ሊያስታውሷቸው የሚገቡ የሥነ-ምግባር ጉዳዮችን በአጽንኦት ሊያስገነዝቧቸው ይገባል፡፡

## ሒደት

1. የሙስና አሉታዊ ውጤት (ተጽእኖ) የሚያሳዩትን ከ "ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል" የፎቶ የቡድን ውድድሮች የሚገኙትን ምስሎች ለተማሪዎችህ አሳይ፡፡ በ"Fliker" የሚገኘውን "Transparency International "Capture Corruption – Global photo competition" ተመልከት፡፡

   በተጨማሪ የሚከተለውን የትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል "Youth Photo Winner: Corruption, Toxic Waste and the Power of Photography" November 21 .2013 "ብሎግ ፖስት" ሊያሳያቸው ይችላል።

2. ተማሪዎቹ በቡድን ካደራጀክ በኋላ የሚከተሉትን አንድ ወይም ሁለት ምስሎችን እንዲመርጡ ከጠየቁ በኋላ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ላይ ይወያዩ።
   ሀ/ ፎቶዎቹ ምን አይነት ጉዳይን ያመለክታሉ?
   ለ/ እነዚህ ምስሎች ጉልበታም ወይንም ጠንካራ ተፅእኖ'እንዲኖራቸው ያደረጋቸው ምንድን ነው?
   ሐ/ ፎቶ ስናነሳና ስናጋራ ወይንም በበይነ መረብ ስንለጥፍ ልናስብባቸው የሚያስፈልጉን የሥነ-ምግባር ጉዳዮች ምንድን ናቸው?
3. ተማሪዎች በሚቀጥሉት ጥቂት ቀናት በሚኖሩበት ማህበረሰብ ውስጥ የሐቀኝነት ጉድለት ውስጥ የሚያመላክቱ ፎቶዎችን በካሜራ ወይም በስማራት ስልኮች እንዲያነሱ ጠይቅ።

4. በመቀጠልም ተማሪዎቹ ፎቶዎች በሚቀርቡበት አውደ ርዕይ ካዘጋጀህ በኋላ እያንዳንዱ ተማሪ የፎቶዎቹን ርዕስ ጉዳይ እና ያቀዱትን መልዕክት ላማስተላለፍ የተጠቀሙትን ቴክኒኮች እንዲያስረዱ ጋብዝ፡፡

5. በመጨረሻም ተማሪዎች በቡድን ሆነው ፎቶዎቻቸው እንዴት ሙስናን በውጤታማነት ለመታገል ጥቅም ላይ ሊያውሏቸው እንደሚችሉ እንዲወያዩ አድርግ፡፡

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

ኢንተርኔት ተደራሽ የማይሆን ከሆነ ተማሪዎች ፎቶ እንዲነሱ ካደረገ በኋላ ወይም እንደጋዜጣ ያሉ ሌሎች የፎቶ ምንጮችን ካገኘ የመጀመሪያውን ደረጃ (step)በመዝለል በሁለተኛው ደረጃ በተቀመጡት ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ማድረግ ትችላላህ አለበለዚያ መምህሩ ለሁለተኛ ደረጃ እንደ ስዕል መንገዶችን ሊጠቀም ይችላል፡፡ እንደ "ፕሮጀክተር" ወይም " ፕሪነተር" ያሉ መሳሪዎች ከሌሉ ተማሪዎች ስልካቸውን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡

## ማጠናከሪያ

ተማሪዎች የቀደሙ የፎቶ ውድድር አሸናፊዎች ምን እንዳነሳሳቸው(እንዳበረታታቸው)ሊያነቡ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ ፡
- የትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል "Capture Corruption: 18-30 Age Group Winners" August 17 2015 የሚለውን የበይነ መረብ ዘገባ መመልከት ትችላለህ፡፡ በተጨማሪም ፎቶዎቻቸውን ለውድድር ስለማቅረብ ሊያስቡ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፡- የ"Allard Prize" የፎቶ ውድድር ሰአንዱ ነው፡፡



# የማህበራዊ ሚዲያ ሃይል

## የትምህርት አይነት

- ቋንቋ እና ስነ ጽሁፍ
- የመረጃ ቴክኖሎጂ
- ሥነ-ምግባር

## ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

ዝቅተኛ (9ኛ እና 10ኛ) እና ከፍተኛ (11ኛ እና 12ኛ) ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

## የተመደበው ጊዜ

80 ደቂቃ

## አስፈላጊ ቁሳቁሶች

እቅድ በማውጣት ሂደት የሚያስፈልግ ግብአት አይኖርም ይሁንና ለመጨረሻዎቹ ደረጃዎች ኢንተርኔት እና እስማርት ስልክ ያስፈልጋል፡፡

## ቁልፍ ቃላት

- የሲቪክ (ዜጎች) ተሳትፎ
- ሚዲያ

## የትምህርቱ ውጤት

ሐቀኝነትን ለማጠናከር በንቃት መሳተፍ እና የጋራ እርምጃ መውሰድ፡፡

## ምክንያት (RATIONALE)

ምንም እንኳን ማህበራዊ ሚዲያእጅግ በጣም አስተማማኝ እና ከአድሎዎ የጸዳ የመረጃ ምንጭ ሊሆን ባይችልም መልእክት በሰፊው ለማስተላለፍ እና ሌሎችን ለማስተባበር ውጤታማ (ሃይለኛ) መሳሪያ ነው፡፡ በዚህ መረጃ ተማሪዎች ሙስናን ለመታገል (ለመከላከል) ያለመ የማህበራዊ ሚዲያ ዘመቻ ይቀርጻል፡፡

## ሒደት

1. ተማሪዎች በማህበራዊ ሚዲያ ያላቸውን መድረክ (platform)ስለ ሐቀኝነት ግንዛቤ የሚያስጨብጡ፣ ሐቀኝነት እንዲስፋፋ የሚቀሰቅሱ እና የሚያበረታቱ እንዲሁም የሚታገሉ ተጽእኖ ፈጣሪዎችን ከበይነ መረብ (ኢንተርኔት) ፈልገው እንዲያገኙ አሳስባቸው ስለሚከተሉት ጥያቄዎች እንዲያስቡ (እንዲያሰላስሉ)ይደረግ፡፡
   ሀ/ ተጽእኖ ፈጣሪዎች ስለ ሐቀኝነት የሚቀሰቅሱባቸው ፣ ግንዛቤ የሚያስጨብጣቸው እና ሐቀኝነት እንዲጎለብት የሚያበረታቱባቸው ናቸው ብለህ የምትገምታቸው ምሳሌዎች ምን ሊሆን ይችላሉ?
   ለ/ የሚያስተዋውቃቸውና የሚያበረታቷቸው እሴቶች ምንድን ነው?
   ሐ/ ይህ ጥረታቸው ታላሚ ያደረገው እነማንን ነው ? ወይም ተጽእኖ ሊያሳርፍባቸው የፈለጉትን ሰዎችና አካላት እነማን ናቸው?
   መ/ ተከታዮቻቸው ላይ ሊኖራቸው የሚችለው ተጽእኖ ምን ሊሆን ይችላል?
   ሠ/ በሰዎች ሥነ-ምግባር ላይ እየፈረዱ ወይም የሰዎችን ባህሪ እየገመገሙ ያሉ ተደረገው እናዳይታዩ ምን ማድረግ ይችላል ?
2. ተማሪዎች እጅግ አሳሳቢ ነው የሚሉትን ጉዳይ እንዲመርጡ አድርግ፡፡ ስለዚህ ጉዳይ በማህበራዊ ሚዲያ የወጡ ጽሁፎች አይተው ከሆነ እና ይህን ጉዳይ በተመለከተ ፈጽሞ የተለየ አመለካከት የያዙ ሰዎች የአቋማቸው መነሻ ምን ሊሆን እንደሚችል ጠይቃቸው፡፡
3. በመቀጠልም ተማሪዎች ለአንድ ተጽዕኖ ፈጣሪ የሚሆን ዘመቻ እንዲቀርጹ ጋብዝ፡፡ ይህን በማድረግ ሂደት የሚከተሉትን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ አስታውሳቸው፡፡
   ሀ/ ጉዳያችሁ (የዘመቻው አጀንዳ) ምንድን ነው?
   ለ/ ቁልፍ መልእክቶቻችሁ ምንድን ናቸው?
   ሐ/ መልእክት የምታስተላፉበት መንገድ ምንድን ነው?(ቪዲዮ ፣ ጽሁፍ ፣ ድምጽ ፣ ቃለመጠይቅ ወዘተ)
   መ/ ታዳሚዎቻችሁን የምታሳምኑት እንዴት ነው?

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

ተግባሩን (መልመጃውን) የበለጠ ግልጽ ለማድረግ መምህሩ እንደ መነሻ በማህበራዊ ሐቀኝነትን የሚያስተዋውቁ ታዋቂ ሰዎችን ወይም ተጽዕኖ ፈጣሪዎችን በምሳሌነት ሊሰጥ ይችላል፡፡ ምሳሌዎች በዚህ "B the change" "10 Celebrities Making an Impact as Socially Responsible Company Founders (አስር ማህበራዊ ሃላፊነታቸውን እየተወጡ ያሉ ታዋቂ የኩባንያ መስራቾች), 1 August 2016 በሚለው የድህረ ገጽ ዘገባ ማግኘት ይችላሉ፡፡ ተማሪዎች የሚያገኙ ከሆነ ሚዲያውን ራዲዮ እንዲሁም የሚቀርበውም በጽሁፍ መልክ እንዲሆን ማድረግ ይችላል፡፡

ለሁለተኛ ደረጃ (step) ተማሪዎች ኢንተርኔት የሚያገኙ ከሆነ እምነታቸውን የሚቃረን በማህበራዊ ሚዲያ የሚሰራጭ አሳሳች መረጃን ፈልገው እንዲያገኙ አድርግ የሚከተሉትን ጠቃሚ ምንጮች ሊሆን ይችላሉ፡፡

Sierra Filucci "How to Sport Fake News (and Teach Kids to be Media-Savvy)" common media , March 5 2021 (የፈጠራ ወሬ (ዜና) እንዴት መለየት እነደሚቻልና ልጆች ብልህ የሚዲያ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስተማር እንደሚቻል)፡፡

Jamie Waters, "Meet the man who want let the haters win", The Observer, 8 May 2022 . (ጥላቻ ያለባቸው ሰዎች እንዲያሸንፉ የማይፈቅደውን ሰው ተዋወቁት)

## ማጠናከሪያ

እድሜያቸው የሚፈቅድ ከሆነ እና ቀድመው እየተገበሩት ካለሆነ ተማሪዎች ከአካባቢው ታዋቂ ሰዎች ጋር ሐቀኝነትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በሕብረት ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ ወይም እንደ አማራጭ ስለ አሳሳች ፅሁፎች የተዘጋጀውን ዘገባ በማንበብ በማህበራዊ ሚዲያ የወጡ አሳሳች ፅሁፎችን ለመለየት ሊሞክሩ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በወጡት ፅሁፎች ላይ ለአስተያየት መረጃ አጸፋ ሊሆን (ሊቃወም)ይችላል ብለው በሚያምኑት መንገድ አስተያየት ሊፅፉ ይችላሉ፡፡

# የዜና ክፍለ ጊዜ (ሰዓት)

## የትምህርት አይነት

- ቋንቋ እና ስነ ጽሁፍ
- ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ
- ሚዲያ
- ጋዜጠኝነት

## ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

11ኛ እና 12ኛ ክፍል ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

## የተመደበው ጊዜ

በርካታ የትምህርት ክፍለ ጊዜዎች

## አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ምንም አያስፈልግም

## ቁልፍ ቃላት

- የሲቪክ የዜናዎች ተሳትፎ
- ሚዲያ

## የትምህርቱ ውጤት

ሐቀኝነትን ለማጠናከር በንቃት መሳተፍ እና የጋራ እርምጃ መውሰድ፡፡

## ምክንያት (RATIONALE)

ብዙውን ጊዜ የሙስና ተግባራትን ለመደበቅ ሆነ ብለው በሚደረጉ ጥረቶች የተነሳ እውነት የሚዘግብ ማንኛውም ጋዜጠኛ የሚያቀርበው ዘገባ ከፍተኛ የትክክለኝነት እና ሚዛናዊነት መመዘኛ እንዲያሟላ ይጠበቅበታል፡፡ በዚህ መልመጃ ተማሪዎች የተወሰኑ የምርመራ ጋዜጠኝነት ክህሎቶች ከቀሰሙ በኋላ እነዚህን ክህሎቶች ለሚያዘጋጁት የቲቪ ወይም ሬዲዮ ዜና ጥቅም ላይ ያውላሉ፡፡

## ሒደት

1. ተማሪዎች በቡድን ሆነው በአገራቸው ለተከናወነ ፕሮጀክት የተመደበ የመንግስት በጀት እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋለ ለማጣራት እየሞከሩ ያሉ መርማሪ ጋዜጠኞች እንደሆኑ እንዲያስቡ አሳስባቸው፡፡ በመቀጠልም የሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ እንዲወያዩ ጠይቅ፡፡
    - መርማሪ ጋዜጠኛ ሊያጋጥሙት የሚችሉ የሥነ-ምግባር ጉዳዮች ምንድን ናቸው?
    - ከምትመረምሯቸው ሰዎች (አካላት) የበለጠ (ከፍያለ) መመዘኛ (standares) ማሟላት ያለባችሁ ለምንድን ነው?
    - ማረጋገጥ የሚቻል ማስረጃ አስፈላጊነት ምክንያት ምንድን ነው?
    - የሰሚ ሰሚ ወይም ስማ በለው (አሉባልታ) ወሬ ምንድን ነው?
2. ቡድኖቹ በምርመራ ሪፖርት አቀራረብ ላይ መመሪያ ለማግኘት በራሳቸው ቋንቋ የኢንተርኔት ፍለጋ እንዲያደርጉ ጠይቋቸው እና ያገኙትን አጭር ማጠቃለያ ያዘጋጁ።
3. ቡድኖቹ የትኞቹን ጥያቄዎች እንደሚጠይቁ እና ማንን እንደሚጠይቁ የሚገልጽ እቅድ እንዲያዘጋጁ ይጠይቋቸው።
4. ቡድኖቹ ለለዩት የታማኝነት ጉዳይ የተለያዩ ምንጮችን፣ የስልክ ቃለመጠይቆችን ጨምሮ የድምጽ ወይም የምስል ዘገባ እንዲያዘጋጁ ይጠይቋቸው። ማስታወሻ፡ ለደህንነት ሲባል ይህ ሁሉ ምናባዊ ይሆናል እናም ማንኛውንም እውነተኛ ሰው አይጠቅስም ወይም አይለይም።
5. ቡድኖቹ ሪፖርታቸውን ለክፍሉ ያካፍሉ። መረጃው በህጋዊ መንገድ የተገኘ መሆኑን እና መረጃው መረጋገጡን በማጣራት አድማጮቹ የአርታኢነት ሚና ይወስዳሉ። ይህ ማስመሰል እንደሆነ በማሰብ ተማሪዎች ምናባዊ ምንጮችን እንዲፈጥሩ ይጠበቅባቸዋል።

## ማጠናከሪያ

መምህሩ ለተማሪዎች ገለጻ የሚያደርግ የምርምራ ጋዜጠኛ ሊጋብዝ ይችላል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች ታዋቂ ስለሆኑ የምርመራ ጋዜጠኞች አጠር ያለ ዳሰሳ (ጥናት) እንዲያከናውኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡

# የምንኖርበትን አለም የሚቀይር እቅድ

### የትምህርት አይነት

- የስነ ዜጋ ትምህርት

### ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

ዝቅተኛ (9ኛ እና 10ኛ) እና ከፍተኛ (11ኛ እና 12ኛ) ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

### የተመደበው ጊዜ

60 ደቂቃ እና እቅድ የሚቀርብበት ተጨማሪ ጊዜ

### አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ምንም አያስፈልግም

### ቁልፍ ቃላት

- የሲቪክ የዜጎች ተሳትፎ
- የሐቀኝነት ስርአት

## የትምህርቱ ውጤት

ሐቀኝነትን ለማጠናከር በንቃት መሳተፍ እና የጋራ ርምጃ መውሰድ ::

## ምክንያት (RATIONALE)

ሙስናን ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመዋጋት የፀረ ሙስና ታጋዮች ሙስናን የሚታገሉበትን እቅድ በሚቀረጽበት እና በሚተባበሩበት ጊዜ ሁሉ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር መስራት እና የተለያዩ አቀራረቦችን መጠቀም ያሻቸዋል፡፡ በዚህ መልመጃ ተማሪዎች ሐቀኝነትን የሚያስተዋውቁ የሚያበረታቱ እና የሚያጎለብቱ ተቋማትን የሚያካትት ዘመቻ መንደፍ (መቅረጽ) አለባቸው፡፡

## ሒደት

1. ተማሪዎች ጠንካራ ፍላጎት ያሳደረባቸው ማህበረሰባዊ ሐቀኝነትን የተመለከተ ጉዳይ ለይተው እንዲመርጡ አድርግ፡፡ ሐቀኝነት ላይ አትኩሮቱን ያደረገ አነስተኛ መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት አባል እንደሆኑ እንዲያስቡ ንገራቸው (መምህሩ ምሳሌ ማቅረብ ሊያስፈልገው ይችላል፡፡)
2. ተማሪዎች በመረጡት ጉዳይ መሰረት በቡድን እንዲመደቡ ካደረግክ በኋላ ከአስፈላጊው ጋር ለውጥ ማምጣት የሚያስችሉ እርምጃዎችን ለማቀድ የሚያስፈልጉ ሀሳቦችን እንዲለዋወጡ አድርግ፡፡ ይህን ለማድረግ የሚከተሉትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው፡፡
   ሀ/ ሊያማክራቸው ወይም ሊያሳትፏቸው የሚገቡ ተቋማት
   ለ/ ይህም ግንኙነት (ተሳትፎ) ምን መልክ ሊኖረው እንደሚገባ (ደብዳቤ ፣ ጽሁፍ ፣ ስብሰባዎች ወዘተ)
   ሐ/ እርምጃዎቹ ወይም ተግባራቱ መቼ እና በምን አይነት ቅደም ተከተል እንደሚከናወኑ
   መ/ የሚያስፈልጋቸው ግብአቶች ምንነት
   ሠ/ የሌሎች ዜጎችን በተለይም ዝቅተኛ ገብ ያላቸውን እና የሴቶችን ድጋፍ እንዴት ያገኛሉ?
3. የሚከተሏቸውን ደረጃዎች የሚዘረዝር የፅሁፍ መርሃግብር (እቅድ) እንዲያዘጋጁ አድርግ፡፡
4. እያንዳንዱ ቡድን የራሱን እቅድ እንዲያቀርብ እና ከሌሎቹ ቡድኖች ግብረ መልስ እንዲጠይቅ አድርግ፡፡

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

መምህሩ ቡድኖቹ ሊከተሏቸው የሚችሏቸውን ናሙናዎች (template) ምንድን ፣ ለምን (አላማዎች) ፣ እንዴት (ግብአቶች) እና መቼ ከሚሉት እርዕሶች ጋር ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ይህ በተለይም በታችኛው እርከን ላሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች ጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡

## ማጠናከሪያ

ተማሪዎች ካላቸው ግብአት አንጻር ያቀዱቸውን ተግባራት ዝርዝር በመከለስ እቅዳቸውን ሊተግብሩ እና እቅዳቸው ስለመሳካቱ የሚገመግሙበትን ዘዴ ይወስናል፡፡

---

ሰንጠረዥ 6
**ሙስናን በመቃወም ያጋለጡ ሴቶች ታሪኮች**

ቀጥለው የቀረቡት አነቃቂ (ቀስቃሽ) ታሪኮች ሕይወታቸውን ሳይቀር ሰውተው ሙስናን የታገሉ ሴቶች የሚመለከቱ ናቸው፡፡

ማርሊን ጋርሺያ ኢስፔራት (Marlene Garcia-Esperat): በፊሊፒንስ ሙስናን በመመርመር ላይ

እያለች የተገደለች ጋዜጠኛ ናት፡፡

ካትሪን ባልኮቫክ (Kathryn Bolkovac): A በቦሲኒያ ሄርዘጉቪና የተሰማራ የተመድ ወታደራዊ ሃይል በማስረጃ የተደገፈ የወሲብ ብዝበዛ (ዝውውርን)ያጋለጠች የተመድ የቀድሞ ሰራተኛ እና የዩኤስኤ የፖሊስ መኮንን ይህም ስራዋ "The Whistleblower" የሚል ፊልም ሊሰራለት የበቃ ነው፡፡

ለተጨማሪ መረጃ ፡- ማርሊን ጋርሺያየአስፔራትን በተመለከተ “The Road to Justice – A CPJ Special Report” available at: https://cpj.org/reports/2007/10/road/
እንዲሁም ካትሪን ቦልኮቫክን በተመለከተ በ2011 የተፃፈ መጽሐፍ “The whistleblower: sex trafficking, military contractors, and one woman’s fight for justice” https://archive.org/details/whistleblowersex0000bolk

# አሳታፊ (interactive) ሚዲያ መፍጠር

## የትምህርት አይነት

- የስነ ዜጋ ትምህርት
- የመረጃ ቴክኒክኖሎጂ

## ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

ዝቅተኛ (9ኛ እና 10ኛ) እና ከፍተኛ (11ኛ እና 12ኛ) ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

## የተመደበው ጊዜ

በርካታ የትምህርት ክፍለ ጊዜዎች

## አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ኮምፒተርሮችና እና ኢንተርኔት

## ቁልፍ ቃላት

- የሲቪክ የዜጎች ተሳትፎ
- ሚዲያ

## የትምህርቱ ውጤት

ሐቀኝነትን ለማጠናከር ንቁ ተሳትፎ እና የጋራ እርምጃን መውሰድ

## ምክንያት (RATIONALE)

ተማሪዎች ሙስና በማህበረሰባቸው ስለሚያመጣው ተጽእኖ እንዲያስቡ እና ይህን ተጽእኖ እንዲያስቡ እና ይህን ተጽእኖ የሚያመለክት የራሳቸውን አሳታፊ ሚዲያ እንዲፈጥሩ ይበረታታሉ፡፡

## ሒደት

1. ተማሪዎች ሙስና እንደ ጤና ፣ ትምህርት ፣ ዘላቂ የአካባቢ ደህንነት እና ለሁሉም ሚዛናዊ የሆነ እድል መፍጠር በመሳሰሉት የልማት እና ሰብአዊ መብቶች ላይ ስላለው ተጽእኖ እንዲያስቡ (እንዲያሰላስሉ) ጠይቃቸው አሳስባቸው፡፡
2. የሥነ-ምግባር (ሞራል) አጣብቂኞችን መጨመር የሚያስችሉ ወይም ሙስና እና የሐቀኝት እጦትን ሪፖርት ለማድረግ የሚያስችሉ ከታች የተጠቀሱ አይነት አሳታፊ መተግበሪያዎች ምሳሌ ስጥ፡፡
3. ሶፍትዌር የመጻፍ ክህሎት ያላቸው ተማሪዎች በጸረ ሙስና እና ሐቀኝነት ላይ የራሳቸውን መተግበሪያ እንዲፈጥሩ አድርግ ወጣቶች ሶፍትዌር የመጻፍ ክህሎትን ሲማሩና ይህን ክህሎት የህግ የበላይነትን የሚመለከቱ ጉዳዮችን ለመፍታት አገልግሎት ላይ ሲያውሉት የሚሳዩ ከታች ያሉት ቪዲዮዎች ላይ በመመስረት የሚዘጋጁትን የመተግበሪያ ይዘት ሊገቡ ይችላል፡፡
   - United Nations Office on Drugs and Crime, “Coding for a Better World”, video, YouTube, 9 August 2018.
   - United Nations Office on Drugs and Crime, “#Hackathon4Justice in Nigeria”, video, YouTube, 3 April 2019.

   መምህሩ ሶፍትዌር የመጻፍ (coding) ክፍሎች የሌላቸውን ተማሪዎች ሌላ ሚዲያ (ምሳሌ፡- የራዲዮ ፕሮግራም ፣ ፖድካስት ፣ የዩቲብ ቪዲዮ) እንዲጠቀሙ ሊያደርግ ይችላል፡፡

   በ Google play በሚገኙ አሳታፊ (interactive) መተግበሪያዎች :

   - Corruption Reporting App
   - Eye on Corruption
   - Pothole Africa
   - Moral IQ
   - Dilemma
   - ተጨማሪ መገልገያዎች ከ UNODC የትምህርትና ስልጠና መምሪያ መጨረሻ ላይ ይገኛሉ።

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

ኢንተርኔት / በይነ መረብ/ ማግኘት ለማይችሉ ተማሪዎች ሙስና በልማት እና ሰብአዊ መብቶች ላይ ስላለው ተጽእኖ እንዲያጠኑ ማስረጃ እንዲያሰባስቡ እና ማስረጃውን እንዲያወዳድሩ በማድረግ መልመጃዎችን ማስተካከል /ማጣጣም/ ይችላል።

# 3.3 የክፍል ውጭ መልመጃዎች

# የሐቀኝነት ሱቅ (መደብር)

### ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

11ኛ እና 12ኛ ክፍል ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

### አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ሱቁን ለመክፈት የሚያስፈልጉ እቃዎች

### ቁልፍ ቃላት

- ተጠያቂነት
- ስነምግባራዊነት
- ግልጸኝነት

## የትምህርቱ ውጤት

መልካም ሥነ-ምግባር በተላበሰ ባህሪ አማካኝነት ሐቀኛ አኗኗር መምራት

## ምክንያት (RATIONALE)

በዚህ መልመጃ ተማሪዎች ዘላቂ የሆነ የሐቀኝነት የሕይዎት መርሃቸው እንዳይሸረሸር የአጭር ጊዜ የጥቅም ጉጉትን (ፈተናን) መቋቋም ይለማመዳሉ፡፡ በተጨማሪም በህይዎት ውስጥ ለታማኝነት፣ ግልጸኝነት እና ተጠያቂነት አክብሮ (ዋጋ) መስጠትን ይማራሉ፡፡ ይህ ተግባር ተማሪዎችን ፣ መምህራንን እና ሌሎች የት/ቤቱ ባልደረባዎች ስለ ታማኝነት ዋጋ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ለማስቻል በትምህርት አመቱ መገባደጃ ላይ በሚከናወን ክብረ በአል ላይ ሊቀርብ ይችላል፡፡

## ሒደት

1. በትምህርት ቤቱ ውስጥ ከተማሪዎች ወይም ወላጆቻቸው በተለገሱ እንደ አሻንጉሊቶች ወይም ለመቅሰስ የሚሆኑ ምግቦች ያሉ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ሱቅ ይከፈቱ፡፡ በሸቀጦች ላይ ዋጋቸውን በመለጠፍ ይደርድሯቸው፡፡ እነዚህን ሸቀጦች መግዛት የፈለገ ተማሪ ቁጥጥር በሌለበት የታማኝነት የዋጋ መሰብሰቢያ ሳጥን ውስጥ ትክክለኛውን ዋጋ መጨመር ይገባቸዋል፡፡
2. በየሳምንቱ መጨረሻ መምህሩ በተመልካቾች ፊት (በአደባባይ) ሸቀጦችን እና ከሽያጭ የተገኘው ገንዘብ ተቆጥረው የሚቀርቡበት የሒሳብ ማጣራት ያከናውናል፡፡ መረጃውም በግልጽ እንዲታይ ሊደረግ ይገባል፡፡
3. መምህሩ ከጥቂት ሳምንት በኋላ ሰዎችን ማመን ያለማመን የሚፈጥርብንን ስሜት እና ስለ እነርሱ ያለንን አመለካከት ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ የተመለከተ ውይይትን መምራት አለብን፡፡

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

በተጨማሪም የመጨረሻው ውይይት ሰዎች ክትትል በሌለበትና ሊያዙ እንደማይችሉ እያወቁ ተግባራቸውን ሐቀኝነት ላይ የተመሰረተ መሆን ይችላል፡፡ ይህ የሚፈጥረው ስሜት ምንድን ነው? ሐቀኝነት እንዲሰፍን ህግ አስከባሪ አስፈላጊ ነው ብለው ያምኑ እንደሆነ ተማሪዎቹን ሊጠይቅ ይችላል፡፡ በመቀጠልም መምህሩ ያለ ቁጥጥር እና ሕግ አስከባሪ ሐቀኝነት በሕብረተሰቡ ፣ ማህበረሰቡ እና በክፍል ውስጥ እንዴት ሊመሰርት እንደሚችል ጥያቄ ሊሰነዝር ይችላል፡፡

## ማጠናከሪያ

ተማሪዎች ከመልመጃ በፊት እና በኋላ ስላላቸው ተሞክሮ ጽሁፍ እንዲያዘጋጁ ሊደረግ ይችላል፡፡



# የሐቀኝነት ክለቦች

### አላማ የተደረጉ ተማሪዎች

ዝቅተኛ (9ኛ እና 10ኛ) እና ከፍተኛ (11ኛ እና 12ኛ) ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

### አስፈላጊ ቁሳቁሶች

ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ አስፈላጊ ክፍሎችን እና መሳሪያዎች እንዲያገኙ አገዛ ሊፈልግ ይችላል፡፡

### ቁልፍ ቃላት

- የሲቪክ የዜጎች ተሳትፎ
- ውጤታማነት

## የትምህርቱ ውጤት

ሐቀኝነትን ለማጠናከር የነቃ ተሳትፎ እና የጋራ እርምጃን መውሰድ

## ምክንያት (RATIONALE)

ሙስናን ለመታገል ቁልፍ መሳሪያ ከሌሎች ጋር በትብብር መስራትና ትስስሮችን መፍጠር ነው፡፡ በዚህ መልመጃ ተማሪዎች ሐቀኝነት ተቋማትን ለማስተዋወቅና ለማስፋፋት የሐቀኝነት ክለቦችን ያቋቁማል፡፡

## ሒደት

1. የሐቀኝነትን ክለብ ምንነት ለተማሪዎች አስረዳ (የሐቀኝነት ክለብ ውሳኔ ሰጭዎች እና ዜጎች በስራቸው ሁሉ ሐቀኝነትን እንዲከተሉ እና ስለ ሐቀኝነት መስፋፋት የሚያገለግሉና በሐቀኝነት ላይ ያልተመሰረቱ ውሳኔዎችን የሚቃወሙ የተማሪዎች ስብስብ) (ቡድን) ነው፡፡)
2. ተማሪዎች የክለባቸውን ግቦች እንዲወስኑ እና ክለባቸውም የሚስፈልገውን የአደረጃጀት መዋቅር ለይተው እንዲያስቀምጡ ንገራቸው የአደረጃጀት ኮሚቴና አባልነት መሃላ ማዘጋጀት ሊያስፈልጋቸው ይችላል፡፡
3. በመቀጠልም የሐቀኝነት ክለብ ሊያከናውናቸው በሚችላቸው ዝግጅቶች ሃሳብ እንዲያቀርቡ ጠይቅ እነዚህ ዝግጅቶች በዚህ የስልጠና መምሪያ የተካተቱት እነንደ የሐቀኝነት ክብረ-በአልን ማዘጋጀት ወይም ለሐቀኝነት ግንባታ አስተዋጽኦ ካላቸው ተቋማት ወይም ድርጅቶች ንግግር የሚያቀርቡ ሰዎችን መጋበዝ ሊያጠቃልሉ ይችላሉ፡፡ በመቀጠልም ተማሪዎች እነዚህን የቀረቡ ሃሳቦች በመጀመሪያዎቹ ሶስት ወራት የሚከናወኑ መርሃ ግብሮች አካል እንዲያደርጓቸው ይመከራሉ፡፡

   "ኢንተግሪቲ አክሽን" (Integirity Action) ሐቀኝነት ክለቦች መመሪያ አዘጋጅቶ ተደራሽ ወይም ማውረድ (downloadable) እንዲቻል አድርጎ አቅርቧል፡፡ መመሪያውን ለማግኘት Integirity Action ላይ, "Integrity Clubs in Schools: A how-to-guide (according to young people)” (2022) የሚለውን ይመልከቱ፡፡

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

ሊከናወኑ የሚችሉ ተግባራት የሐቀኝነት ቀንን ማክበር ፣ ንግግሮችን ማቅረብ ፣ ተጋባዥ እንግዶችን መጥራት ፣ የአባላት መሃላ ማዘጋጀት ወይም በትምህርት ቤት ውስጥ ፓስተሮችን ማተም መለጠፍ የመሳሰሉትን ሊጠቀልሉ ይችላሉ፡፡

# መረጃን ለተሻለ አስተዳደር መጠቀም

## ኢላማ የተደረጉ ተማሪዎች

11ኛ እና 12ኛ ክፍል ላይ ያሉ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች

## አስፈላጊ ቁሳቁሶች

እንደየ ሚዲያው ይለያያል

## ቁልፍ ቃላት

- ተጠያቂነት
- የሲቪክ (ዜጎች) ተሳትፎ
- ሚዲያ
- ግልጸኝነት

## የትምህርቱ ውጤት

ሐቀኝነትን ለማጠናከር የነቃ ተሳትፎ እና የጋራ እርምጃን መውሰድ

## ምክንያት (RATIONALE)

ወጣቶች ግልጸኝነት ሐቀኝነትንና መታመንን (trust) ለመገንባት ያለውን ጠቀሜታ (ሚና) አቅልለው ሊመለከቱት ይችላሉ ፤ በተመሳሳይም ግልጸኝነትና ተጠያቂነት ሐቀኝነትን የሚገነቡበትን ሂደት (መንገድ) ላያውቁ ይችላሉ፡፡ ይህ ማህበረሰብ አቀፍ ተግባር ወጣቶች በትምህርት ቤታቸው አስተዳደር ውስጥ በንቃት የሚሳተፉበትን (አስተዋጽኦ የሚያበረክቱበትን) እና ት/ቤቱ ጥቅም ላይ ያዋላቸውን ግብአቶች (ሃብቶች) በማስረጃ ተመርኩዞ እንዲያሳይ የሚያበረክቱትን ሂደት (መንገድ) ያመላክታል፡፡

## ሒደት

1. ተማሪዎች የት/ቤቱን አስተዳደር ቀርበው የት/ቤቱ ስብሰባዎችን ወይም የእስኮላርሽፕ አሰጣጥን የመሰሉ ቁልፍ ውሳኔዎች በግልጽ የሚታዩበት የግልጸኝነት ሰሌዳ ማኑጽ የሚያስችላቸው ፈቃድ ይጠይቃሉ፡፡ መረጃው ከተሰበሰበ በኋላ በሰሌዳው ላይ ለሁሉም በሚታይ መልኩ በግልጽ ይለጠፋል፡፡
2. በመቀጠልም ተማሪዎች ሰሌዳው በይፋ የሚተዋወቅበትን (የሚመረቅበትን) ስነስርአት ያዘጋጃሉ፡፡ በስነ ስርአቱም ላይ የሰሌዳውን አላማና በሰሌዳው ላይ የቀረበው መረጃ (ለምሳሌ:- እንደ መነሻ የተጠየቀው የት/ቤቱ በጀት ሊበቃ ይችላል፡፡) እንዲሁም በየጊዜው መረጃው የሚሻሻልበትን መንገድ ያስረዳሉ፡፡
3. የቀረበው መረጃ እየጨመረ ሲመጣ ተማሪዎች መረጃውን እየተነተኑ በትንታኔው መሰረት ሃሳቦቻቸውን ወይም ምክሮችን (suggestion) ያቀርባሉ፡፡ ይህም የአስተዳደር አካላት ለፈጸሙት ተግባር ይፋዊ እውቅና መስጠት ብቻ ሳይሆን እነዚህ አካላት በቀረቡት ፕሮፖዛል ላይ የሕዝብ አስተያየት በሰሌዳው በኩል በሚጠይቁ ጊዜ የሕዝብን አስተያየት እና ጥቆማን ሊያካትት ይችላል፡፡

## ማስተካከል (ADAPTATION) / ጠቃሚ ጥቆማዎች (TIPS)

መረጃን ተደራሽ የማድረጊያ መንገድ በአካል የቆመ (የታነጸ) ሰሌዳ ብቻ አይደለም፡፡ አስፈላጊው ክህሎት ያላቸው ተማሪዎች የት/ቤታቸውን አስተዳዳሪዎች መረጃን በማደራጀት እና በድረገጽ ላይ እንዲወጣ በማድረግ ሊደግፉ ይችላሉ፡፡

## ማጠናከሪያ

ይህ መረጃ ተደራሽ ከሆነ በኋላ እና የት/ቤቱ አስተዳደር አካል በምርጫ የሚሰየም ከሆነ ተማሪዎች በአስተዳደሩ ስብሳቢዎ ላይ የሚታዩም የራሳቸውን ወኪል ሊመርጡ ይችላሉ፡፡

በተጨማሪም ተማሪዎች ይህ ዘዴ እንዴት በአካባቢያቸው በሰፊው ማህበረሰብ ውስጥ በሚገኙ ተቋማት (ድርጅቶች)ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚችል ጥያቄ ሊቀርብላቸው ይችላል፡፡ ለምሳሌ ይህ ዘዴ በአካባቢው ምክር ቤት ፕሮጀክቶች ወይም የስፖርት ክለቦች ላይ ተግባራዊ ሊደረግ ይችላል፡፡ተማሪዎች የተቆፈሩ (ውሃ ያቆሩ) መንገዶ (አስፋልቶች) ቁጥርና የሚገኙበት ቦታ የአካባቢው ክሊኒክ የሚዘጋባቸው ቀናት ቁጥር ወይም የክሊኒኩ የሕክምና ቁሳቁሶች መጠን የመሰሉ የማህበራዊ አገልግሎቶች አመላካከት (ማሳያ) መረጃዎችን ሊሰበስቡ ይችላል፡፡

ተማሪዎች መረጃውን ከመሰብሰባቸው እና ከማጋራታቸው በፊት መምህሩ የሰበሰበው መረጃ ትክክለኛ መሆኑን ማረጋገጥና ፍላጎት ላለው ሁሉ ለማጋራት ፈቃደኛ መሆናቸውን ያስፈለገበት ምክንያት እንዲያስረዱ መጠየቅ ይገባዋል፡፡ በተጨማሪም እንዴት ተጠያቂ ማድረግ እንደምንችል እና ይህን በምናደረግበት ጊዜም ከነሱ ሊመጣ የሚችለን አሉታው ምላሽ (Reaction) እንዴት ማስወገድ እንዳለብን የሚያስገነዝቡ ውይይት ማካሄድ ይገባል፡፡ ለማነቃቂያ (መነሻ) የሚያገለግሉ የሌሎች አገሮች የክፍት መረጃ አጠቃቀም ተሞክሮዎች በ UNESCO Intrnational institution for Education planning ድህረ ገጽ "Open school data" በሚለው ገጽ ላይ ይገኛል፡፡

በተጨማሪም በ Transparency International pamphlet: “Youth Civic Literacy: Participatory Budgets During the Covid-19 Pandemic” ተያያዥ መረጃን ማግኘት ይችላል፡፡

ክፍል 4

# የምዘና ዘዴዎችና መንገዶች



የተለያዩ የምዘና (ግምገማ) ዘዴዎችን መጠቀም ስለ ስልጠናው ስኬት(እድገት) የተሟላ ስእል (ግንዛቤ) እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ ለአለም አቀፍ የዜግነት ትምህርት አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን ለመመዘን ቁልፍ የሆኑ ዘዴዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡፡

## ሀ/ ግለ-ምዘና

ተማሪዎ ራሳቸውን በሚመዝኑበት (በሚገመግሙበት) ጊዜ ስለራሳቸው ያላቸው ግንዛቤ (መረዳት) ይዳብራል፡፡[1] የራሳቸውን ስራ ጥልቀት በተሞላበት እና ተጨባጭ በሆነ መንገድ እንዲመለከቱ የሚያበረታታቸው ሲሆን በተለይም ይህ ግለምዘና ከመምህሮቻቸው ጋር በተዘጋጀ የግምገማ ማዕቀፍ ውስጥ ሲከናወን የበለጠ ውጤታማ ይሆናል፡፡ ይህም በመደበኛነት ከተተገበረ ተማሪዎች በጊዜ ሂደት የሚኖራቸውን እድገት የሚያስተውሉበትን አቅም ያዳብራሉ፡፡

## ለ/ የተማሪዎች ግለ-ማስታወሻ

የተማሪዎች ግለ-ማስታወሻ (ጆርናል) ስለ ትምህርታቸው በጥልቀት የሚያሰላስሉበት መሳሪያ (መንገድ) ነው፡፡ እጅግ ተመራጭ የሆነው ግለ ማስታወሻ(ጆርናል) አወሳሰድ በመምህራን የተዘጋጀ መሪ (አመላካች) ጥያቄዎች መሰረት በእያንዳንዱ ትምህርት መጨረሻ የሚከናወነው ነው፡፡ ተማሪዎች ስለ ትምህርታቸው አካሄድ (እድገት) ተአማኒ እና ግልጽ በሆነ መንገድ እራሳቸውን እንዲመረምሩ ወይም ስለራሳቸው እንዲያሰላስሉ ግለ ማስታወሻቸው ሚስጥራዊ (private) ሊሆን ይገባል፡፡ ምንም እንኳን መምህራን የተማሪዎቻቸውን ጆርናል ማንበብ ባይችሉም ተማሪዎቹ ስለ ትምህርታቸው የሚያሰላስሉበት ጊዜ መመደባቸው በራሱ ስለ እውቀታቸው ፣ ክህሎታቸው እና እሴታቸው እንዲሁም በአለም ላይ ስላላቸው ቦታ የሚኖራቸው ግንዛቤ ይጎለብታል፡፡

## ሐ/ የአቻ ለአቻ ምዘና (ግምገማ)

የአቻ ለአቻ ምዘና ተማሪዎች ስራቸውን በተመለከተ እርስ በእርስ እንዲገማገሙ እና የማሻሻያ ግብረ መልስ እና ሃሳብ እንዲቀያየሩ እድል ይሰጣል፡፡ ገንቢ አስተያየት መስጠት እና መቀበል ቀድመን ልንማረው የሚገባ ጠቃሚ የኑሮ ክህሎ ነው፡፡ ልክ እንደ ግለ ምዘና ሁሉ የአቻ ለአቻ ምዘና ዘዴዎች የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል የሚያጠናክሩ ሲሆኑ ለዚህም ምክንያቱ ተግባራዊና አካታች መሆናቸውን ነው፡፡ ሁለቱም የምዘና መንገዶች እንደ ታማኝነት ፣ ሚዛናዊነት እና በማህበራዊ ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ልዩነት ካላቸው ሰዎች ጋር በሰላማዊ መንገድ መግባባት የሚያስችሉ አስፈላጊ ማህበራዊና ስሜታዊ (emotional) የትምህርት ክህሎቶችን ይገነባሉ፡፡

## መ/ የመምህር ክትትል

የትምህርት ውጤትና የእለት ተእለት የክፍል ተግባራት ገንቢ ምዘናዎች ለማህበራዊ የስሜትና ባህሪ ክህሎቶች ተፈጻሚ እንዲሆኑ የሚያስችል ሁኔታ ማስማማት ይችላል፡፡ ለምሳሌ፡- መምህሩ ተማሪዎችን የቡድን ስራ በሚታዘብበት ወቅት በተመሳሳይ ጊዜ ፣ የተግባቦት ፣ የትብብር እና ግጭትን የመፍታት ክህሎታቸውን መገምገም ይችላል፡፡ እንደ ብዝሃነትን የማክበር እና ሌሎችን እነደ ራስ የማየት(Empathy) መልካም ባህሪያትን የመምህር እና ተማሪ እና የተማሪ ለተማሪ ግንኙነቶች በመመልከት መገምገም ይችላል፡፡ የብቃት ተኮር መመዘኛ ተግባራትና ማዕቀፎችን ለማዋቀር የተለያዩ መንገዶች አሉ፡፡ በስራ ላይ ያሉ ማእቀፎች ከትምህርቱ ውጤቶች ጋር የተጣጣሙ መሆኑን ማጣራት (መመርመር) የመጀመሪያው አስፈላጊ እርምጃ ነው፡፡

## ሠ/ "ፖርትፎሊዮ" (PORTFOLIO)

”ፖርትፎሊዮ”የተማሪዎች ስራዎች ስብስብ ሲሆን የፈጠራ ስራን ፣ የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶችን እና ሌላ ናሙናዎችን ሊይዝ ይችላል፡፡ ስነ ጥበብ ላይ የተመሰረቱ የአለም አቀፍ ዜግነት ትምህርት ዘዴዎች ሲታሰቡ በጣም ውጤታማ ናቸው፡፡ ተማሪዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚያደርጉትን መሻሻል ለመገንዘብ ምሉዕ (Holistic) መንገድ (ዘዴ) በመሆን ያገለግላሉ፡፡ የባለቤትነት መንፈስ እንዲያድርባቸው በፖርትፎሊዮዎቻቸው ቢያንስ የመምረጥ እና የማካተት እድል ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

## ረ/ ፕሮጀክቶች

ተማሪ መር ፕሮጀክቶች ተማሪዎች የትምህርት (Cognitive) ፣ ማህበራዊ ፣ የስሜት እና የባህሪ እድገትን የሚያሳዩበት ጠቃሚ መንገድ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የአካባቢ ነዋሪዎችን የሚያሳትፉ የቡድን ፕሮጀክቶች የጠለቀና ምክንያታዊ አስተሳሰብ ፣ ችግር ፈቺ ፣ የተግባቦት እና አድቮኬሲ ክህሎቶችን እንዲሁም የሲቪክ ተግባራት እና/ወይም የፖለቲካ ተሳትፎ ልዩ ልዩ መንገዶች ግንዛቤን ለመገንባትና ለማጠናከር ያስችላል፡፡

1 UNESCO IBE (2017). Inclusive student assessment. Inclusive student assessment - UNESCO Digital Library

## ሰንጠረዥ 7
## ተማሪዎች ስለ ሐቀኝነት እና ተጓዳኝ ጽንሰ ሃሳቦችን የቀሰሙትን ትምህርት መገምገም (መመዘን)

ተማሪዎች ስለ እሴቶች የቀሰሙትን ትምህርት መገምገም ፈታኝ ነው፡፡ ምንም እንኳን ተማሪዎች ስለ ሐቀኝነት ፅንሰ ሃሳብ "እውቀት" ሊኖራቸው ቢችልም ሐቀኝነት የግድ የሕይወታቸው በተለይም የዕለት ተዕለት ባህሪያቸው አካል ይሆናል ማለት አይደለም፡፡ በተጨማሪም መምህራን የሰጡትን ትምህርት ውጤት ጊዜያዊ (ዘላቂ ያለሆነ) እና ተማሪዎቻቸው ከወሰዱት የሐቀኝነት ፅንሰ ሃሳብ የተቃራኒ ጠባይ ሲያሳዩ ሊያገኟቸው ይችላሉ፡፡ ሌላው አትኩሮት የሚያሻቸው ጉዳይ ምንም እንኳን አንዳንድ ተማሪዎች የትምህርት ውጤታቸው አጥጋቢ ላይሆን ቢችልም እጅግ ጠቃሚ (አስፈላጊ) የሆነው ትኩረት የሚያመጡት የባህሪ ለውጥ (ውጤት) ነው፡፡

በነዚህ ምክንያት ተማሪ ሐቀኛ መሆን ያለመሆኑን ለመወሰን ጥቅል ወይም ድምር ምዘናን ለመጠቀም መሞከር ተስማሚ (የላቀ) ዘዴ ላይሆን ይችላል፡፡ በተለይም ይህ ምዘና በመደበኛ የውጤት (ግሬድ) ምዘና ውስጥ የሚካተት የሚሆንበት ጊዜ ተመራጭ አይደለም፡፡ የተሸለው መንገድ የተገኘውን ውጤት ማጣራት ሲሆን ይህን መረጃ መጠቀም ያለብን የተመዘገቡትን መሻሻሎች (እድገቶች) ለመገንዘብ ብቻ ነው፡፡ በሌላ አባባል ይህ መረጃ ሊውል የሚገባውን ተማሪዎች የራሳቸውን እድገት (መሻሻል) እንዲገመግሙ እና መምህራን የትምህርት እቅዳቸውን መስራት ያለመስራቱን እንዲፈትሹ የሚያስችላቸው ጥረት ላይ ነው፡፡ ለጠቅላላ ምዘና (ግምገማ) በተለይም የተገኙ የባህሪ ውጤቶችን (ለውጦችን)ለመገምገም የግለ ምዘናን (ግምገማን) ወይም የአቻ ለአቻ ግምገማን መጠቀም ይመከራል፡፡ መምህራን በሚከተለው ምሳሌ ላይ በመመስረት ቀላል ጥያቄዎችን የያዘ መጠየቅ እንዲያዘጋጁ ይመከራል፡፡

### የተማሪዎች ራስን መገምገም

#### ከትምህርት (ከኮርሱ)በፊት

- ስለ ሐቀኝነት ተያያዥ ፅንሰ ሃሳቦች የነበረኝ ግንዛቤ ነበር፡፡
  ደካማ / መካከለኛ / ጥሩ/
- ሐቀኝነት ከባህል ጋር ስላለው ቁርጠኝነት እና የሐቀኝነት እጦት በማህበረሰባዊ ላይ ስለሚያመጣው ጉዳይ (ተፅዕኖ) የነበረኝ ግንዛቤ ነበር፡፡
  ደካማ / መካከለኛ / ጥሩ/
- ሐቀኝነት ውሳኔ አሰጣጥን የሚመራ መሰረታዊ እሴት ስለመሆኑ የነበረኝ ግንዛቤ
  ደካማ / መካከለኛ / ጥሩ/
- ከትምህርቱ (ስልጠናው) አስቀድሞ ሐቀኝነት በአካባቢየ እና ማህበረሰቤ ውስጥ ለማስፋፋት እና ለማስረጽ የሚያስችል አቅም እንደተፈጠረልኝ ይሰማኝ ነበር፡፡
  ደካማ / መካከለኛ / ጥሩ/
- ሐቀኝነትን ተግባራዊ እዳደረክ እና ሌሎችም ተመሳሳዩን እንዲያደርጉ እንድሚበረታቱ አምናለሁ፡፡
  አንዳንድ ጊዜ / ብዙ ጊዜ / ሁልጊዜ/

#### ከትምህርት (ኮርሱ) በኋላ

- አሁን የሐቀኝነትን ፅንሰ ሃሳብ ተጓዳኝ ቃላትን መገንዘብ ችያለሁ፡፡
  ፈፅሞ / በከፊል / ሙሉ በሙሉ
- አሁን ሐቀኝነት ከባህል ጋር ስላለው ቁርጠኝነት እና የሐቀኝነት ጉድለት በማህበረሰቡ ላይ ስለሚያሳድረው ጸፅዕኖ (ጉዳይ) ያለኝ ግንዛቤ:
  አልተሸሻለም / ተሸሽሏል / በእጅጉ ተሸሽሏል
- ሐቀኝነት ውሳኔ አሰጣጥን የሚመራ መሰረታዊ እሴት ስለመሆኑ ያለኝ ግንዛቤ ነው፡፡
  ደካማ / መካከለኛ / ጥሩ/
- ከትምህርቱ (ስልጠናው) በኋላ ሐቀኝነትን በአካባቢዬ እና ማህበረሰቤ ውስጥ ለማስፋፋት ለማስረጽ አቅም እንደተፈጠረልኝ ይሰማኛል፡፡
  አይ / ምን አልባት / አዎ
- ወደ ፊት ሐቀኝነትን ተግባራዊ እንደ ማድረግ እና ሌሎችም ተመሳሳዮን እንዲፈጽሙ እንደሚበረታታ አምናለሁ፡፡
  እንደ በፊቱ / ከበፊቱ በበለጠ / ከበፊቱ እጅግ በበለጠ/

# ዋቢዎች


Abbas, H. 2017. The Cultural Map: A Tool for Development and Peacebuilding. Arab Reform Initiative. https://www.arab-reform.net/en/node/1086 (Accessed 2 July 2019.)

Amnesty International. 2017. Human Rights Friendly School: A Toolkit. London, Amnesty, p. 11. https://www.amnesty.org/en/documents/pol32/6609/2017/en/ (Accessed 1 October 2018.)

Amnesty International. 2018. Write for Rights 2018 – A Human Rights Education Toolkit for Educators. London, Amnesty International. https://www.amnesty.org/en/documents/pol32/8969/2018/en/ (Accessed 13 January 2019.)

Bowman, E.W. 2017. Training Manual on Human Rights for Former Political Prisoners of Myanmar. Washington, DC, RFK Human Rights, p. 22. https://rfkhumanrights.org/assets/documents/Versione-Inglese-Finale-1-1.pdf (Accessed 29 January 2019.)

Council of Europe and PHZH - International Projects in Education. 2008. Teaching Democracy: A collection of models for democratic citizenship and human rights education (EDC/HRE). Vol 6. Gollob, R. and Krapf, P. (eds). Council of Europe Publishing, pp. 51–52. https://www.living-democracy.com/textbooks/volume-6/ (Accessed 14 January 2019.)

Council of Europe. 2009. Compasito: Manual on Human Rights Education for Children. N. Flowers (ed). Budapest, Council of Europe Directorate of Youth and Sport, pp. 103–108, 113-117 and 135-137. http://www.eycb.coe.int/compasito/pdf/Compasito%20EN.pdf (Accessed 20 October 2018.)

Council of Europe. 2015. Compass: Manual for Human Rights Education for Young People. Strasbourg, Council of Europe. https://www.coe.int/en/web/compass/throwing-stones (Accessed 14 January 2019.)

Derbaix, B. 2018. École Citoyenne. https://ecolecitoyenne.org/outils/regles/ (Accessed 2 September 2019.)

Equitas. 2015. Child Rights Fortune Teller. Montreal, Equitas. https://equitas.org/wp-content/uploads/2014/06/PIF-child-rights-fortune-teller.pdf (Accessed 28 January 2019.)

Flowers, N., Tolman, J., Bernbaum, M., and Rudelium-Palmer, K. 2000. The Human Rights Education Handbook: Effective Practices for Learning, Action and Change. Minneapolis, Human Rights Resource Center, University of Minnesota. http://hrlibrary.umn.edu/edumat/hreduseries/hrhandbook/activities/18.htm (Accessed 29 January 2019.)

Generation Human Rights. 2014. Sex Trafficking is Worldwide. Lesson One. New York. https://generationhumanrights.squarespace.com/lesson-one-sex-trafficking-is-worldwide (Accessed 29 January 2019.)

Generation Human Rights and Robert F. Kennedy Human Rights. 2016. The Refugee. Brooklyn, Generation Human Rights and Washington, DC, RFK Human Rights. https://generationhumanrights.squarespace.com/the-refugee-unit (Accessed 29 January 2019.)

IBE-UNESCO. 2017. Inclusive Student Assessment. Geneva, IBE-UNESCO. https://unesdoc.unesco.org/ark:/48223/pf0000250054 (Accessed 16 January 2019.)

IDP Foundation, Inc. 2018. Module 4: Developing and Teaching with Creative Low Cost Resources [Video]. https://www.youtube.com/watch?v=xVZaeVjaZF8&list=PLtbHivrgX6Jx0y7n4SM72TCjqjh9lvRnh&index=4 (Accessed 4 July 2019.)

Instituto Promundo. 2011. Em seu Lugar [In their place]. Sao Paulo: Promundo. https://promundo.org.br/recursos/em-seu-lugar/ (Accessed 4 February 2019.)

Instituto Promundo. 2016. Education and Sports for Equality. Rio de Janeiro, Instituto Promundo, p. 80. Full information on this resource can be found at: https://promundoglobal.org/wp-content/uploads/2016/07/PraticandoEsporte_Guia_24MAI.pdf

Integrity Action. 2016. Integrity Clubs Manual Outline. London, Integrity Action. https://integrityaction.org/what-we-are-learning/learning/integrity-clubs-guidebook/ (Accessed 28 January 2019.)

International Center for Alcohol Policies. 2013. Human Total: A Violence Prevention Learning Resource. Washington, DC, International Center for Alcohol Policies. https://www.iard.org/science-resources/detail/Human-Total-A-Violence-Prevention-Resource (Accessed 15 January 2019.)

Karuna Center for Peacebuilding. 2013. A Trainer's Guide to Inter-faith Peacebuilding in Sri Lanka. Amherst, MA, Karuna Center for Peacebuilding. http://www.karunacenter.org/uploads/9/6/8/0/9680374/___karunacenter-_inter-faith-tot-guide-2013.pdf (Accessed 14 January 2019.)

Masculino, C.J.V. 2017. Volunteers' queries raise transparency in school. CheckMySchool. https://checkmyschool.org/volunteers-queries-raise-transparency-in-schools/ (Accessed 26 January 2019.)

McLaughlin, K.A. and Brilliant, K.J. 1997. Healing the Hate: A National Hate Crime Prevention Curriculum for Middle Schools. Newton, MA, Education Development Center and Rockville, MD, Office of Juvenile Justice and Delinquency Prevention. https://www.ncjrs.gov/pdffiles1/165479.pdf (Acceesed 20 April 2019.)

Minero, Emelina. 2017. 13 Powerful SEL Activities. Edutopia. https://www.edutopia.org/article/13-powerful-sel-activities-emelina-minero (Accessed 28 January 2019.)

OSCE/ODIHR. 2012. Guidelines for Human Rights Education in Secondary School Systems. Warsaw, OSCE/ODIHR, pp. 35-36. https://www.osce.org/odihr/93969 (Accessed on 5 July 2019.)

OECD. 2018. Education for Integrity – Teaching on Anti-Corruption, Values and the Rule of Law. Paris, OECD, p. 27. https://www.oecd.org/governance/ethics/education-for-integrity-web.pdf (Accessed 14 January 2019.)

Oxfam. 2003. Get Global! A skills-based approach to active global Citizenship: Key stages three & four. (Section 1: Get global steps), p. 18 and p. 45. Full information on this resource can be found at: https://www.oxfam.org.uk/education/resources/get-global (Accessed 13 January 2019.)

Public Legal Education Association of Saskatchewan, Inc. 2006. Just law: Teaching youth about the law in their lives. Saskatchewan, PLEA. https://www.princealbertlibrary.ca/index.php/sm/search/item/367463 (Accessed 4 June 2019.)

Sentencing Council. 2019. Information for teachers: Understanding criminal sentencing in England and Wales – resources for teachers. London, The Sentencing Council for England and Wales, The Royal Courts of Justice. https://www.sentencingcouncil.org.uk/research-and-resources/resources-for-teachers/ (Accessed 14 January 2019.)

Republic of El Salvador Ministry of Education, Science and Technology. 2019. Disfruta y Cuidate en Internet. http://www.miportal.edu.sv/recomendaciones-y-buenas-practicas-para-el-uso-de-internet/ (Accessed 15 March 2019).

Robert F. Kennedy Human Rights. 2016. Speak Truth to Power: A Guide to Defending Human Rights. Washington, DC, RFK Human Rights. https://rfkhumanrights.org/assets/documents/Malala-Yousafzai062018.pdf (Accessed 10 March 2019.)

Street Law, Inc. Undated. High School Law Course. https://www.streetlaw.org/programs/high-school-law-course (Accessed 14 January 2019.)

Taranto Law Association. 2018. Legal Guide Between the School Desks (Guida Giuridica tra i Banchi di Scuola). https://www.oravta.it/site/images/pubblicazioni_vdm/Guida_Giuridica_sec.pdf (Accessed 11 January 2019.)

The Danish Institute of Human Rights. 2013. The Human Rights Education Toolbox. Copenhagen, The Danish Institute for Human Rights, pp. 94–97. https://www.humanrights.dk/publications/the-human-rights-education-toolbox (Accessed 13 January 2019.)

UNESCO. 2004. Changing Teaching Practices: Using curriculum differentiation to respond to students' diversity. Paris, UNESCO. http://unesdoc.unesco.org/images/0013/001365/136583e.pdf (Accessed 18 March 2019.)

UNESCO. 2014. Teaching Respect for All: Implementation guide. Paris, UNESCO, pp. 213–215. http://unesdoc.unesco.org/images/0022/002279/227983e.pdf (Accessed 14 January 2019.)

UNESCO. 2015. Global Citizenship Education: Topics and Learning Objectives. Paris, UNESCO. https://unesdoc.unesco.org/ark:/48223/pf0000232993?posInSet=1&queryId=ce7a17f4-d721-4ad9-8878-7712ad7f6189 (Accessed 5 December 2018.)

UNESCO. 2016. A Teacher's Guide on the Prevention of Violent Extremism. Paris, UNESCO. https://unesdoc.unesco.org/ark:/48223/pf0000244676 (Accessed 15 July 2019.)

UNESCO. 2017. Making textbook content inclusive: A focus on religion, gender, and culture. Paris, UNESCO. https://unesdoc.unesco.org/ark:/48223/pf0000247337 (Accessed 12 September 2019.)

UNESCO. 2018. Global Citizenship Education: Taking it Local. Paris: UNESCO. http://unesdoc.unesco.org/images/0026/002654/265456e.pdf (Accessed 16 December 2019)

UNESCO and UNODC. 2019. Strengthening the Rule of Law through Education: A Guide for Policymakers. Paris, UNESCO. https://unesdoc.unesco.org/ark:/48223/pf0000366771 (Accessed 11 March 2019.)

UNESCO Bangkok. 2006. Practical Tips for Teaching Large Classes: A Teacher's Guide. Embracing Diversity: A Toolkit for Creating Inclusive, Learning-Friendly Classrooms, Specialized Booklet 2. Bangkok, UNESCO. https://unesdoc.unesco.org/ark:/48223/pf0000148867 (Accessed 12 February 2019.)

UNESCO-IICBA . 2017. Transformative pedagogy for peace-building: A guide for teachers. Ethiopia: UNESCO, pp. 56-57. https://unesdoc.unesco.org/ark:/48223/pf0000261349 (Accessed 28 January 2019.)

UNODC. 2018. Promoting the rule of law through Model United Nations. https://www.unodc.org/e4j/en/model-united-nations/index.html (Accessed 13 January 2019.)

# አባሪ 1፡ የቁልፍ ቃላት መፈለጊያ

### ተጠያቂነት

- ተመጣጣኝ (ተገቢ) ወጭ ማውጣት
- መረጃን (ዳንታ) ለተሸለ አስተዳደር ማዋል

### የሲቪክ (የዜጋ) ተሳትፎ

- ሐቀኛኝነት ሰምልክቶች (አርአያዎች)
- ከተመልካችነት ወደ ማገዝ
- የኔ "ቴድ ቶክ" (Ted talk)
- ለሚመለከተው ሁሉ
- ምስሎች
- የማህበራዊ ሚዲያ ሃይል
- አለሜን የሚቀይር እቅድ
- የሐቀኝነት መልቲ ሚዲያ
- የሐቀኝነት ክለቦች
- ብሄራዊ ሐቀኝነት ስርአት
- በጋራ(በህብረት) መስራት
- አሳታፊ (interactive) ሚዲያ መፍጠር
- መረጃን (ዳታን) ለተሻለ ሰአስተዳደር ሰማዋል

### Conflict of interest

- We have a word for that!
- What would you do?
- Spending reasonably

### ግጭት አፈታት

- ግጭትን ማስተናገድ(Dealing with conflict)
- አሰርቲቭ ፣ ፓሲቭ ፣ አግረሲቭ

### ሙስና

- እኔ ምንም አልሆንኩም
- ምስሎች
- ለዚህ ስያሜ (ቃል) አለን

### ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔ አሰጣጥ

- እውነት ያሸንፋል
- የኔ ቃል ኪዳን

### ዖታ

- ዖታ እና ሙስና
- አሰርቲቭ ፣ ፓሲቭ ፣ አግረሲቭ

### ሚዲያ

- እውነቱ የትኛው ነው?
- የማህበራዊ ሚዲያ ሃይል
- የዜና ሰአት
- የኔ "ቴድ ቶክ" (My Ted talk)
- አሳታፊ (በይነተገናኝ) ሚዲያ መፍጠር

### ሰብአዊ መብቶች

- ዖታ እና ሙስና

### የሐቀኝነት ስርአት

- የብሄራዊ ሐቀኝነት ስራአት
- ሐቀኝነትን ከሚገነቡ ድርጅቶች ጋር ሰየሚኖር መስተጋብር
- የኔ ቃል ኪዳን ሰ

### ስፖርቶች

- ሐቀኝነት በስፖርት ውስጥ

### ግልፀኝነት

- እሴቶችህ ምንድን ናቸው?
- ተማጣጣኝ (ተገቢ) ወጭ ማውጣት
- መረጃን (ዳታን) ለተሸለ አስተዳደር መጠቀም

### ስሜትን መጋራት (Empathy)

- ተግባሮቼ (ስራዎቼ) እሴቶቼን ያንፀባርቃሉ?
- ከተመልካችነት ወደ አጋዥነት
- እኔ ምንም አልሆንኩም (አልደረሰብኝም)

### ሚዛናዊነት

- ሐቀኝት በስፖርት ውስጥ
- ተግባሮቼ (ስራዎቼ) እሴቶቼን ያንጸባርቃሉ?
- እሴቶችህ ምንድን ናቸው?
- የኔ ቃል ኪዳን

### ኃላፊነት

- ተግባሮቼ ሰእሴቶችን ያንፀባርቃል?
- ሰበቦች (ምክንያቶች)
- ከተመልካች ወደ አጋዥ
- እውነት ያሸንፋል
- እሴቶችህ ምንድን ናቸው?
- የኔ ቃል ኪዳን

# አባሪ II፡ የርዕሰ ጉዳይ መፈለጊያ

## ስነ ጥበብ

- የሐቀኝነት ትርጉም (ምንነት)
- ሐቀኝነት በስፖርት
- ሐቀኘኝነት ምልክቶች
- እውነት ያሸንፋል
- እኔ ምንም አልሆንኩም
- የኔ ቃል ኪዳን
- ሐቀኝነትን ማክበር (celebrity integrity)
- የግጭት አፈታት (አያያዝ)
- አሰርቲቭ ፣ ፓሲቭ ፣ አግረሲቭ
- የሐቀኝነት መልቲ ሚዲያ

## የሥነ-ምግባር ትምህርት

- የሐቀኝነት ትርጉም (ምንነት)
- ብሄራዊ የሐቀኝነት ስርአት
- እኔ ምንም አልሆንኩም
- የኔ ቃል ኪዳን
- ለሚመለከተው ሁሉ
- አየር ንብረት ላውጥ እና ሐቀኝነት
- ምስሎች
- አለሜን የሚቀይር እቅድ
- የሐቀኝነት መልቲ ሚዲያ

## ኢኮኖሚክስ

- ፆታና ሙስና
- እሴቶችህ ምንድን ናቸው?
- ተመጣጣኝ (ተገቢ) ወጭ ማውጣት
- መረጃን (ዳታን) ለተሸለ አስተዳደር ማዋል

## ጆኦግራፊ

- የአየር ንብረት ለውጥና ሐቀኝነት

## ታሪክ

- ብሄራዊ ሐቀኝነት ስርአት
- ሐቀኝነትን ከሚገነቡ ድርጅቶች ጋር ሚኖር መስተጋብር
- ፆታ እና ሙስና
- የሐቀኝነት ምልክቶች (ተምሳሌቶች)
- እሴቶችህ ምንድን ናቸው?
- ሐቀኝነትን ማክበር
- የግጭቶች አፈታት (አያያዝ)

## የመረጃ ቴክኖሎጂ

- የሐቀኝነት ምልክቶች (ተምሳሌቶች)
- ምስሎች
- የማህበራዊ ሚዲያ ሃይል
- የኔ "ቴድ ቶክ" (My Ted talk)
- የዜና ሰአት
- አሳታፊ ሚዲያን መፍጠር

## ቋንቋ እና ስነ ጽሁፍ

- የሐቀኝነት ትርጉም (ምንነት)
- ሐቀኝነት ምልክቶች (ተምሳሌቶች)
- ተግባሮቼ (ስራዎቼ) እሴቶቼን ያንጸባርቃሉ?
- ለዚህ ስያሜ (ቃል) አለን
- እውነቱ የትኛው ነው?
- አሰርቲቭ ፣ ፓሲቭ ፣ አግረሲቭ
- የኔ "ቴድ ቶክ" (My Ted talk)
- ለሚመለከተው ሁሉ
- የማህበራዊ ሚዲያ ሃይል
- የዜና ሰአት

## ሒሳብ

- እሴቶችህ ምንድን ናቸው?
- የሐቀኝት ሱቅ

## የሰውነት ማጎልበቻ ትምህርት

- ሐቀኝነት በሳፖርት
- በሕብረት (በጋራ) መስራት

## ሃይማኖት

- የሐቀኝነት ምልክቶች (በጋራ) መስራት
- ተግባሮቼ (ስራዎቼ) እሴቶቼን ያንጸባርቃሉ?

# አባሪ ။፡ የርዕሰ ጉዳይ መፈለጊያ

## ስነ ጥበብ

- የሐቀኝነት ትርጉም (ምንነት)
- ሐቀኝነት በስፖርት
- ሐቀኘኝነት ምልክቶች
- እውነት ያሸንፋል
- እኔ ምንም አልሆንኩም
- የኔ ቃል ኪዳን
- ሐቀኝነትን ማክበር (celebrity integrity)
- የግጭት አፈታት (አያያዝ)
- አሰርቲቭ ፣ ፓሲቭ ፣ አግረሲቭ
- የሐቀኝነት መልቲ ሚዲያ

## የሥነ-ምግባር ትምህርት

- የሐቀኝነት ትርጉም (ምንነት)
- ብሄራዊ የሐቀኝነት ስርአት
- እኔ ምንም አልሆንኩም
- የኔ ቃል ኪዳን
- ለሚመለከተው ሁሉ
- አየር ንብረት ላውጥ እና ሐቀኝነት
- ምስሎች
- አለሜን የሚቀይር እቅድ
- የሐቀኝነት መልቲ ሚዲያ

## ኢኮኖሚክስ

- ዖታና ሙስና
- እሴቶችህ ምንድን ናቸው?
- ተመጣጣኝ (ተገቢ) ወጭ ማውጣት
- መረጃን (ዳታን) ለተሸለ አስተዳደር ማዋል

## ጆኦግራፊ

- የአየር ንብረት ለውጥና ሐቀኝነት

## ታሪክ

- ብሄራዊ ሐቀኝነት ስርአት
- ሐቀኝነትን ከሚገነቡ ድርጅቶች ጋር ሚኖር መስተጋብር
- ዖታ እና ሙስና
- የሐቀኝነት ምልክቶች (ተምሳሌቶች)
- እሴቶችህ ምንድን ናቸው?
- ሐቀኝነትን ማክበር
- የግጭቶች አፈታት (አያያዝ)

## የመረጃ ቴክኖሎጂ

- የሐቀኝነት ምልክቶች (ተምሳሌቶች)
- ምስሎች
- የማህበራዊ ሚዲያ ሃይል
- የኔ "ቴድ ቶክ" (My Ted talk)
- የዜና ሰአት
- አሳታፊ ሚዲያን መፍጠር

## ቋንቋ እና ስነ ጽሁፍ

- የሐቀኝነት ትርጉም (ምንነት)
- ሐቀኝነት ምልክቶች (ተምሳሌቶች)
- ተግባሮቼ (ስራዎቼ) እሴቶቼን ያንጸባርቃሉ?
- ለዚህ ስያሜ (ቃል) አለን
- እውነቱ የትኛው ነው?
- አሰርቲቭ ፣ ፓሲቭ ፣ አግረሲቭ
- የኔ "ቴድ ቶክ" (My Ted talk)
- ለሚመለከተው ሁሉ
- የማህበራዊ ሚዲያ ሃይል
- የዜና ሰአት

## ሒሳብ

- እሴቶችህ ምንድን ናቸው?
- የሐቀኝት ሱቅ

## የሰውነት ማጎልበቻ ትምህርት

- ሐቀኝነት በሳፖርት
- በሕብረት (በጋራ) መስራት

## ሃይማኖት

- የሐቀኝነት ምልክቶች (በጋራ) መስራት
- ተግባሮቼ (ስራዎቼ) እሴቶቼን ያንጸባርቃሉ?

United Nations Educational, Scientific and Cultural Organization

GRACE Global Resource for Anti-Corruption Education and Youth Empowerment

United Nations Office on Drugs and Crime

# ተማሪዎችን ለፍትሃዊ ማህበረሰብ ግንባታ ማብቃት

## ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የተዘጋጀ የሐቀኝነት ማስተማሪያ

የትምህርት መሰረታዊ ጠቀሜታ የሚቀጥሉትን ትውልዶች እሴቶች በመቅረፅ እና በእውቀት ላይ የተመሰረተ ውሳኔ እንዲወስኑ በማስታጠቅ ለህብረተሰባቸው አወንታዊ ለውጥ የበኩላቸውን እንዲወጡ ማስቻል ነው። በእሴቶች መቀነስ የተነሳ በዓለምአቀፍ ደረጃ ቀውስ እየተከሰተ ሲሆን የዚህም መገለጫ የሙስና መስፋፋት ፣ አለመቻቻል እና ለዴሞክራሲ የሚደረገው ድጋፍ እየቀነሰ መምጣቱ ነው። ሙስናን ጨምሮ ወቅታዊ ተግዳሮቶች፣ ህዝቡ በአስተዳደር ላይ ያለውን እምነት ይሸረሽራል፣ በተለይም በትምህርት መስክ ውስጥ በጣም ተጠቃሚ መሆን ያለባቸውን ሰዎች ከሚያገለግሉበት ጠቃሚ ሀብቶች እንዲርቁ ያደርጋቸዋል።

እነዚህን ጉዳዮች ለመፍታት የትምህርት ሚና የላቀ ነው። ነገር ግን፣ በአለም አቀፍ የትምህርት የወደፊት ጊዜ (ፊውቸር) ኮሚሽን ሪፖርት ላይ እንደተገለጸው፣ ትምህርት ራሱ በመጀመሪያ መለወጥ አለበት። በዚህ በተለወጠው ትምህርት ውስጥ፣ ዓለም አቀፋዊ የዜግነት ትምህርት ህፃናት እና ወጣቶች ብልሹ አሰራሮችን እንዲከዱ እና የስነምግባር ደንቦችን እና የህብረተሰብ እሴቶችን እንዲያሳድጉ እውቀትን፣ ክህሎቶችን እና መርሆዎችን ማስታጠቅ ይችላል። የተማሪዎችን ንፁሕ አእምሮ መንከባከብ ቀደም ብሎ መጀመር አለበት። ወላጆች፣ ትምህርት ቤቶች እና ማህበረሰቦች በወሳኝ ማህበራዊነት ሂደት ውስጥ እነዚህን እሴቶች በማዳበር ይገባቸዋል።

ይህ ህትመት የተማሪዎችን ወሳኝ ብቃቶች እንደ ስነምግባራዊ አስተሳሰብ፣ ሂሳዊ አስተሳሰብ፣ የቡድን ስራ እና ሐቀኝነት የመሳሰሉ እሴቶችን የማስተማር ስልቶችን ለማሳደግ ያለመ የትምህርት መሳሪያዎችን፣ መልመጃዎቿን እና የትምህርት እቅዶችን ያቀርባል። ይህ ግብአት ሐቀኝነት ከማጠናከር ባለፈ ወጣቶችን ፍትሃዊ ማህበረሰቦችን እንዲፈጥሩ ሃይል ይሰጣቸዋ። ይህም ልዩነትን በማቻቻል በተለያዩ የእድገት ሁኔታዎች ውስጥ ለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አስተማሪዎች በዋጋ የማይተመን ድጋፍ ያደርጋል።

9 789231 006838

4 QUALITY EDUCATION

16 PEACE, JUSTICE AND STRONG INSTITUTIONS

Sustainable Development Goals